
መንግሥት ቅር እንደማይሰኝ አረጋግጦልኛል:: ...... የፈረንሣይ መንግሥት ባለው ጠቅላላ አመለካከት፣ የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች በጂኦግራፊና በታሪክ፣ በፖለቲካና በኤኮኖሚ ረገድ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ከፍተኛ ጉዳዮች መሆናቸውን ይገነዘባል:: ..... » ካለ በኋላ፤ ጣልያንና ኢትዮጵያ ተባብረው በጋራ ሞግዚትነት አሥመራንና ምፅዋን እንዲያስተዳድሩ ቢደረግ የተሻለ አይሆንም ወይ ? ሲል ሮበርት ሹማን የታላቋ ብሪታንያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጠየቀ:: ቤቨን ይህንን ሀሳብ አልተቀበለም:: « .... በዘርና በሀይማኖት የሚመሳሰለው የደጋው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር ሲቀላቀል፤ ከዚሁ ውስጥ አሥመራና ምፅዋ ተቆርጠው ሊወጡ አይችሉም:: የጣልያን ስጋት በአሥመራና በምፅዋ ለሚኖሩት ዜጎቿ ሲሆን፣ ኢትዮጵያም በዚያ ሠፈር የጣልያንን ሥልጣን ማየት አትፈልግም:: ለዚህ መፍትሔ የሚሆነው የጣልያን መንግሥት ኤርትራ እንዲመለስለት ያቀረበውን ጥያቄ ሠርዞ፣ ከኢትዮጵያ ጋር በኤኮኖሚና በልማት ረገድ ተባብሮ ለጋራ ጥቅም ለመሥራት የሚያስችል የሠላምና የወዳጅነት ስምምነት መመሥረት ነው:: ጣልያን ለዚህ ከተዘጋጀች፣ ኢትዮጵያም እንደምትቀበል አምናለሁ .... » ሲል ኧርነስት ቤቨን ሀሳቡን ደምድሟል::

የእንግሊዝና የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ለንደን ላይ ከተነጋገሩ ከአራት ወር በኋላ፣ የኤርትራ ጉዳይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መታየት ሲጀምር፣ እንግሊዞች ሀሳባቸውን አልለወጡም:: ያው ደጋግመው በተናገሩት ከአቆርዳት በስተቀር ሌሎቹ የኤርትራ አውራጃዎች ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀሉ በሚለው ሀሳብ ረግተዋል:: የፈረንሣይ አቋም ግን የጠራ መልክ ይዞ አልታየም:: በእርግጥ ኤርትራ ለጣልያን ይመለስ ማለቱን አቁሟል:: ስለ አሥመራና ምፅዋ ከተሞች አስተዳደር ግን፣ የጣልያን እጅ የሚገባበትን ዘዴ ለማግኘት እንደሚጥሩ ይታይባቸው ነበር::

ሚያዝያ 12 ቀን 1949 ዓ.ም አቶ አክሊሉ ለጃንሆይ በላኩት ቴሌግራም፣ ምንም እንኳን በፈረንሣይ ፖሊሲ መተማመን ባይቻል በኒውዮርክ የፈረንሣይ መልዕክተኞች መሪ የሆነው ሞሪስ ኩቭ ደሙርቪል ጨዋና አርቆ አስተዋይ ስለሆነ፣ ሊረዳን ይችላል በማለት፤ ተስፋ ማድረጋቸውን ገልጸው እንደነበረ ይታወሳል:: እንደዚህ ጨዋና አስተዋይ እያሉ የገኑበትና እምነት የጣሉበት ሰው፣ አቶ አክሊሉ እንደ አሰቡት ሆኖላቸው ይሆን ? የኤርትራን ታሪክ እየተከተልን ስንጓዝ ወደፊት እናየዋለን::

## የአምሳለ ገነት ጉባኤና ውሳኔ

ሐሙስ ሚያዝያ 7 ቀን 1949 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን በታላቋ ብሪታንያ እና በኢትዮጵያ ዋና መልዕክተኛ መካከል ስለተደረገው የአስተያየት ልውውጥ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ለጃንሆይ የላኩት ሪፖርትና የእንግሊዙ አምባሳደር ለአቶ ተፈራወርቅ የሰጠው ማስታወሻ ረቡዕ ሚያዝያ 13 ቀን 1949 ዓ.ም ሁለቱም በአንድነት ለንጉሠ ነገሥቱ ቀረቡ::



እጅግ የታወቀው የፋሽስት መምህር ኤንሪኮ ቸሩሊ

« ...... የሙሶሊኒ ወኪል ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ በሥልጣን ሲፈነጭ የነበረው፣ የታወቀው ፋሽስት ኤንሪኮ ቸሩሊ፣ ዛሬ አዲሲቷ የተባለችው ጣልያን መልዕክተኛ ሆኖ በተባበሩት መንግሥታት አዳራሽ ስናየው፡ ምን ያህል አሳፋሪ ድርጊት መሆኑን የማይገነዘብ ማነው? ....... »

(አክሊሉ ሀብተወልድ ኒውዮርክ ሚያዝያ 1949)

ጃንሆይ ከሁለቱም ወገን የተገለጹትን ጉዳዮች ሲመለከቱ ካመሹ በኋላ በማግሥቱ ሐሙስ ሚያዝያ 14 ቀን 1949 ዓ.ም ከጠዋቱ በሶስት ሰዓት በእምሻለ ገነት ቢሮአቸው ሆነው ውሳኔ ለመስጠት፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስን ጠሩ:: በዚሁ ሰዓት የጃንሆይ ልዩ ጸሐፊ አቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድና የጽሕፈት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር አቶ ገብረወልድ እንግዳወርቅ እንዲገኙ ተደርጓል::

« ...... የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ጣልያንን ለመርዳት አስቦ፣ ሱማሌን መልሶ እንዲያገኝ በዓለም ጉባኤ ፊቷ በመናገሩ፣ በጣም አዝናል:: አክሊሉ በዚህ ተቆጭቶ ኃይለኛ መልስ በመስጠቱ የእንግሊዝ መንግሥት ቅሬታ አድሮበታል ስለተባለውና ይኼ ጉዳይ እየከረረ ሲሄድ ወደፊት ስለሚሆነው ሀሳብህን ግለጥ ... » ሲሉ ንጉሠ ነገሥቱ ጸሐፊ ትእዛዛቸውን ጠየቁ::

ጃንሆይ እንደተናገሩት ጉዳዩን አጣርቶ መረዳት ተገቢ መሆኑን ወልደጊዮርጊስ ከጠቀሱ በኋላ « ...... የእንግሊዙ አምባሳደር የጻፈውን ማስታወሻ እኔ እንዳውቀው አቶ ተፈራወርቅ አስፈላጊ መስሎ ስላልታየው ኮፒ አልሰጠኝም:: ሆኖም ጃንሆይ አሁን በነገሩኝ ጉዳዩን ስለተረዳሁት፣ በመጀመሪያ የእንግሊዞችን የዲፕሎማሲ ጠባይ ደህና አድርጎ የሚያውቀው አቶ ተፈራወርቅ፣ በተለይ ለእሱ ታስቦ ስቀረበለት ማስታወሻ ምን እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ ሀሳብ ቢሰጠን የተገባ ይመስለኛል ..... » አሉ:: የወልደጊዮርጊስ ውስጠ ወይራ አነጋገር፣ መልዕክቱ ምን እንደሆነ ጃንሆይ ቢያውቁም፣ አቶ ተፈራ ወርቅ የተጠየቁትን እንዲመልሱ አዘዙ::

የጃንሆይ ልዩ ፀሐፊ፣ በተፈጥሮአቸው በቃል ንግግር አስተያየታቸውን አሳክተው ወይም በሰፊው አብራርተው የማቅረብ ልምድ ስለሌላቸው፣ ወልደጊዮርጊስ ለጠየቁት የሰጡት መልስ ቁንጽል ነበር:: « ..... የእንግሊዝ መንግሥት ወዳጅነት ለጃንሆይ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ፣ ለአምባሳደሩ የይቅርታ ደብዳቤ ቢጻፍለትና ክቡር አቶ አክሊሉም ለወደፊቱ ከእንግሊዝ ዋና መልዕክተኛ ጋር በወዳጅነት እንዲተባበር መምሪያ ቢላክለት የተገባ ይመስለኛል ..... » የሚል ሀሳብ አቀረቡ::

ወልደጊዮርጊስ ብው አሉ:: የምን ይቅርታ ? « ..... አቶ ተፈራወርቅ ጥሩ አድርጎ የሚያውቃቸው እንግሊዞች፣ በውነት የጃንሆይ ወዳጅ ቢሆኑ ኖሮ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ጣልያን ተመልሳ ሱማሌን እንድትይዝ ሀሳብ አቅራቢዎች አይሆኑም ነበር:: ኤርትራም በከፊል ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል እንደግፋለን የሚሉት፣ ጃንሆይ እንደሚያውቁት የምዕራቡን እውራጃ ወደ ራሳቸው ቅኝ ግዛት ወደ ሱዳን ለመጨመርና ባለፈው ሰሞን ትልቅ ሱማሌ እንፍጠር ብለው ሲዳንቱብን እንደከረሙት ሁሉ፣ አሁንም ትልቅ ሱዳን እያሉ ሊጮሁብን ስለአሰቡ ነው:: ...... አቶ ተፈራወርቅ ከእንግሊዙ አምባሳደር የተላከለትን ማስታወሻ በየዋህነት አክብሮ መቀበሉን ነው እንጂ የደብዳቤውን ትክክለኛ ዓላማ ጠልቆ አልተገነዘበውም:: እኔ እንደሚገባኝ ሁለት ዓላማ አለው::

1ኛ/ ከሁሉ በፊት በኒውዮርክ የታላቋ ብሪታንያ ዋና መልዕክተኛ ያቀረበውን ሀሳብ የጃንሆይ ሚኒስትር አጨብጭቦ አለመቀበል ብቻ ሳይሆን፣ ደህና አድርጎ በመቃወሙ፣ የእንግሊዝ አምባሳደር ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ ? በማለት በጣም መገረሙን ለማስረዳት ነው::

2ኛ/ በሱማሌና በኤርትራ ጉዳይ ላይ የቀረበውን ሀሳብ የጃንሆይ መንግሥት ተደስቶ ባይቀበልም፣ የእንግሊዝ መንግሥት ሊገፋበት የወሰነ መሆኑን፣ ዛቻው እንዲታወቅለት ነው::

...... በበኩሌ እዚህ ላይ ይቅርታ የሚያስጠይቅ ነገር አላይም:: አምባሳደሩም ከአቶ ተፈራወርቅ ጋር ባለው የቅርብ ወዳጅነት ይቅርታ እንዲጻፍለት በቃል ጠይቆ እንደሆነ አላውቅም:: በጻፈው ደብዳቤ ላይ ግን ይህን መንፈስ አላሳየም:: ደግሞ አንድ ነገር ስለ ወደፊቱ ሥራችን ማወቅ የሚያስፈልገው ጃንሆይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው በፖሊሲ ረገድ ተሳስቶ ከባድ ጥፋት ቢያደርስ እንኳን፣ ለአንድ አምባሳደር የይቅርታ ደብዳቤ አይጽፉም:: ይኼ ጉዳይ ዛሬም ነገም ወደፊትም ቋሚ መመሪያ መሆኑ መታወቅ አለበት:: አሁን ጃንሆይ ቢፈቅዱልኝ አቶ አክሊሉ ለእንግሊዙ መልዕክተኛ ንግግር ስለሰጠው መልስ አስተያየቴን አቀርባለሁ:: የግርማዊነትዎ ዋና መልዕክተኛ ለጉባኤው በሰጠው መግለጫ አንድም ጊዜ የእንግሊዝን መንግሥት ስም ጠቅሶ አልነቀፈም:: የተናገራቸውንም ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች ስንመለከት፣

1ኛ/ ጣልያን ሱማሌ ላይ ስትመለስ ኢትዮጵያ ዝም ብላ አትመለከትም ብሏል:: ይኼ ትክክለኛ የጃንሆይ ፖሊሲ ነው::

2ኛ/ ካለፉት ስምንት ዓመታት ጀምሮ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ የጠየቀው ፍርድ፣ ከእናቱ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀድ ነው ብሏል:: ይኼም የማይካድ ትክክለኛ ነገር ነው:: ጃንሆይም ያዘዙት ይህንን መሠረት አድርጎ በዓለም ጉባኤ ፊት እንዲከራከርበት ነው::

3ኛ/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የታላላቅ አገሮችን ብቻ ሳይሆን የታናናሽ አገሮችንም ጉዳይ በእኩል ደረጃ መመልከት አለበት ብሏል:: ይኼም ጃንሆይ ከዛሬ አሥራ ሶስት ዓመት በፊት ዤኔቭ ላይ ለመላው ዓለም የተናገሩት ትንቢትና ኋላም ደርሶ በታሪክ የታየ ነው:: አቶ አክሊሉም ይህንን መጥቀሱ የሚገባ ነው:: እንግዲህ እንግሊዞችን ያስቀየመው፣ ወይም አቶ ተፈራወርቅ የእነሱን ስሜት እንደተረጐመው ቅር የተሰኙበት ጉዳይ ምኑ ይሆን ? እንደ እውነቱ የሆነ እንደሆነ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ስለ ሱማሌ ጉዳይ ኢትዮጵያን የሚጐዳ ሀሳብ በማቅረቡ መቀየም የሚገባቸው ጃንሆይ ናቸው:: ይኸ ሳይሆን ቀርቶ የተገላቢጦሽ ተቀያማዎቹ እንግሊዞች ከሆኑ እንግዲህ ምን ይደረግ ? ባለጊዜዎቹ እነሱ ናቸው:: እስከሚያልፍላቸው ዝም ብለን በትዕግሥት ከማየት በስተቀር ምን ማድረግ እንችላለን ? ...... » የሚል ጥያቄ በማቅረብ ወልደጊዮርጊስ አስተያየታቸውን ደመደሙ::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከልዩ ጸሐፊያቸው የቀረበውን ይቅርታ የመጠየቅ ሀሳብና ከጸሐፊ ትእዛዛቸው የተገለጸውን ስፊ ትችት ካዳመጡ በኋላ፣ የሚከተለውን መምሪያና ውሳኔ ሰጡ::

« ..... ወልደጊዮርጊስ የተናገርከው የእኛን ሀሳብ የተከተለ ነው:: አክሊሉ ከኒውዮርክ የላከልንን ማስታወሻና የእንግሊዝ አምባሳደር ለተፈራወርቅ የጻፈውን በተመለከትን ጊዜ፣ የእንግሊዝን መንግሥት ቅር የሚያሰኝ ነገር አለመኖሩን እኛም አይተናል:: እንዲያውም አክሊሉ ጠንክሮ የኛን ሀሳብ በማስረዳቱ ማለፊያ ሥራ

ሠርቷል:: አምባሳደሩም ቢሆን የእንግሊዝ መንግሥት ይቅርታ እንዲጠየቅ ያስፈልጋል ብሎ በደብዳቤው ላይ ፍንጭ አልሰጠም:: ተፈራወርቅ ግን ይቅርታ ቢጻፍ ይሻላል ብሎ ሀሳብ ሲያቀርብ ወደፊት ላለብን ከፍተኛ ሥራ የእንግሊዝ መንግሥት በዚህ ቂም ይዞ እንቅፋት እንዳይሆንብን ሰግቶ ነው:: እንተም (ወ.ጊ) ደህና አድርገህ እንዳመለከትከን አሁን በደብዳቤም ሆነ በቃል ይቅርታ የሚል ነገር አያሻም:: ይቅርታ ያስፈልጋል ቢባል እንኳን እኛ የምንጽፈው ለእንግሊዝ ንጉሥ ነው እንጂ ለአምባሳደሩ አደለም:: አሁን በትላቁ የሚያሳስቡን ሁለት ነገሮች ናቸው:: የመጀመሪያው፣ ጣልያን ተመልሶ ሱማሌን ያስተዳድር የተባለው ነገር ነው:: በዚህ ነገር የተባበሩት መንግሥታቶች እንዳይስማሙበት፣ አክሊሉ የኛን ሀሳብ እያስረዳ መከራከሩን እንዲቀጥል ትእዛዛችን ይተላለፍለት:: በሚያደርገውም ንግግር እኛ የምንቃወመው፣ የታወቀውን ጠላታችንን ጣልያንን እንጂ፣ እንግሊዞችን በፍቅር ዓይን የምንመለከታቸው መሆኑን እንዲረዱት ያድርግ::

..... ሁለተኛው፣ በኤርትራ ዋና ጉዳያችን ላይ አገሩ በሁለት ይከፈል የተባለው ነው:: የተባበሩት መንግሥታቶች ጠልቀው እንዲያውቁት የሚያስፈልገው፣ አንድ ሆኖ የኖረውን አገር በሀይማኖት መከፋፈል የማይገባና፣ ይኼም እደራረግ ለመላው ዓለም ሠላም መጥፎ ምሣሌ መሆኑን ነው:: በዚህ ጉዳይ አክሊሉ የኛን ሀሳብ በረኸሙ ማስረዳት አለበት:: የኤርትራን ሕዝብ በሀይማኖት ምክንያት ሁለት ላይ መክፈል ከእኛም ከሕዝባችንም አልተጠየቀም:: ለዚህም ሆነ ለዚያኛው ጉዳይ፣ መምሪያችንና ውሳኔያችን ለአክሊሉ በቴሌግራም ዛሬውኑ እንዲላክለት ገብረወልድ አዘጋጅቶ ያቅርብልን:: ....... »

ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ እጅ ነስተው የንጉሠ ነገሥቱን ውሳኔ ከተቀበሉ በኋላ፣ አንድ የሚጨመር ስለአለ ይፈቀድልኝ አሉ:: « ..... በኤርትራና በሱማሌ ጉዳይ ለዋናው መልዕክተኛዎ ለአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ጃንሆይ የሰጡት ኃላፊነትና የጣሉበት አደራ በጣም ሰፊና በጣምም ከባድ ነው:: ጃንሆይ እንደሚያውቁት፣ ይህን ትልቁን የኤርትራ ጉዳይ ካለፈው አራት ዓመት ጀምሮ በዳኝነት የሚያዩት የአራቱ ታላላቅ መንግሥታት ወኪሎች ነበሩ:: አሁን እነሱ ስለአቃታቸው ጉዳዩ ወደ ዓለም ማህበር ተዛውሮ በስልሣ መንግሥታት እንደራሴዎች መታየት ጀምሯል:: ስለዚህ የግርማዊነትዎ ዋና መልዕክተኛ የሚሟገተው ከአራት አገሮች ጋር መሆኑ ቀርቶ ከስልሣ (60) አገሮች ጋር ስለሆነ፣ የጃንሆይን አደራ በሚገባ ለመፈጸም የተለየ ሥልጣን እንዲሰጠው ያስፈልጋል:: በእኔ በኩል የተለየ ሥልጣን የምለው አሁን በደረሰው ዓይነት፣ አቶ አክሊሉ ለጃንሆይ ክብርና ላገር ጥቅም ከተንከለኞች መንግሥታቶች ጋር በተሟገተ ቁጥር፣ እንግሊዝ እንዳይቀየም፣ አሜሪካ እንዳያዝን፣ ፈረንሣይ እንዳያኮርፍ የትኛው ይጐዳናል የትኛው ይጠቅመናል እያለ በየጊዜው ዝርዝር መምሪያ በመጠየቅ፣ ሥራው እንዳይጓተትበት ነው:: ስለዚህ ከጃንሆይ የተሰጠውን መሠረታዊ መምሪያና ከፍተኛ አደራ ተከትሎ በዝርዝሩ ጉዳይ እንደ አስፈላጊነቱ አራሱ በቦታው ላይ እየወሰነ ቢሠራ ይሻላል:: ቀጥሎ ደግሞ፣ የአንዳንድ መንግሥታት አምባሳደሮች በኒውዮርኩ ጉባኤ ላይ የጃንሆይ ዋና መልዕክተኛ በተናገረ ቁጥር፣ መንግሥታችን ቅሬታ ተሰምቶታል እያሉ የሚያመለክቱት ነገር ካላቸው፣ ጉዳዩን በጽሑፍም ሆነ በቃል ማቅረብ ያለባቸው አግባቡ ለሆነው ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንጂ፣ <u>የግርማዊነትዎን ልዩ ጽሕፈት ቤት እየደፈሩ በቀጥታ ወደ ቤተመንግሥት መምጣት</u> የለባቸውም:: ይህ ሥርዓት በመላው ዓለም የሚሠራበት ስለሆነ፣ ጃንሆይ የሚደክሙላት ኢትዮጵያም ከሌላው የምትለይበት ምክንያት የለም:: ሀሳቤን ለማጠቃለል የግርማዊነትዎን መልካም ፈቃድና ትእዛዝ የምለምነው፤

1ኛ/ አቶ አክሊሉ፣ ጣልያን እንደገና ወደ ሱማሌ መመለስ የለባትም:: ኤርትራም በሁለት አትከፈልም ብሎ የሰጠው መግለጫ ተገቢ መሆኑን፣

2ኛ/ መልዕክተኛዎ በኤርትራና በሱማሌ ጉዳይ ከጃንሆይ የተሰጠውን ዋና መምሪያ ተከትሎ፣ ስለአፈጻጸሙ ዝርዝር ጉዳይ እሱ በሚመስለውና ይጠቅማል ብሎ ባመነበት የዲፕሎማሲ ጥበብ ሥራውን ለማከናወን ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን፣

3ኛ/ አዲስ አበባ ያሉት የውጭ አገር መንግሥታት አምባሳደሮች ሚኒስትሮችና ቆንስሎች፣ ከየመንግሥታቸው የተላከ መልዕክትም አስተያየትም ቢኖር በቀጥታ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ ነው እንጂ፣ ድንበርና ወግ እየጣሱ ግርማዊነትዎ ልዩ ጽሕፈት መምጣት የሌለባቸው መሆኑን የሚገልጽ ቋሚ መምሪያ እንዲሰጥ ነው:: ...... »

ጃንሆይ በሁለቱ ሀሳቦች ተስማምተው ሶስተኛውን ለጊዜው ይቆይ አሉ:: « ...... አክሊሉ ደህና መሥራቱ ይገለጥለት:: ሁለተኛ የኛን መሪ ሀሳብ ተከትሎ በከፍተኛ ኃላፊነት እንዲሠራ ከዚህ ቀደም ተነግሮታል:: አሁንም በጽሑፍ ይጨመርለት ከተባለ ይሁን:: ሶስተኛ የውጭ አገር አምባሳደሮች ግን ከልዩ ጸሐፊያችን ጋር በቀጥታ መነጋገር የለባችሁም:: ጉዳያችሁን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ብቻ አቅርቡ ብሎ በአንድ ጊዜ በሩን መዝጋት አይሆንም:: በፊቱኑ ባልተዠመረ ነበር:: ሲሠራበት የቆየውን ልማድ በአንድ ጊዜ ማቋረጡ ምን ተፈጠረ ? ያሰኛል:: ሀሳቡ ሳይወድቅ ጥቅምና ጉዳቱ በዝርዝር ተጠንቶ ወደፊት ቀርቦልን እንመለከተዋለን ...... »

ይህ ከንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠው መሪ ቃል ወልደጊዮርጊስን አስደስቷል:: የአክሊሉ ሀብተወልድን ሥራ ለማደናቀፍ የተሞከረውን ተንኮል አክሽፈው፣ ጃንሆይ ለኒውዮርኩ መላክተኛቸው የሠራኸው መልካም ነው የሚል ቴሌግራም እንዲልኩ አስደረጉ:: ሁለተኛ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ለሚያደርጉት ትግል ነፃ መንፈስ ይዘው ለመሥራት እንዲችሉ የተሰየ ሥልጣን እንዲሰጣቸው ያቀረቡትን ሀሳብ ንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃዳቸው ሆኗል:: ሶስተኛ በአቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ አሠራር ለማሾፍና ስሜታቸውን በውስጠ ወይራ አነጋገር ለመግለጽ መልካም አጋጣሚ አገኙ:: ሁኔታውም ስለአደፋፈራቸው ለወደፊቱ የውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎች ለጃንሆይ የሚያቀርቡት ማናቸውም ኮሬስፖንዳንስ በልዩ ጸሐፊው በአቶ ተፈራወርቅ በኩል መሆኑ ቀርቶ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኩል እንዲሆን የንጉሠ ነገሥቱን ውሳኔ ጠየቁ:: ጸሐፌ ትዕዛዝ፣ የግርማዊነታቸው ልዩ ጽሕፈት ቤት የሚባለውን ቢሮና አቶ ተፈራወርቅን በቀጥታ ለመቆጣጠር ባለመቻላቸው ቁሬታ ሲሰማቸው ይኖር ነበር:: ወልደጊዮርጊስ ተፈራወርቅን በቀጥታ ባይቆጣጠሩም በዚህ በልዩ ጽሕፈት ቤት የሚከናወነው ጉዳይ አያመልጣቸውም:: በየቦታው ሰው ስለአላቸው ሁሉንም አስቀድመው ይሰሙታል ወይም ይደርሱበታል:: ከውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎች ጋር ላለው ግንኙነት ኃላፊነቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲሆን፣ አቶ ተፈራወርቅ ጣልቃ ገብተው የጃንሆይን ኮሬስፖንዳንሶችና የአምባሳደሮቹን የሹመት ደብዳቤ አቀራረብ ፕሮቶኮል መያዛቸው፣ የልዩ ጸሐፊነት ተግባር አለመሆኑን፣ ቀደም ሲል ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበሩ ጊዜ፣ ቀጥሎም አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ተችተውበታል:: ግርማዊነትዎ የሚደክምላት ኢትዮጵያ

የሠለጠነው ዓለም ከሚከተለው የአሠራር ሥርዓት የተለየች መሆን የለባትም በሚል ማግባቢያ፤ ከውጭ አገር መንግሥታት አምባሳደሮች ጋር የሚደረገው ግንኙነት ሁሉ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል እንዲፈጸም ወልደጊዮርጊስ ያቀረቡት ሀሳብ፣ አቶ ተፈራወርቅንና ቢሮአቸውን ያስአንጻች ሥራ የሚያስቀራቸው መሆኑን ለመረዳት አስቸጋሪ አልነበረም:: በኢትዮጵያ ሲሠራበት በቆየው ልማድ የልዩ ጸሐፊነትን ተግባር በሙሉ የሚያከናውነው የጽሕፈት ሚኒስትሩ ነው:: በአገሩ ጠቅላላ ጉዳይ የጃንሆይን መሪ ቃል የሚመዘግበውንና ትዕዛዙን ለየአስፈላጊው የሥራ ዘርፍ የሚያስተላልፈው ጸሐፊ ትዕዛዙ ወይም ረዳቱ ነው:: አሠራሩ በዚህ መልክ እስከቀጠለ ድረስ የአቶ ተፈራወርቅ ልዩ ጸሐፊነት ለምን እንዳስፈለገ አይታወቅም እየተባለ ሲተች የቆየ ጉዳይ ነው::

ጃንሆይ ከጸሐፊ ትዕዛዛቸው የቀረበላቸው ሀሳብ ምንም እንኳ በመሠረቱ ትክክል መሆኑን ቢረዱትም፤ የወልደጊዮርጊስ ጥበብ ተፈራወርቅን ጨፍልቆ ከታ ለማሳጣት ሳይሆን አይቀርም ብለው ስለጠረጠሩ፣ የጽሕፈት ሚኒስትራቸው ቅር እንዳይላቸው፣ ልዩ ጸሐፊያቸውም በድንጋጤ እንዳይወድቁ፤ ሀሳቡ በዝርዝር ተጠንቶ ወደፊት ይቅረብልን በሚል መምሪያ ጉዳዩን ለጊዜው አቆዩት::

# በኒውዮርክ፣ ያልተጠበቀ ደስታ

ቅዳሜ ሚያዝያ 16 ቀን 1949 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በአሥር ሰዓት፣ ከንጉሠ ነገሥቱ፣ ለአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የተላከው ቴሌግራም ደረሰ::

ጉዳዩ እንደሚታወሰው፣ ከአሥር ቀናት በፊት የእንግሊዙ መልዕክተኛ ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ ያቀረበውን ሀሳብ በመቃወም፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ስለሰጡት መልስ ነው:: አቶ አክሊሉ የወረወሩት ቃል እንግሊዞችን እንደአስቆጣ ስለሚያውቁ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ይደርሰኛል ብለው የሚጠብቁት ቴሌግራም « ሽረት » ወይም «ግሳፄ » ከሁለት አንዱ ሊሆን ይችላል ብለው ነው::

ነገሩ ተአምር ሆነ:: የተጠበቀው ቴሌግራም ሲደርስ የሚገልጸው፣ ሽረትም፣ ግሳፄም አይደለም « የሠራኸው ማስፈያ ነው» በሚል ቃል ብቻ የተወሰነም አይደለም:: አድናቆትንና ተጨማሪ ሥልጣንን የሚያጐናጽፍ ሆኖ ሲገኝ፣ ለጊዜው አቶ አክሊሉ ማመን አቃታቸው:: ከጃንሆይ የተላከውን ከድ የፈታውን ዲፕሎማት ጠርተው፣ የቁጥር ቃሉ በትክክል ነው ወይ የተፈታው ? ብለው እስከመጠየቅ ደረሱ:: ኮዱ በትክክል መፈታቱንና የተጨመረም የተፈጠረም ቃል አለመኖሩ ተነገራቸው::

ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ከጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስና ከወንድማቸው ከአቶ መኰንን ሀብተወልድ ላቶ አክሊሉ የደረሱት መልዕክቶች የሚከተሉት ናቸው::

## ከግርማዊ ጃንሆይ

*ይድረስ ላቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣*

*እንደምን ሰንብተሃል:: እኛ በእግዚአብሔር ቸርነት ደህና ነን::*

*ስለ ሱማሌና ስለ ኤርትራ ጉዳይ ከእንግሊዝ ዋና መላክተኛ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የቀረበውን ሀሳብና አንተም የሰጠኸውን ምላሽ ፍሬ ነገሩን አየነው::*

*ከዚህ ቀደም የሰጠንህን መሪ ቃል ተከትለህ ከሀሳባችን ጋር የሚስማማ ንግግር በማድረግህና ጠንከር ብለህ በማስረዳትህ፣ ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠርተሃል:: የተባበሩት መንግሥታት አባሎች፣ የሚያደርጉትን ዲስኩሮችና የሚያቀርቡትን ሀሳቦች በጥንቃቄ ማዳመጥና ማመዛዘን ብቻ ሳይሆን፣ በቶሎ ምላሽ መስጠትም አስፈላጊ መሆኑ የታወቀ ነው:: አንተም በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በሚፈጠረው ሁኔታ የኛን መምሪያና ፈቃድ ለማግኘት በመገናኛ በኩል ያለብህን ከፍተኛ ችግር ስለተረዳነው፣ ከዚህ ቀደም የሰጠንህን መምሪያ ትእዛዝ መሠረቱን ጨብጠህ፣ ለዝርዝሩ የሥራ አፈጻጸም ጠቃሚ የመሰለህን ሁሉ እዚያው እየወሰንክ እንድትሠራ ፈቅደን ተጨማሪ ኃላፊነት ሰጥተንሃል:: ......*

*በኤርትራ ዋና ጉዳዮችን የኛ ሀሳብ አገሩ ሳይከፈል እስላም ክርስቲያን ሳይባል በሙሉ ወደ እኛ እንዲሆን ነው:: አንተም ይህንኑ ሀሳባችንን የዓለም መንግሥታት እንደራሴዎች በትክክል እንዲገነዘቡት የምታደርገው ጥረት የተገባ ነው:: ሆኖም የተባበሩት መንግሥታቶች፤ በተለይ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የቀረበላቸውን ሀሳብ ለማጽደቅ የሚያመዝኑ ሆኖ ስታገኘው፣ ሌላ አደናቃፊ ሀሳብ ሳይፈጠር፣ በእኛ ዘንድ ቅሬታ መኖሩን በሚያሣይ አኳኋን የለሰለሰ ንግግር አድርገህ፣ መቀበላችንን ትገልጣለህ:: በተለይ በሱማሌ ጉዳይ ግን፣ ጣልያን ተመልሳ እንድትገዛ ከታላቋ ብሪታንያ የቀረበው ሀሳብ፣ እኛን በጣም የሚጎዳን መሆኑን ለዓለም ጉባኤ እያስረዳህ በምትሟገትበት ጊዜ፣ እንግሊዞችን፣ እኛም መንግሥታችንም በፍቅር ዓይን የምናያቸው መሆኑን እንዲያውቁት አድርግ:: የሰጠ ንህ ኃላፊነትና የጣልንብህ አደራ ከፍተኛ ስለሆነ፣ ፈቃዳችንን ለመፈጸም በምታደርገው ጥረት እግዚአብሔር አይለይህ::*

አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፤ ይህ አስደሳች የሆነው የጃንሆይ ቴሌግራም ከደረሳቸው ከጥቂት ቀናቶች በኋላ፤ ከጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስና፤ ከወንድማቸው ከአቶ መኰንን ሀብተወልድ በግሊዝ ዲፕሎማቲክ የደረሳቸው ደብዳቤዎች፤ ስለ ሥራቸው የተለያዩ ምክሮችና ግብረታቻዎች የሚሰጡ ሆነው አገኟቸው::

## ከጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ፤

*« ...... ያለብህን ከፍተኛ ድካም እንደጉርፍ በሚወርድልን ቴሌግራምህ እያየሁ አደንቃለሁ:: አንተም የጀመርከውን ካልጨረስክ የማታርፍ መሆንህን ስለማውቅ ብርታቱን እንዲሰጥህ እመኝልሃለሁ::*

መቸም እነዚህ ወዳጆቻችን እንግሊዞች፣ እኔን ከጽሕፈት ሚኒስቴር፣ አንተን ከውጭ ጉዳይ ካላስነቀሉን፣ ሠላም አያገኙም። እኔና አንተም ከእነሱ ተንኮል ካልተገላገልን የሠላም እንቅልፍ እንደሌለን የታወቀ ነው። በሊክስክሌስ (ኒውዮርክ) የእንግሊዙ ዋና መልዕክተኛ ሱማሌ ተመልሳ በጣልያን እንድትገዛ የተጠየቁት መንግሥታትን ሲጠይቅ፣ ወዲያውኑ ተነስተህ የሰጠኸውን መልስ አይቼ በጣም ደስ አለኝ። ያስተላለፍከው ሰፊ መልዕክት ከቀቀር ቃሉ ተፈትቶ፣ ያንተ ሀሳብ ለእኛ በሚስማማ መልክ እስኪስተካከል ድረስ፣ የተለመደው የእንግሊዞቹ ስምታ በጓዳ በር በኩል ቀርቦ ነበር። እኛም ያንተ መልዕክት ተቀጥና በቶሎ እንዲቀርብ ስለአደረግን አልተቀደምንም። ለእኔም በላከልኝ ዝርዝር መሠረት የሠራኸው ሁሉ የተሰጠህን መምሪያ ተከትለህ መሆኑን፣ በረኸሙ ለጌቶቹ አስረድቼ የምሥጋና እና የማበረታቻ መልዕክት ልከውልሃል። እጌቶቹ ዘንድ እኔና የወዳጆቻችን ባለሟል ያደረግነውን ክርክርም ሆነ የሀሳብ መለዋወጥ፣ አቶ ገብረወልድ እንግዳወርቅ ደህና አድርጉ ፕሮሴቨርባል ስለአዘጋጀ፤ ኮፒው በቶሎ እንዲደርስህ አደርጌያለሁ። አቶ ገብረወልድ በያዘው ማስታወሻ ፍሬ ነገሩን በሚገባ ለቅም ያሰፈረ ስለሆነ ረጋ ብለህ ተመልከተው። ለዛሬውና ለወደፊቱ ኢክስፔሪያንስ ይረዳሃል። ከጃንሆይ በተላከልህ መልዕክት የተለየ ሥልጣን ስለተሰጠህ፣ ሳትጨነቅ እንደመሰለህ መሥራት ነው። በዚያ ቦታ ላይ ለአገራችን ጠቃሚ የሚሆነውን ሁሉ ካንተ የተሻለ የሚያውቅ ስለሌለ አእምሮህ ነፃ ሆኖ እንዲያስብ አስፈላጊ ነው። እንግዲህ ከየጥቃቅኑ ጉዳይ እኛን በማስፈቀድና በማማከር የምታጠፋው ጊዜ ተቀንሶልሃል ቢባልም፣ በየጊዜው የተሠራውን ሁሉ የሚገልጸው ራፖርህ መድከም የለበትም። ይኸንን ወተሩ አማርኛ ሀሳብህን የሚያዘጋጅልህና የሚከታተልልህ አንድ ሰው ስለሚያስፈልግህ፣ ከዚህ ቀደም ምርጫህን ጠይቁህ እምሩ ዘለቀ አብሮኝ ስለአለ፣ ይበቃኛል ማለትህ ትዝ ይለኛል። በኔ ግምት ለብዙ ጉዳይ ሊረዳህ የሚችለው፤ ዘውዴ ገብረሕይወት ነበር። እሱ ደግሞ እዚህ ያንተ ሊየዞን ሆኖ የያዘው ቀንበር ብዙ ነው። የሆነ ሆኖ ምርጫው ያንተ ስለሆነ በፍቱ ንገረኝና በተጨማሪ ሰው ከቦሬሊያው ልላክልህ። ከብላታ ኤፍሬም ጋር በመግባባትና በመተባበር መሥራታችሁን ጌቶቹ ሰምተው ደስ ብሏቸዋል። መቸም ሁለት ዲፕሎማቶች ቢግባቡ ሥራው መልካም እንደሚሆን የታወቀ ነው። እንግዲህ ያለብህ ሥራና ጣጣ ብዙ ስለሆነ በወረቀት ላደክምህ አልፈልግም። አንተ እዚያ በርታ እኔ እዚህ እታገልልሀለሁ ......... »

ያንተው ወልደጊዮርጊስ

## ካቶ መኰንን ሀብተወልድ የተላከ፤

« ...... እዚህ አንተ እንደሰጋህበት የሚሆን ነገር የለም። ለሱማሌ ጉዳይ ለዓለም ጉባኤ የተናገርከው የጃንሆይን ሀሳብ ተከትለህ መሆኑን ጸሐፌ ትእዛዝ በሰፊው አስረድቶልሀል። የእንግሊዝ አምባሳደር ላቶ ተፈራወርቅ የላከው ማስታወሻ የመንግሥት አቤቱታ ሆኖ ለጃንሆይ በወግ ስላልቀረበ፣ ነገሩ በዝምታ እንዲታለፍ ተደርጓል። የአምባሳደሩ አደራረግ ግን በመንግሥቱ ስም ሳይሆን በራሱ የተንኮል ዘዴ መሆኑን ጃንሆይ ደርሰውበታል። ለወደፊቱም ሥራህ ጸሐፌ ትእዛዝ ችግርህን ለጃንሆይ አስረድቶ፣ ለአገር የሚጠቅመውን ሁሉ እዚያው እያሰብክ እንድትወስን የተለየ ኃላፊነትና አደራ ተሰጥቶሃል። ኃላፊነት ተጨመረ ሲባል ያው እንደምታውቀው የጃንሆይን መምሪያ ተከትሎ ሥራውን ለማፋጠን እንዲቻል ማለት ነው።

እኔ አንድ የሚያሳስበኝ ነገር አለ። ከማንም ጋር አልተወያየሁበትም። ታላላቅ ከተባሉት አገሮች ከእንግሊዝና ከአሜሪካን ጋር ደህና ግንኙነት ከሌለህ ሥራህ እንዴት ሊቃናልህ ይችላል ? እያልኩ እጨነቃለሁ። መቸም በዚህ ዓለም እንዳየኸው፣ ፍርድ የሚሰጠው በትልልቆቹ ነው እንጂ፣ የትንንሾች ሀሳብ የሚደመጥበት ጊዜ ገና አልመጣም። አንተም በዓለም ማህበር ጉባኤ ለኢትዮጵያ ፍርድ ለማስገኘት የትላላቆቹ እርዳታ ከሌለህ እንዴት ይሆናል ?.... ከትላላቆቹ ውስጥ ያው እንደምታውቀው፣ ከሞስኮብ ጋር የጥንቱ ታሪካችንና ሀይማኖታችን ቢመሳሰልም፣ ዛሬ በሀሳብም በአሠራርም አንጣጣምም። እነሱም

እኛን አይወዱንም:: እኛም የእነሱን ሞዴል አንፈልገውም:: ወደፊት የሚፈጠረው አይታወቅም:: እነሱም ባመኑበት እኛም በቆምንበት ሆነን በኢኮኖሚም በንግድም አብረን ለመሥራት እንችል ይሆናል:: እስከዚያው ድረስ ግን እነሱ እኛን እንዲረዱን፣ እኛም የእነሱን ድጋፍ እንድንጠይቅ፤ የሚቻል አልመሰለኝም:: ስለ ፈረንሣዮችም አሰብኩበት:: ባለፈው ታሪካችን እንዳየናቸው በቃላቸው የሚረጉ አይደሉም:: ዛሬም ለኛ ደህና ነገር ያስባሉ ማለት አይቻልም:: የዛሬውን ሁኔታቸውን ስመለከተው፣ እነሱም እንደ እኛ አጋር ፈላጊዎች ይመስሉኛል:: ይህን ሁሉ ካሰብኩ በኋላ፣ ያው ዞሮ ዞሮ ምንም ቢተናኮሉን እንግሊዞች፣ ከእነሱም በላይ አሜሪካኖች የሚያስፈልጉን ናቸው:: በተለይም አሜሪካ ዋና ነገር ነው እላለሁ:: የዲፕሎማቲክ ሥራ የዛሬውንና የወደፊቱን አርቆ እየተመለከተ ግምት የሚሰጥ ነው ሲባል እሰማለሁ:: ስለዚህ፤ ለኢትዮጵያ ለአጭር ጊዜ የሚጠቅመውንና ለሩቅ ጊዜ የሚጎዳውን አንተ ታውቃለህ ብዬ አልፈዋለሁ:: ያለኸው በጦር ሜዳ ላይ እንደሚዋጋ ወታደር ዓይነት ነው:: ማሸነፍም መሸነፍም እንዳለ ታውቃለህ:: የምታሸንፈው በአጋር ብዛት የምትሸነፈው በጠላት ኃይል ይሆናል ካልክ፣ ጃንሆይ የጣሉብህ ኃላፊነትና አደራ እንዲቃናልህ፤ ከኃያላኖቹ ከአሜሪካኖችና ከእንግሊዞች ጋር ባትቃቃር ይሻላል::

...... ጓደኞችህ ይልማ ዴሬሳና መኩንን ደስታ እኔ ዘንድ መጥተው አክሊሉ የእንግሊዙን መላከተኛ ደህና አድርጐ ስለአስታጠቀው፣ ደስ ብሎናል አሉኝ:: እኔም የመጠ በት እኳኋን ስላልጣመኝ፣ እንደሰማችሁት አክሊሉ የተወቀሰው በንግግሩ ያንድን ትልቅ አገር ወኪል ዘልፏል ተብሎ ነው:: መቸም ዘለፋ የጅግኖች መለኪያ አይደለም:: ለጊዜው መደሰትም ማዘንም አያሻም ብዬ መለስኳቸው:: ለማናቸውም ስለ አሠራሩ የበለጠ የምታውቀውና ኃላፊው አንተ ነህ:: ጥቃትና መከራ ስትቀበል የኖረች አገራችን የሚገባትን ፍርድ እንድታስገኝላት እግዚአብሔር ይርዳህ ...... »

በሠላም ይገጠመን
ያንተው መኩንን ሀብተወልድ

# አቶ አክሊሉ ..... የትኛውን ይከተሉ?

ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት፣ ከጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ የጽሕፈትና ያገር ግዛት ሚኒስትር፣ ካቶ መኮንን ሀብተወልድ የርሻ፣ የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስትር፣ የተላኩት መልዕክቶች በጠቅላላው ላቶ አክሊሉ ከፍ ያለ የሞራል እርዳታ ያበረከቱ ቢሆኑም፤ ከሶስቱም የተገለጹት ሀሳቦች እያንዳንዳቸው የተለያዩ ትርጉሞች አሏቸው::

የጃንሆይ መልዕክት በሶስት ነጥቦች ላይ ያተኮረ ነው:: የመጀመሪያው፣ « ያደረግከው ዲስኩር ከሀሳባችን ጋር የሚስማማ ስለሆነ ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠርተሃል » የሚለው ምሥጋና ነው:: ሁለተኛው፣ «በጉባኤው ላይ ለሚፈጠረው ዝርዝር ጉዳይ የኛን መልካም ፈቃድ ለማግኘት ስትጠብቅ ጊዜው እንዳያልፍብህ ዋና መምሪያችንን መሠረት ይዘህ ጠቃሚ የመሰለህን እዚያው እየወሰንክ ሥራበት» በማለት የተሰጠውን የተለየ ሥልጣን የሚገልጸው ነው:: ሶስተኛው ነጥብ ግን ልዩ መልዕክት አለው:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ምንም እንኳን እንግሊዞች ብዙ ያሳዘኗቸው እና የሚያደርጉትንም ተንኮል ደህና አድርገው ቢያውቁም፣ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ጋር ያላቸው ግንኙነት በዓለም አደባባይ ላይ የሻከረ ሆኖ እንዲታይ አይፈልጉም:: ማናቸውም ጉዳይ መከናወን ያለበት በመጋተር ሳይሆን በሠላምና በወዳጅነት መንፈስ እንዲሆን ጽኑ እምነት አላቸው:: በዚህ መሠረት አቶ አክሊሉ እንዲገነዘቡት ለማድረግ በገለጹት ቃል « ...... በተለይ በሱማሌ ጉዳይ ጣልያን ተመልሳ እንድትገዛ ከቃል ኪዳን ወዳጆችን ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት

የቀረበው ሀሳብ እኛን የሚጐዳን መሆኑን ለዓለም ጉባኤ በምታስረዳበት ጊዜ፣ እንግሊዞችን እኛም፣ መንግሥታችንም፣ በፍቅር ዓይን የምንመለከታቸው መሆኑን በሚገባ እንዲያውቁት አድርግ ..... » ብለዋል:: ይህ የንጉሡ ነገሥቱ ቃል በሌላ አነጋገር ሲተረጐም፣ ባለፈው ጊዜ በጠነከረ ቃል በማስረዳትህ ማለፊያ ስርተሃል ብንልህም፣ ለወደፊቱ ከታላቋ ብሪታንያ ዋና መልዕክተኛ ጋር የምትለዋወጠውን ሀሳብ፣ መቃወምም ቢያስፈልግ አነጋገርህን በወዳጅነት መንፈስ ማለስለስ አለብህ ማለት ነው::

እንግሊዞች ላይ ብዙ ቅያሜ ያላቸው ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ የላኩት መልዕክት፣ አቶ አክሊሉ ያደረጉትን ንግግር በማድነቅ ወደፊትም በዚሁ መንፈስ እንዲቀጥሉ የሚያተጋ መሆኑ ግልጽ ነው:: እንደ ጃንሆይ፤ እንግሊዞች ምንም የሚጐዳ ሀሳብ ቢሰንዝሩብን በፍቅር ዓይን የምንመለከታቸው መሆኑን በሚገባ እንዲያውቁት አድርግ አይሉም:: እንደ መኰንን ሀብተወልድ፣ ምንም ቢተናኰሉን ከእንግሊዞች ጋር መቃቃር ይጐዳናል ብለው አይሰጉም::« ...... እነዚህ እንግሊዞች እኔን ከጽሕፈት ሚኒስቴር፣ አንተን ከውጭ ጉዳይ ካላስነቀሉ ሠላም አያገኙም:: እኔና አንተም ከእንግሊዞች ተንኮል ካልተገላገልን እንቅልፍ የለንም ..... » ካሉ በኋላ፤ ወልደጊዮርጊስ ለሀሳባቸው መዝጊያ ያደረጉት <u>አንተ እዚያ በርታ እኔ እዚህ</u> አለሁልህ ብለው ነው::

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት፣ በተለይም በዚያ በ1949 ዓ.ም በነበረው መንፈስ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንግሊዞችን በዲስኩሩ አስቀየመ ሲባል፣ ንጉሣዊ ቤተሰቡን በሙሉ ጭንቀትና ሀሳብ ላይ ሊጥል ስለሚችል፣ ወልደጊዮርጊስ ባላቸው ኃይልና ዘዴ ነገሩን በማቃለል ሠላም እንዲሰፍን አድርገዋል:: በጓዳ በር የቀረበው ተንኰል ከአምሣለ ገነት ቢሮ ሳይወጣ፣ በጃንሆይ ተመርምሮ በጃንሆይ ብቻ እንዲወሰን፤ ውሳኔውም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ሥልጣን የሚጨምርና ሞራልን ከፍ የሚያደርግ እንዲሆን፤ ወልደጊዮርጊስ ያደረጉትን ጥረት፤ አክሊሉ ሀብተወልድ በሕይወታቸው ዘመን አልዘነጉትም::

ወልደጊዮርጊስ፤ በሚወዱ ጊዜ ለፍቅራቸው ወሰን፣ ሲቀየሙ ደግሞ ለጠ ባቸው ገደብ ስለሌለው፣ አክሊሉ ሀብተወልድ በዚያን ጊዜ የጸሐፊ ትእዛዙ ተወዳጅ መሆናቸው ለሥራቸው በጣም ረድቷቸዋል::

እንደ አባት ያሳደጓቸው ወንድማቸው መኰንን ሀብተወልድ የገለጹት ሀሳብ፣ ከወልደጊዮርጊስ ይልቅ ወደ ጃንሆይ የሚቃረብ ነበር:: የሠራኸው ወይም ያደረግከው ንግግር የሚያስደስት..... የሚያስደንቅ.... ነው ለማለት ጨርሶ አልፈለጉም:: በጀመርከው አኳኋን መበርታትና መቀጠል ነው ብለው ለማትጋትም አልሞከሩም:: እሳቸው የተጨነቁት፣ አቶ አክሊሉ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ጋር ከተቃቃሩ፣ ጃንሆይ ከፍ ያለ አደራ የጣሉባቸው የኤርትራ ጉዳይ ይበላሻል ብለው ነው:: ስለዚሁ ጉዳይ ለወንድማቸው ሀሳባቸውን ሲገልጹ « ...... በዚህ ዓለም እንዳየኸው ፍርድ የሚሰጠው በታላላቆቹ ነው እንጂ፣ የትናንሾች ሀሳብ የሚደመጥበት ጊዜ ገና አልመጣም ...... እንተም በዓለም ማህበር ጉባኤ፣ ለኢትዮጵያ ፍርድ ለማስገኘት የትላልቆቹ እርዳታ (የእንግሊዝና የአሜሪካ) ከሌለህ እንዴት ይሆናል ? ..... » የሚል ጥያቄ አቅርበዋል:: መስከቦች አይወዱንም:: ፈረንሣይን ማመን አይቻልም:: ካሉ በኋላ፤ « ...... ያው ዞሮ ዞሮ ምንም ቢተናኰሉን እንግሊዞች፣ ከእነሱም በላይ አሜሪካኖች የሚያስፈልጉን ናቸው::

ስለዚህ፣ ለኢትዮጵያ ላጭር ጊዜ የሚጠቅመውንና ለሩቅ ጊዜ የሚጐዳውን አንተ ታውቃለህ ብዬ አልፈዋለሁ ....፡ » ብለዋል። በዚህ አኳኋን ጠቅላላው ሁኔታ ሲታይ፣ የንጉሠ ነገሥቱና የወንድማቸው የመኰንን ሀብተወልድ መልዕክት ለወደፊቱ ከእንግሊዞች ጋር በቀጥታ መኳታረኩ አይበጅም በሚል ማስጠንቀቂያ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ የወልደጊዮርጊስ ሀሳብ ግን በጀመርከው ጠንክረህ ግፋበት የሚል ነው።

አቶ አክሊሉ እንግሊዞችን በቀጥታ ካልተቋቋምናቸው ምንጊዜም ሠላም አይሰጡንም ብለው ያምናሉ። « ..... ኢትዮጵያ ከፋሽስት አገዛዝ ከተላቀቀችበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ ለአራት ዓመታት እንግሊዞች በቅኝ አስተዳደር መልክ በአገራችን ላይ ሥልጣናቸውን ዘርግተው፣ በንጉሠ ነገሥቱና በሚኒስትሮቻቸው ላይ ይፈጽሙት የነበረውን ግፍ፣ ምንጊዜም ለመርሣት አይቻልም። ዛሬም በ 1949 ዓ.ም ሙሉ ነፃነት አለን በምንልበት ዘመን፣ አገራችንን በሚመለከት ጉዳይ እየገቡ በሚተበትቡት ተንኮል፣ ሠላም አላገኘንም። ኤርትራ ተከፍሎ ግማሹ ከኢትዮጵያ ጋር ይሁን የሚሉት፣ የምዕራቡን አውራጃ ከሱዳን ጋር አቀላቅለው የቅኝ ግዛታቸውን ለማስፋፋት እንዲመቻቸው ነው። ጣልያን ተመልሳ ሱማሌን ታስተዳድር የሚሉት፣ በዚህ አጋጣሚ በኢትዮጵያና በጣልያን መካከል ጦርነት እንዳይነሳ ጠረፉን እንጠብቃለን በሚል ሰበብ <u>ኦጋዴንን ይዘው ለመቆየት ስለሚመኙ ነው።</u>

...... እስከ ዛሬ ድረስ ሲመቻቸው በራሳቸው መንገድ ሲጨቁኑን፣ ሳይመቻቸው ደግሞ በውጭ ጠላት ሲያስጠቁን ኖረዋል። በኤርትራ ጉዳይ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ጣልያኖችን አደፋፍረውና ረድተው ምፅዋን እንዲይዙ ያደረጉት እንግሊዞች መሆናቸው የሚዘነጋ አይደለም። ስለዚህ እንግሊዞች ባለፉት ዘመናት ከፈጸሙብን በደል የበለጠ ዛሬ ምን ሊያደርሱብን ይችላሉ ? ይልቅስ እኛ ከበረታንና ከቆረጥን፣ የእንግሊዞች ግፍ ከደረሰባቸውና መራራ ሕይወት ከቀመሱት እንደ ሕንድ ከመሳሰሉት አገሮች ጋር ተሰልፈን በየኢንተርናሽናል ጉባኤዎች ላይ እያጠመድን ብናወግዛቸው፣ ቁጭታችንን እንወጣ ነበር። እነሱም ሲያስፈልግ ደካሞች አለመሆናችንን ተረድተው፣ ሳይወዱ በግድ ያከብሩን ነበር። በተለይ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ከእንግሊዞች የሚቀርቡት ሀሳቦች ሁሉ በተንኮል የተመረዙና የሚጐዱን ስለሆኑ፣ መቃወማችንን መግለጽ ያለብን በጠነከረ ቃል ነው እንጂ፣ ጃንሆይ እንደሚፈልጉት በወዳጅነት በማለስለስ መሆን የለበትም። እንደዚህ ካደረግን በቀጥታ እነጋገር መለማመጥ ማለት ነው። ባለፉት ስምንት ዓመታት እንግሊዞችን ደህና አድርገን አውቀናቸዋል። ትዕግሥታችንን ደካማነት፣ ትህትናችንን በታዛዥነት እየተረጐሙ፣ ሲጨቁኑን የነበረው ዘመን ዛሬ አልቋል። ስለዚህ በዓለም ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ በነፃነቷ አምና፣ በድህነቷ ሳታፍር እንገቷን አቅንታ እንግሊዞችን ስትቋቋም መታየት፣ ለብዙ ታናናሽ አገሮች ትልቅ ሞራል ይሰጣል። ኢትዮጵያንም ያስከብራል። ...... »

በዚህ አቋም አቶ አክሊሉ ቢገፉበት ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ያለ እንዳች ማመንታት እንደሚቆሙላቸው ያውቃሉ። ሆኖም በሌላ መንገድ ደግሞ ከንጉሠ ነገሥቱ የተሰጣቸውን መምሪያና ከወንድማቸው የተላከላቸውን ምክርና ማስጠንቀቂያ ችላ ማለት አይችሉም። በመሠረቱ፣ ጃንሆይ የሚፈልጉትና አቶ መኰንን የሚደግፉት ሀሳብ ምን እንደሆነ አቶ አክሊሉ የተብራራላቸው በዚህ መልክ ነበር። « ...... በዓለም መንግሥታት ማህበር ጉባኤ ላይ ከእንግሊዞች ጋር በከረረ ቃል መጋተሩ የሚጐዳን እንጂ የሚጠቅመን አይደለም። ባለንበት ሰዓት

ከእንግሊዞች ጋር ለመጣላት የሚያስችል አቅም እንደሌለን ማወቅ አለብን:: ጠረፎቻችን የተከበቡት በእንግሊዝ ጦር ነው:: በመንግሥታችንም አስተዳደር ውስጥ አንዳንድ ቁልፍ የሆኑት ቦታዎች፣ እንደ ፍርድ፣ እንደ ጦር ሠራዊትና ፖሊስ የመሳሰሉት ገና አልተለቀቁልንም:: በኤርትራም ሆነ በሱማሌ ጉዳይ፣ እንግሊዞች ከጠመሙ የምንፈልገውን አናገኝም:: እንግሊዞችን ስንዳፈር ደግሞ አሜሪካኖች እኛን ደግፈው ይቆሙልናል ብለን ማለም አንችልም:: ስለዚህ ከእነሱ ጋር የምናደርገው ንግግር ሳንወድ በግድ፣ በለሰለሰና በወዳጅነት መንፈስ ከመሆን በስተቀር ሌላ ምርጫ የለንም:: ..... » የጃንሆይ ሀሳብ በዚህ አኳኋን ሲተረጉም፣ መኩንን ሀብተወልድ ደግሞ በበኩላቸው የሚጨምሩት አስተያየት « ..... ኤርትራ እጃችን ገብቶ፣ የባሕር በር ተከፍቶልን፣ ሥልጣኔና እድገት ለሕዝባችን ተስፋፍቶ፣ የአገራችን አቅምና ሀብት በቂ ሆኖ፣ እንግሊዞችን የምንቋቋምበት ጊዜ እንደሚመጣ አንጠራጠርም:: ነገር ግን የዛሬውን ችግራችንን በዛሬው አቅማችን መለካት ስለአለብን ነገ ማድረግ የምንችለውን ዛሬ ካልሆነ ብለን፣ የባሰ መከራ ላይ እንዳንወድቅ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ...... » የሚል ነው::

እንግዲህ፣ አቶ አክሊሉ የትኛውን ይከተሉ ? ..... በወልደጊዮርጊስ ድጋፍ ተመክተው ቢጓዙ፣ እንኳንስ ንጉሠ ነገሥቱ ወንድማቸው መኩንን ሀብተወልድም ይቅርታ አያደርጉላቸውም:: ደግሞም የአባ ጠቅልን ትእዛዝ ተጋፍቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ለመቆየት እንዴት ይቻላል ? በሌላ በኩል « እኔ አለሁልህ በርታ » ብለው ከፍተኛ ማበረታቻ የሰጧቸውን የወልደጊዮርጊስን ምክር ችላ ለማለት ይቸገራሉ:: ይህን ሁሉ በጥልቀት ካጠኑ በኋላ፣ ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች መካከል፣ በዕድሜና በኤክስፔሪያንስ ላቅ ካሉት ከክቡር አቶ ተስፋዬ ተገኝ በፓሪስ የንጉሠ ነገሥቱ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ጋር አቶ አክሊሉ ከተመካከሩ በኋላ፣

1ኛ/ ከእንግዲህ ወዲህ የእንግሊዙ መልዕክተኛ በሚያቀርበው ሀሳብ ኢትዮጵያ መቃወም ካስፈለጋት፣ መልሱን የሚሰጡት በአቶ አክሊሉ ፋንታ ምክትሉ የመልዕክተኞች መሪ ብላታ ኤፍሬም እንዲሆኑ፣

2ኛ/ መልስ መስጠት አስፈልጎ፣ ብላታ ኤፍሬም በኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ወንበር ላይ ሲተኩ፣ አቶ አክሊሉ ከስብሰባው አዳራሽ እንዲወጡ ቢደረግ፣ የተሻለ ዘዴ ይሆናል ተባለ::

ከእንግሊዞች ጠብ ለመሸሽ ይህ የአቶ ተስፋዬ ዘዴ ጠቃሚ ነው በማለት፣ አቶ አክሊሉ የመንፈስ እርካታ ቢያገኙበትም፣ ሱማሌ ለጣልያን ትሰጥ፣ ኤርትራ በሁለት ትከፈል፣ ተብሎ በእንግሎ ሳክሶኖች የቀረበውን ሀሳብ ማስወገድ አልተቻለም:: ይልቁንም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሀሳቡ በስሉ ብዙ ደጋፊዎች ስለአገኘ፣ ኢትዮጵያ መስማማት ብቻ ሳይሆን ለአፈጻጸሙም ብዙ ጥረት እንድታደርግ ግዴታ ሆኖባት ነበር::

# ኢትዮጵያና ጣልያን

የዓለምን ሕግ በመጣስ የመንግሥታት ማህበር አባል የሆነችውን ነፃ ኢትዮጵያ፣ ቅኝ ግዛቷ ለማድረግ በጦር ወግታ በሕዝቧ ላይ ምንጊዜም የማይረሳ አሠቃቂ ግፍ የፈጸመች፣ ከሂትለር ጋር ተሠልፋ ለዓለም ሕዝብ እልቂት የወንጀል ድርሻዋን ያበረከተች፣ ይህች « ጣልያን » የተባለች ፋሽስት የበቀለባት አገር፣

ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ፣ ወንጀለኛ መሪዬን ሙሶሊኒን ቀብሬ፣ ፋሽስት ያለበሰኝን ሸማ አውልቄ፣ የዲሞክራሲን ጥበብ ኩታ ተጐናጽፌ፣ አዲሲቷ ሬፑብሊክ ተብዬ፣ ከደሙ ንፁህ ሆኛለሁ ብላ፣ በዓለም አደባባይ ብቅ ማለቷን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ አልተቀበለችም።

ከዚያ ሁሉ መከራ በኋላ የዓለም ጦርነት አልቆ ሠላም እንደገና ሲገኝ፣ ወንጀለኛዋ ጣልያን በኢትዮጵያና በሌሎችም አገሮች ላይ ላደረሰችው በደል የሚሰጣትን ቅጣትና ውሳኔ አሜን ብላ ከመቀበል በስተቀር፣ ይኸ ቀረብኝ ይኸ ይገባኛል እያለች፣ ለማስቸገር ይፈቅድላታል ተብሎ በኢትዮጵያ በኩል ጨርሶ አልተጠበቀም ነበር። ከሂትለር መደምሰስ በኋላ፣ የጀርመን ሕዝብ አንድነቱን እንዲያጣ፣ ነፃ ሆኖ እንዳይንቀሳቀስና በዓለም ጉዳይ በሚመከርበት አደባባይ ዝር እንዳይል፣ በአራቱ ታላላቅ መንግሥታት ኃይል ተይዞ፣ ያ ሁሉ ከባድ ቅጣት ሲወርድበት፣ ለጣልያን ሙሉ ነፃነት ተሰጥቶ መንግሥት ሆና መቋቋሟን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ማመን አልቻሉም።

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አስተያየት፣ « ..... ሙሶሊኒና ሂትለር ምንም ዓይነት ልዩነት የላቸውም። ሁለቱም እኩል አብዶች እኩል ግፈኞች ናቸው። ሙሶሊኒ ሞተ። ፋሽስት አብሮት ተቀበረ ተብሎ፣ ለጣልያን ሙሉ ነፃነት ከተሰጠ፣ ሂትለር ሲቃጠልና ናዚ ሲጠፋ፣ በጀርመን ሕዝብ ላይ እስከዚህ መጨከን ባላስፈለገ ነበር። የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መነሻ ሂትለር አይደለም። የዓለም ሠላም መናድ የጀመረው በ1935 ዓ.ም፣ ሙሶሊኒ የመንግሥታት ማህበርን ሕግ ጥሶ፣ ነፃ የሆነችውን ኢትዮጵያን በጦር ኃይል ሲወር ነው። በዚያን ጊዜ እንግሊዝና ፈረንሣይ፣ ኢትዮጵያ የሙጥኝ ብላ ስትማጸናቸው በር ከፍተው ከማስጠቃት፣ ነገ በእኔ ብለው በማሰብ ሙሶሊኒን ቢያግዱ ኖሮ፣ ከአራት ዓመት በኋላ ሂትለር ደፍሮ ያንን ሁሉ እልቂትና ያንን ሁሉ አፍዳ አያደርስባቸውም ነበር። ሥላሴዎች ይመሥገኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍርድ እጦት ያፈሰሰው እንባ መሬቱን ብቻ አርጥቦ አልቀረም። በየመልኩና በየደረጃው ሁሉም ብድሩን እንዲያገኝ ፈጣሪ ፈቅዷል። ዛሬም ታላላቅ መንግሥታቶች ካለፈው ሁኔታ ተምረው የወደፊቱን ያሰቡበት አይመስልም። እኛ ግን በእግዚአብሔር ላይ የተረጋገጠ እምነት ስላለን፣ በዘመናችን ይህንን የመሰለ እልቂት እንደገና ይደርሳል ብለን አንሰጋም። ሆኖም ኃያላን መንግሥታት በጀርመን ላይ ጨክነው ጣልያንን ይህን ያህል መረን መልቀቃቸው አሳዝኖናል ..... » ብለው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ይገረሙም ያዝኑም ነበር።

ጃንሆይ በዚህ ጉዳይ ማዘናቸው ትክክል ነው። የኃያላን መንግሥታቶች ዳኝነት በጥቅም ላይ የተመሠረተ ስለሆነ፣ በዓለም ላይ ለደረሰው ዕልቂት የሂትለር ተባባሪ የሆነችው ጣልያን፣ ጦርነቱ ሲፈጸም የፋሽስት ኮቷን ገልብጣ በዓለም ጉባኤ ላይ አስተያየቷን እንድታቀርብ ፈቀዱላት። በዚህ በተሰጣት ዕድል ጣልያን የምትጠቀመው፣ በመጀመሪያ ይህችኑ የፈረደባት ኢትዮጵያን ለማጥቃት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ጣልያን፣ ለኢትዮጵያ ምንጊዜም የማትተኛ ጠላት መሆኗን ባለፉት ታሪኮች ደህና አድርጋ አስመስክራለች። ዛሬም ቀጥላለች።

በ1949 ዓ.ም አዲሲቷ ሬፑብሊክ ተብላ አዲስ የዳቦ ስም የወጣላት ጣልያን፣ ኤርትራ ወደ መሠረተ አገሯ ወደ ኢትዮጵያ እንዳትመለስ በዓለም ላይ የፖለቲካና የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ለማካሄድ ቆርጣ ተነሳች። ይሁን እንጂ በተለያዩ ጊዜያቶች ጠላታችን ጣልያን በአገራችን ላይ የፈጸመችውን ግፍ ለመከላከል፣

በአገር ፍቅር እሣት እየነደዱ ለአገር ነፃነትና ክብር ሲሉ መስዋዕትነትን እንደተቀበሉት ጀግኖች አባቶቻችን፣ በ 1949 ዓ.ም ደግሞ በዓለም ሸንጎና በፖለቲካ ሜዳ ጣልያን የጫረችውን ጦርነት፣ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ልጆች ጽኑ በሆነ መንፈስና በረቀቀ ዘዴ እስከ መጨረሻው ታግለው አሸንፈዋል::

የአዲሲቷ ጣልያን ሬፑብሊክ የአልቺዴ ደጋስፐሪ (ALCIDE DEGASPERI) መንግሥት በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያን ጥያቄ ለማክሸፍ በዓለም ላይ የነዛው የአጥቂ ፕሮፓጋንዳ ቋሳል አልነበረም:: « .... ኢትዮጵያ ሥልጣኔን ወደ አገሬ ለማስገባትና ሕዝቤም እንዲጠቀም ለማድረግ እንዳልችል፣ በእንግሊዝ፣ በፈረንሣይና በጣልያን ኃይሎች የባሕር በር ተዘግቶብኝ ለብዙ ዘመናት ታፍኜ እኖራለሁ እያለች፣ ምክንያት ስትደረድርና ስትወተውት ቆይታለች:: እንግዲህ ኢትዮጵያ ላይ የፊውዳል አስተዳደር ተከማችቶ፣ ድህነትና ድንቁርና የተስፋፋው በባሕር በር እጦት ከሆነ፣ በኤርትራ በኩል የአሰብ አውራጃ ይለቀቅላትና የባሕር በር ይዛ የምትሠራው ተዓምር ይታይ:: ..... ከዚህ ሌላ ግን፣ ኢትዮጵያ መላ ኤርትራንና ሱማሌን ለማስተዳደር እንዲሰጣት፣ ያለ አቅሟ የምታደርገው መንጠራራት፣ የነዚህን አገሮች ሕዝቦች እንደራሷ ሕዝብ ሕይወት ለማጨለምና ድህነት ላይ ለመጣል መሆኑ መታወቅ አለበት:: ኢትዮጵያ ዛሬ ባላት አቅም፣ እንኳንስ አልፋ ተርፋ ከግዛቷ ውጭ የባዕድ አገሮችን ለማስተዳደር ይቅርና፣ የራሷንም ሕዝብ ከድህነትና ከበሽታ ለማላቀቅ አትችልም:: ....... »

በዚህ መልክ ነበር፣ በዓለም የዜና ማሠራጫ ድርጅቶች አማካይነት፣ የተባበሩት መንግሥታት አባሎችን አስተያየት ለመለወጥ፣ የደጋስፐሪ መንግሥት ስፊ ጥረት ያደረገው:: በዓለም ዋና ዋና ሥፍራዎች ያሉት የጣልያን አምባሳደሮችም፣ ከየአገሩ የፖለቲካና የውጭ ጉዳይ መሪዎች ጋር በየጊዜው እየተገናኙ፣ እጅግ ብርቱ የሆነ የማወናበድ ዲፕሎማሲ በመጠቀም፣ ኢትዮጵያን ለማጥቃት የሚያደርጉት ጥረት ልክ አልነበረውም:: በዋሽንግተን የጣልያን አምባሳደር የነበረው አልቤርቶ ታርኪያኒ (ALBERTO TARCHIANI) መጋቢት 25 ቀን 1949 ዓ.ም ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ረዳት ሚኒስትር ለዲን ራስክ (DEAN RUSK) በመንግሥቱ ስም የገለጸው ሀሳብ ለታሪክ የሚጠቀስ ነው:: « ..... ኤርትራ የኢትዮጵያ ሆና አታውቅም:: በታሪክ፣ በዘርና በባሕል የኤርትራ ሕዝብ የሚመሳሰለው፣ ከቀይ ባሕር ባሻገር ካሉት የዓረብ አገሮች ጋር ነው እንጂ፣ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያዛምድ ምንም ነገር የለም:: በሀይማኖትም በኩል አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ እስላም ሲሆን፣ የክርስቲያኑ ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው:: በጠቅላላው የኤርትራ ሕዝብ እስላሙም ሆነ ጥቂቱ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ፊውዳል መንግሥት እንዳይወድቅበት፣ የጣልያንን አስተዳደር ይመርጣል:: ...... » በማለት፣ የአሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያን ጥያቄ በከፊልም ቢሆን በመደገፍ የወሰደውን አቋም ለማስለወጥ የጣልያን አምባሳደር ብዙ ቀላመደ::

የኤርትራ ሕዝብ ከግማሹ የሚበልጠው ከኢትዮጵያ ጋር ለመሆን መፈለጉንና፣ የጣልያን ቅኝ አስተዳደር እንዳይመለስበት አጥብቆ መቃወሙን የሚገልጽ፣ ዩናይትድ ስቴትስ አባል የሆነበት የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ያቀረበውን ራፖር፣ የስልሣ ዓመቱ የጣሊያን ዲፕሎማት ጨርሶ ዘንግቶታል:: አንድ ጥሩ ዲፕሎማት ለአገሩ ክብርና ጥቅም ሲል መዋሸት ይኖርበታል ቢባልም፣ እንደዚህ የመሰለውን ደረቅ ውሸት በማቅረብ አልነበረም::

በዚህ በ 1949 ዓ.ም በትሩማን አድሚኒስትሬሽን የውጭ ጉዳይ ረዳት ሚኒስትር አልፎ አልፎም ተጠባባቂ ሚኒስትር እየሆነ ከሠራ በኋላ፣ በጆን ኤፍ ኬኔዲ (JHON F.KENNEDY) ዘመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በመሆን የታወቀው ዲን ራስክ (DEAN RUSK) ከጣልያን አምባሳደር በቀረበው ውሸት ላይ መሟገት አልፈለገም:: « ...... የጣልያን ሬፑብሊክ መንግሥት ሱማሌን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር፣ ኤርትራ ከምዕራቡ አውራጃ ከአቆርዳት በስተቀር ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል ...... » የአሜሪካ መንግሥት የወሰደውን አቋም የማይለውጥ መሆኑን፣ ዲን ራስክ በጥሞና አስረድቶ አምባሳደር ታርኪያኒን አሰናብቶታል:: በዚህ የጣልያን መንግሥት ተስፋ አልቆረጠም:: ይህ ከሆነ ከሁለት ሳምንት በኋላ ሚያዝያ 11 ቀን 1949 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት የመጀመሪያው ኮሚሲዮን ላይ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሰጠው መግለጫ « ኤርትራ የኢትዮጵያ ሆና አታውቅም » ብሎ መናገሩ ይታወሳል:: ቀጥሎም በስተኛው ቀን ሚያዝያ 13/1949 ኮምት ስፎርሳ ለአሜሪካ መልዕክተኛ ለጆን ፎስተር ደለስ ባቀረበው ሀሳብ፣ « ..... ኢትዮጵያን መርዳት ከፈለጋችሁ፤ የሞቃዲሾ ሱማሌ ይሰጣትና ኤርትራ በጣልያን ሞግዚትነት ትተዳደር ..... » ብሎ ነበር:: ይህ ሁሉ በግልጽ የሚያሳየው፣ የጣልያን መንግሥት ኤርትራን መልሶ ለመያዝ ምን ያህል እንደሚንገበገብ ነው::

በኤርትራም ውስጥ ሕዝቡ ኢትዮጵያን እንዲጠላ፤ ኢትዮጵያ ወይ ሞት ብሎ የተነሳውን የአንድነት ማህበር ለማፍረስ፣ እስላምና ክርስትያኑን ለማጋደል፣ « ጣልያን ይመለስልን » የሚሉ ባዶ ቀፎ የተንጠለጠለላቸው ፓርቲዎች ለማቋቋም፣ የደጋስፐሪ መንግሥት የረጨው ገንዘብ ልክ አልነበረውም::

በኢንተርናሽናል መስክ ላይ በተለይም የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ በሚደረግበት አካባቢ፣ የጣልያን ዲፕሎማቶችና ጋዜጠኞች የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ጉልበት የሚመክተው አልነበረም:: ሆኖም የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ባላቸው አቅም በሚገባ ተከላክለዋል:: ፕሮፓጋንዳ ጥሩ ውጤት የሚሰጠው፣ አጥቂ ሆኖ ሲተኩስ ነው እንጂ፣ በተከላካይነት ሲመክት አይደለም ቢባልም፤ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ጨዋ በሆነው አቀራረባቸው የብዙ አገሮችን የተዛባ አስተያየት ለማቃናት ችለዋል::

ከጣልያን በኩል ለሚነዛው የአጥቂ ፕሮፓጋንዳ፣ ከኢትዮጵያ የሚሰጠው የመከላከያ መልስ፣ የኢትዮጵያንና የመረብ ምላሽ ሕዝቦችን የታሪክ አንድነት በማብራራት ብቻ የተወሰነ አልነበረም:: ጣልያን፣ የተባበሩት መንግሥታት መልዕክተኞች ታሪክን እያውቁም፣ ወይም እያስታውሱም ብላ በመገመት፣ እውነተኛውን ታሪክ በሀሰት ፕሮፓጋንዳ እየሸፈነች ማቅረቧን፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች በትጋት በማስረዳታቸው፣ ከላቲን አሜሪካ መልዕክተኞች በስተቀር፣ ቁጥራቸው በርከት ያሉት የመንግሥታት ወኪሎች ከጣልያን የቀረበውን ዶክመንት መጠራጠርና መመራመር ጀምረው ነበር::

ለምሳሌ የፖላንድ መንግሥት የመልዕክተኞች መሪ አቶ አክሊሉን በቀጠሮ አግኝቶ የገለጸላቸው አስተያየት፣ የጣልያን ፕሮፓጋንዳ ውጤት መሆኑን ያሳያል:: « ... የጣልያን አምባሳደር የላከልኝን የታሪክ ዶክመንት ሳነብ፣ ኢትዮጵያና ኤርትራ ከጉርብትና በስተቀር ጨርሶ የማይመሳሰሉ ሕዝቦች መሆናቸውን ተረዳሁ:: ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላትን አገር ካልተሰጠኝ ብላ ጊዜ

ከምታጠፉ፣ የባሕር በር በአሰብ በኩል አግኝታ ጉዳዩ ባጭሩ ፍጻሜ ቢያገኝ አይሻልም ወይ ? ....... » ብሎ ጠየቃቸው።

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ የሰጡት መልስ፣ በተለይ የሰውየውን ሞራል የሚነካ ነበር። « ..... አንተን የመሰለ የአንድ ትልቅ ታሪክ ያለው አገር እንደራሴ፤ የጣልያን አምባሳደር ምን ያህል ዝቅተኛ ግምት ቢኖረውና ምንስ ያህል ንቀት ቢያድርበት ነው ? ይህን የመሰለ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ እንድታነብ ደፍሮ የላከልህ ? ..... እኔ በጣም የማዝነው ጣልያን የተባበሩት መንግሥታት አባሎችን ለማታለል በመሞከሩ ሳይሆን፣ አንተን የመሳሰሉ ታሪክን የማይመራመሩ የተጻፈላቸውን ብቻ አንብበው የሚስለፉ ደጋፊዎች ለማግኘት መቻሉ ነው ...... » አሉት። አቶ አክሊሉ ንግግራቸውን ሳይጨርሉ፣ የፖላንዱ መልዕክተኛ ተበሳጭቶ ትቷቸው ወደ ወንበሩ ተመለሰ። ሆኖም ይህች « አንተን የመሳሰሉ ታሪክን የማይመራመሩ » የተባለችው ቃል በጣም ስለነካችው መጠነኛ ምርምር (ሪሰርች) ካደረገ በኋላ እንደገና በሌላ ቀን ወደ ኢትዮጵያ መልዕክተኞች መቀመጫ ሄዶ፣ አቶ አክሊሉን ችላ ብሎ፤ ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህንን በማነጋገር እንዲህ አለ። « ..... ስለ ኤርትራ ጉዳይ የጣልያንን ብቻ ሳይሆን የእናንተንም ዶክመንት፣ ሌሎችንም የታሪክ መጻሕፍቶች ተመልክቻለሁ። የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት ከተቋረጠ ስልሣ ዓመት ስለሆነ፤ በድሮው መንፈስና አስተሳሰብ ላይ ተመሥርቶ፣ ይህ ሕዝብ ዛሬ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መሆን ይችላል ብሎ መፍረድ ያስቸግራል። በዚህ በስልሣ ዓመታት ውስጥ የትውልድም፣ የአስተሳሰብም፣ የሕይወት ኑሮም፣ ለውጥ መኖሩ የማይካድ ነው። ኢትዮጵያ የባሕር በር እንድታገኝ እንኳንስ እኛን የመሳሰሉ አገሮችና ጠላቴ የምትለው ጣልያንም ራሱ ይደግፉታል። ነገር ግን <u>ኤርትራ በሙሉ ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ መስማማት የሚቻለው፣ የኤርትራ ሕዝብ ኢትዮጵያን እፈልጋለሁ ሲል ብቻ ነው</u> ..... » አላቸው።

ብላታ ኤፍሬምም እንደ አቶ አክሊሉ አልተበገሩለትም። በጣም በረጋ መንፈስ መልሰውለታል። « ..... የጣልያንን ፕሮፓጋንዳ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያንም ማስረጃ በማንበብህ ጥሩ አድርገሃል። ሆኖም፣ እዚህ ላይ ሁለት ነገር መለየት ያስፈልጋል። ለሁላችሁም እስከ መኝታ ቤታችሁ ድረስ አምሮና ተጠርዞ የተላከላችሁ የጣልያን ዶክመንት ዝግጅቱም ግቡም ለፕሮፓጋንዳ ነው። የኢትዮጵያ ጽሑፍ ግን እውነተኛውን ታሪክ ለማያውቁ ትምህርት እንዲሆናቸው የተዘጋጀ ነው። አንተም በበኩልህ አደረግኩ የምትለው ምርምር፣ አሁንም አንድ ነገር ይጐለዋል። ከሁለት ዓመት በፊት የኤርትራ ሕዝብ ስሜቱም ፍላጐቱም ምን እንደሆነ፤ ታላቁ ወዳጃችሁ መስኮብ፤ አባል የሆነበት የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ተልኮ ተጠይቋል። ከኤርትራ ሕዝብ አብዛኛው፣ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል መፈለጉን በትክክል አስታውቋል። ወዳጄ ፈቃድህ ቢሆን የመርማሪው ኮሚሽን የሰጠውን ራፖር ብታነበው ጥያቄህን ይመልስልሃል » አሉት።

የፖላንዱ መልዕክተኛ በዚህ ማብራሪያ አልረካም። « ..... ስልሣ ዓመት ሙሉ ተለያይቶ የኖረ ሕዝብ ዛሬ ምን እንደሚፈልግ የራሱን ዕድል በራሱ መወሰን አለበት ሲባል፤ ከሁለት ዓመት በፊት የእንግሊዝና የአሜሪካ መልዕክተኞች (መስኮብ ሳይስማማ) የሰጡት ራፖር እውነተኛውን የሕዝቡን ስሜት የጨበጠ ነው ማለት አይቻልም ...... » አለ። በዚህ ጊዜ አቶ አክሊሉ ጣልቃ ገብተው ጥያቄ አቀረቡለት። « ..... የመስኮብ፤ የኦስትሪያና የጀርመን መንግሥታቶች፣ በተለያዩ

ጊዚያቶች በጉልበት የአገርህን የፖላንድን ነፃነት እየገፈፉ፣ አገሩን ለሶስት ተከፋፍለው ሲገዙ ኖሩ። የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ምክንያት ሆኖ፣ ከመቶ ዓመታት ሥቃይ በኋላ የፖላንድ አንድነትና ነፃነት ተመሠረተ። እንግዲህ፣ ለሶስት ኃያላን መንግሥታት አገሩም ሕዝቡም አሶስት እጅ ተከፍሎ፣ ልዩ ልዩ የባዕድ ቋንቋና ባሕል ሲከተል ለመቶ ዓመታት በመኖሩ፣ የአንዱ አውራጃ ከሌላው አውራጃ ሕዝብ ጋር ሳይረሳሳ አይቀርምና አንድነቱን መፈለግ አለመፈለጉ መጠየቅ አለበት የሚል ሀሳብ ቀርቦ ኖርዋል ወይ ? ..... » መልዕክተኛው፣ ራሱን እየነቀነቀ፣ ጨርሶ የማይመሳሰሉ ጉዳዮች ስለሆኑ፣ የፖላንድን ፕሮብሌም ከኤርትራ ጋር ለማነጻጸር የሚደረገውን ሙከራ አልቀበልም አለ። ታሪኩን ባጭሩ እንድገልጽ ብትፈቅድልኝ ትቀበለዋለህ ብለው አቶ አክሊሉ ማብራሪያቸውን ቀጠሉ።
« ..... ኢትዮጵያ የምትባለው የብዙ ሺህ ዓመት ታሪክ ያላት አገር ወሰኗ በሰሜን ቀይ ባሕር፣ በደቡብ የሕንድ ውቅያኖስ ነው። ፖላንድ በአሥራ ስምንተኛው መቶኛ ዓመት መጨረሻ ላይ የውጭ ኃይሎች በግፍ አገሯን እንደተከፋፈሏት፤ በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ፍጻሜ ላይ፣ የጣልያን ኮሎኒያሊስትም፤ ከሰሜን ዛሬ ኤርትራ የተባለውን ክፍለ ሀገር የኢትዮጵያን መንግሥት ወግቶ ያዘ። ይህ ቀድሞ «መረብ ምላሽ» እየተባለ ይጠራ የነበረውና ኋላም በኮሎኒያሊስት ጣልያን «ኤርትራ» የተባለ ስም የወጣለት አገር፣ ለስልሣ ዓመታት ከእናት አገሩ ተለይቶ ቢኖርም፣ እንደ ፖላንድ ሕዝብ ባሕሉንና የኢትዮጵያዊነት ስሜቱን ጠብቆ ይዞ የኖረ ነው። የፖላንድ ሕዝብ ነፃነትና አንድነት እንደገና ሲገነባ፣ ጥንቱንም ቢሆን አንድ ዘር አንድ ባሕልና አንድ ሀይማኖት የነበረው በመሆኑ፤ ለአንድነቱ ጥያቄ አልቀረበበትም። ኢትዮጵያ ግን ሁልጊዜ ፍርድ ስለሚነፈጋት፣ ያቀረበችው ማስረጃ አይበቃም ተብሎ፣ ቀደም ሲል ብላታ ኤፍሬም እንዳስረዱት፣ የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ኤርትራ ተልኮ፤ የአብዛኛውን ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት ፍላጐት አረጋግጦ ተመልሷል። ይህንን ሪፖርት የሶቪየት ሕብረት መንግሥት አልቀበልም ብሏል። የፖላንድ መንግሥትም መስኮብ ያልተስማማበትን ጉዳይ አብሮ ከመቃወም በስተቀር ሌላ ምርጫ ስለሌለው በጣም አናዝንለታለን። ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ሆነ ከአሜሪካ፣ ከመስኮብ ሆነ ከፈረንሣይ፣ የሚቀርበውን ሀሳብ ለመቃወምም ለመተቸትም መብቷና ነፃነቷ የተጠበቀ ነው። ...... አሁንም አቶ አክሊሉ ማብራሪያቸውን ሳይጨርሱ፣ የፖላንዱ መልዕክተኛ በብስጭት መንፈስ አቋርጦ ወደ ወንበሩ ተመለሰ።

እነዚህ የመስኮብ የሥልጣን ጃንጥላ የተጋረደባቸው « ሳቴሊቶች » እየተባሉ የሚጠሩ አገሮች፣ በመሠረቱ የፋሽስት ደጋፊዎች አልነበሩም። በጌኔቭ የመንግሥታት ማህበር ዘመን የሙሶሊኒ ጦር ኢትዮጵያን በወጋ ጊዜ፣ እነዚህ አገሮች ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የሞራል እርዳታ መስጠታቸው ይታወሳል። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች፤ ፖላንድ .... ቼኮዝሎቫኪያ ... ወዘተ ..... ሳይወዱ በግድ የስታሊን ጭፍሮች እንዲሆኑ ተፈረደባቸው።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ፣ በሚታይበት ጊዜ፣ እነ ፖላንድና ቼኮስሎቫኪያ፣ የመስኮብን መምሪያ እየተቀበሉ ከመናገር በስተቀር የየመንግሥታቸውን አስተያየት መግለጽ አይፈቀድላቸውም ነበር። የፖላንዱ መልዕክተኛ ባሳየው መንፈስ፣ የመስኮብ ተከታይ መሆኑን ለማስመስከር ከሚያደርገው ጥረት ጋር፣ በተለይ ለኢትዮጵያ ቅን አስተያየት የሌለው ሰው እንደነበረ ታውቋል።

# የላቲን አሜሪካ አገሮች፤ የጣልያን ጠበቆች

በ 1949 ዓ.ም አሥራ ስምንቱ የላቲን አሜሪካ አገሮች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ በድምፅ ቁጥር ያላቸው ተሰሚነት፣ ከፍ ያለ መሆኑ ጉልቶ ይታይ ነበር። አንድ ጉዳይ በኮሚሲዮን ተጠንቶ፣ ውሳኔው በአባል መንግሥታቶች በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ማለፍ ካለበት፣ የእነዚህን የአሥራ ስምንቱን ላቲኖች ድጋፍ ካላገኘ ሊጸድቅ አይችልም። ይሁን እንጂ በዚያን ዘመን አሳዛኝ ሆኖ የሚታወሰው፣ ላቲኖቹ ለአፍሪካ ሕዝቦች ምንም ዓይነት ስሜት ስላልነበራቸው፣ ያላቸውን የድምፅ ኃይል የሚለግሱት ለኮሎኒያሊስ ቶች ጥቅም በመሆኑ ነበር።

የኤርትራ፣ የሊቢያና የሱማሌ ጉዳይ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቀርቦ በሚመረመርበት ጊዜ፣ እነዚህ አገሮች ለቀድሞ ቅኝ ገዢያቸው ለጣልያን ተመልሰው እንዲሰጡ፣ የላቲን አሜሪካ መንግሥታት መልዕክተኞች ያደረጉት ጥረት ወሰን አልነበረውም። በተለይ እንደ አርጀንቲና የመሳሰሉት አገሮች ከሲኞር ደጋስፐሪ መንግሥት ጋር ተሰልፈው፣ ኮሎኒ የነበሩት አገሮች ሁሉ፤ ተመልሰው ኮሎኒ ሆነው ተረግጠው እንዲገዙ ጉሮሮአቸው እስኪደርቅ የጮሁትና የታገሉት፣ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፣ በሚያሣፍርም አኳኋን ነበር።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጠቅላይ ሚኒስትር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ በ1966 ዓ.ም፤ አንድ ቀን ከወዳጆቻቸው ጋር ሲጨዋወቱ የተናገሩት ቃል በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀስ የሚገባው ነው። « ...... የላቲን አሜሪካ አገሮችን ምንጊዜም ይቅርታ ሳላደርግላቸው የምኖረው፣ በተለይ በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያን ጥያቄ ለምን አልደገፉም ? ብዬ አይደለም። በጣም ያሳዘነኝ ከኮሎኒያሊስት ጣልያን ጋር ሆነው፤ የቀድሞዎቹ ቅኝ አገሮች በሙሉ ተመልሰው የጣልያን ኮሎኒ እንዲሆኑ፣ ሳያፍሩ በግልጽ በተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ ያደረጉት ተጋድሎ ነው። ...... » ጸሐፊ ትእዛዝ እንዳሉት በዚያን ዘመን የላቲን አሜሪካ አገሮች ከፈረንሣይ ጋር ሆነው ለጣልያን መንግሥት ጥቅም በብዙ የተዋጉ ናቸው።

በሚያዝያ ወር 1949 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን ላይ፣ የኤርትራ ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ በዘር፣ በባሕልና በታሪክ፣ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ያላቸውን አንድነት በማብራራት፣ የሁለቱ ሕዝቦች መዋሀድ ለሠላምና ለልማት ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን እየደጋገሙ ያስረዱ ነበር። ከዚህም በቀር አቶ አክሊሉ በሚያደርጉት ንግግር ሁሉ ጣልያንን አጠንክረው ስለሚያወግዙ፣ የአርጀንቲና መልዕክተኞች መሪ አምባሳደር ሆሴ አርሴ ተበሳጭቶ የኢትዮጵያን ሀሳብ ሲቃወም እንዲህ አለ።
« ..... አንድ ዓይነት ዘርና ባሕል አለው የሚባል ሕዝብ ሁሉ፣ ከያለበት እየተሰበሰበ በአንድነት እንዲቀላቀል ያስፈልጋል ከተባለ፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለምን ጂኦግራፊ ለማስተካከል ሥልጣን ያልተቀበለ መሆኑን የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ቢያውቀው እንዴት ጥሩ ነበር ? ..... ለምሣሌ የግብፅና የሊቢያ ሕዝቦች ከአንድ ዓይነት ዘር የመነጩ፣ አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ፣ አንድ ዓይነት ባሕልና አንድ ዓይነት ሀይማኖት የሚከተሉ ናቸው። ነገር ግን የግብፅ መንግሥት ሊቢያ ለእኔ ትሰጠኝ ብሎ አልጠየቀም። የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ይህንን ሁሉ የሚገነዘብ ቢሆን ኖሮ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት

ጊዜ አይባክንበትም ነበር ...... » ብሎ ጮኸ። ይህ አነጋገር የኢትዮጵያን መልዕክተኞች በብርቱ አበሳጭቷል።

የአርጀንቲና መልዕክተኛ ንግግር ከተፈጸመ በኋላ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ መልስ ሲሰጡ፣ ከሁሉ በፊት ራሳቸውን ማስተዋወቅ አስፈላጊ ሆኖ ታይቷቸዋል። « ..... የዛሬ አራት ዓመት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተሩ ሲዘጋጅና አንቀጽ በአንቀጽ ሲጠና፣ የሕግ ኮሚቴው አባል ሆኜ አስተዋፅኦ ያደረግኩና፣ ብመጨረሻም ቻርተሩ ሲጸድቅ፣ በአገሬ ስም የፈረምኩ እኔ ነኝ። ከዚህም በቀር የተባበሩት መንግሥታት ሥልጣንና ተግባር ምን እንደሆነ፣ ገና ከጦርነቱ በፊት በገኔቭ የመንግሥታት ማህበር ይባል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ተከፍዬ የማውቀው ስለሆነ፣ እንደ አርጀንቲና መልዕክተኛ ከመሳሰሉት አዲስ መጭዎች፣ ዛሬ የምማረው ትምህርት ወይም የማገኘው አዲስ ኤክስፔሪያንስ የለም። ይልቅስ በእኔ ግምት ከተሰበሰብንበት ጉዳይ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን የዳንቴን (DANTE) ድርሰት እየጠቀሱ ከመመጻደቅና በጣልያን ፕሮፓጋንዳ ተመርዞ ለኮሎኒያሊስቶች ጥቅም ከመጨፈር፤ የአርጀንቲና ወኪል ላለንበት ዘመን በጣም አስፈላጊ የሆነውን የቅርቡን የዓለም ታሪክ ለማስተዋል ቢሞክር፣ በዚህ ጉባኤ ላይ በየጊዜው ከሚያደርጋቸው የተዘበራረቁ ስህተቶች ሊድን ይችል ነበር። ለምሣሌ በኮሎኒያሊስት ጣልያን፣ ስም የወጣለት «ሊቢያ»፤ የግብፅ መንግሥት ግዛት ሆኖ የማታውቅና፤ የጣልያን ኮሎኒያሊስትም አገሪቱን ቅኝ አድርጉ የወሰደው ከቱርኮች ላይ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ኤርትራ ግን፣ በ1885 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ላይ የጣልያን ኮሎኒያሊስት በጦር ነጥቆ የወሰደው አገር ነው። ስለዚህ፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለዓለም ሠላምና ለትክክለኛ ፍርድ ተብሎ የቆመ በመሆኑ፣ በቀማኛ የተወሰደ አገር ወደባለቤቱ እንዲመለስ ፍርድ ሲጠየቅ፣ የዓለምን ጂኦግራፊ ማስተካከል አለማስፈለጉን ክቡር አምባሳደር አርሴና አጃቢዎቹ እንዲያውቁት አሳስባለሁ።

....... የአርጀንቲና መልዕክተኛ ሀሳቡን ሲደመድም፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ በሚፈጥረው ችግር ምክንያት፣ የተባበሩት መንግሥታት ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ውሳኔ እንዳይሰጥ፤ ጊዜ እባክኖበታል የሚል ትችት ሰጥቷል። እንደ እውነቱ ከሆነ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን የቀረበለትን ሥራ ለማቀላጠፍ ያልቻለው፤ «የዳንቴ» አድናቂዎች ነን በማለት ለጣልያን ኮሎኒያሊስት ከበሮ መችዎች የሆኑት አገሮች፣ በሚያደርጉት አሰልቺ የሆነ የፕሮፓጋንዳ ሙዚቃ ምክንያት መሆኑን፣ የተከበሩ የልዩ ልዩ አገሮች መልዕክተኞች መታዘባቸውን አልጠራጠርም።

በዚህ አጋጣሚ ለወዳጆቼ የላቲን አሜሪካ አገሮች እንደራሴዎችና፤ በተለይም ለአርጀንቲና መልዕክተኛ አጥብቄ ለማሳሰብ የምፈልገው አንድ ትልቅ ጉዳይ አለ። ዛሬ ከኮሎኒያሊስት ጣልያን ጋር አድማ መትታችሁ በአፍሪካ ሕዝቦች ላይ የምታደርሱትን በደል፤ አገሬ ኢትዮጵያ ከላይቤሪያና ከግብፅ ጋር ሆና በትዝብት ትመለከታችኋለች። ዛሬ ሶስት ብቻ ሆነን የምታዩን ነፃ የአፍሪካ አገሮች፤ በቅርብ ዘመን ውስጥ አሥር ጊዜ ታጥፈን፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ተገቢ ሥፍራችንን ይዘን፤ ከእናንተ በተለየ ሁኔታ ለዓለም ሠላምና ለትክክለኛ ፍርድ ድምፃችንን የምናሰማበት ዕድል እንደሚኖረን አንጠራጠርም። ..... ወዳጆቻችን የላቲን አሜሪካ አገሮች እና በተለይ የአርጀንቲና ወኪል የኤርትራ፣ የሱማሌና የሊቢያ ሕዝቦች በጭካኔ አገዛዝ ሲያስተዳድራቸው ለነበረው ለጣልያን ኮሎኒያሊስት መንግሥት ተመልሰው እንዲሰጡ የምታቀርቡትን ድጋፍና

የምታደርጉትን ዲስኩር፣ የነገው የዓለም ሕዝብ ታሪክ ምን ያህል የወቀሳ ምዕራፍ አዘጋጅቶ የሚጠብቃችሁ መሆኑን እንድትገነዘቡት፣ አደራ እያልኩ ንግግሬን አቆማለሁ:: ....... »

አቶ አክሊሉ ተበሳጭተው የገለጹትን ትንቢትና ምክር ያዘለ ሀሳብ፣ የላቲን አሜሪካ መንግሥታት ወኪሎችና በተለይም አርጀንቲና ቁም ነገር አድርገው አላደመጡም:: በዚያን ዘመን ላቲኖቹ ከጣልያን ጋር በመሠለፍ አውሮፓውያን ነን ብለው ስለአመኑ፣ የነገው አፍሪካ ጉዳይ አላሳሰባቸውም:: ይልቁንም ለአፍሪካውያኖችና ለእስያውያኖች ያላቸው ግምት በንቀት መንፈስ ላይ የተመሠረተ እንደነበረ አንዳንድ የታሪክ መዝጋቢዎች ታዝበዋል:: ይሁን እንጂ ኢትዮጵያና ላይቤሪያ በአፍሪካዊነታቸው ኮርተው፣ ለላቲኖቹ ጥጋብ አጸፋውን በመመለስ ደህና አድርገው ተቋቁመዋቸዋል:: ላቲኖቹም የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ፣ በተባበሩት መንግሥታት ሸንጎ ላይ የመጨረሻው ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ፣ ለጣልያን ታማኝነታቸውን ሳያጓድሉ ዘልቀዋል::

በ 1949 ዓ.ም አቶ አክሊሉ ምርር ብለው የሰጡት ትንቢት አየር ላይ አልቀረም:: ከአሥር ዓመታት በኋላ የሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳኛው ዘመን ሲጀመር፣ የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች፣ ከኮሎኒ አስተዳደር እየተላቀቁ በብዛት ነፃነታቸውን ሲጐናጸፉ፣ የላቲን አሜሪካ አገሮች የፈረንጅነት መንፈስ ሊቀጥል አልቻለም:: አፍሪካውያንና እስያውያን «የሶስተኛው ዓለም» በተባለው ክበብ ውስጥ (AFRO ASIAN GROUP) ሕብረታቸውን አጠንክረው ለጋራ ጥቅማቸው ከምዕራባውያኖች ጋር ሲታገሉ፣ ላቲኖቹ ከሁለት ያጣ ጐመን ሆነው ማህል ቤት ቀሩ:: በሥልጣኔ አለመግፋታቸው፣ በኢኮኖሚም ድህነታቸው፣ በግልጽ እየታያቸው መጣ:: የላቲን የደም ጠብታዎች፣ የሠለጠነ ህይማኖት ተከታዮች፣ ከአውሮፓውያኖች ጋር የሥጋ ዘመዶች ነን ብለው ተኩፍሰው የኖሩት፣ በባዶ ሜዳ መሆኑ ገባቸው:: ከምዕራባውያኖችም ጋር ያላቸውን ግንኙነት በጥልቅ ሲመረምሩ፣ በአሽከርና በጌታ ደረጃ እንጂ በእኩልነት አለመሆኑን ተገነዘቡት:: በዚህ ጊዜ ከአፍሪካና ከእስያ አገሮች ጋር ሶስተኛው ዓለም ተብሎ በተሰየመው ክበብ፣ እኛም እንደእናንተው ነን ብሎ ተንደርድሮ ከመመዝገብ በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም:: በኋላ የመጣ ዓይን አወጣ እንደሚባለው፣ የሶስተኛው ዓለም ሕብረት እየተስፋፋ ሲሄድ፣ የገለልተኞች አገሮች ፖሊሲ ሲመሠረት፣ የሰባ ሰባቱ አገሮች ግሩፕ ሲቋቋም፣ ዋና ተዋናይ ለመሆንና ልታይ ልታይ ለማለት የቃተቱት እነዚሁ ላቲኖች ሆነው ታዝበናቸዋል:: በሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሣኛው ዓመተ ምህረት ላይ ከኮሎኒያሊስቶች ጋር በመሠለፍ፣ የአፍሪካን መብት በመጻረር፣ የሚፈጽሙትን አሳዛኝና አሳፋሪ አድራጐት በትክክል ያዩና፣ ባላቸው አቅም ለመከላከል የተጋፈጡት ኢትዮጵያና ላይቤሪያ ብቻ በመሆናቸው፣ በሌሎቹ አፍሪካ አገሮች ዘንድ ያልታወቀባቸው መስሎ ሳይታያቸው አልቀረም:: ይህ ጉዳይ ራሱን የቻለ አንድ ታሪክ ስለሆነ፣ የዛሬውም ሆነ የሚቀጥለው የአፍሪካ ትውልድ በዝርዝር ተመራምሮ እንደሚጽፈው እንጠራጠርም::

ቀደም ሲል እንደተነገረው፣ የኤርትራን፣ የሱማሌንና የሊቢያን ጉዳይ መፍትሔ ለመስጠት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሚያጠናበት ጊዜ፣ የላቲን አሜሪካ አገሮች የሚከተሉት ፖሊሲ፣ ከጣልያን መንግሥት በሚሰጣቸው መመሪያ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ በየጉዳዩ ላይ ድጋፍ ለመስጠትም ሆነ ለመቃወም፣ ላቲኖቹ የየአገራቸውን መንግሥት መጠየቅ የለባቸውም:: ድካሙ እንዲቃለልላቸው ከቴሌግራም ወጭም እንዲድኑ፣ ኒውዮርክ ያለው የጣልያን



የአርጀንቲና ዋና መልዕክተኛ ሆሴ አርሴ እና የጣልያን አምባሳደር አልቤርቶ ታርኪያኒ ሲመካከሩ:: ያለ ጥርጥር ሆሴ አርሴ ከጣልያኑ ባለሥልጣን መምሪያ ሲቀበል መሆን አለበት::

(ኒውዮርክ 1949)
(ፎቶ U.N)

መንግሥት ሊየዞን ቢሮ፣ በሲርኩለር መምሪያውን ያስተላልፍላቸዋል:: ላቲኖቹም ያለባቸው ኃላፊነት ያለ አንዳች ሀሳብና ያለአንዳች ጭንቀት የተሰጣቸውን መምሪያ ተከትለው በጉባኤው ላይ የጣልያን አዋጅ ነጋሪ ሆኖ ማቅራራት ብቻ ነው::

አንድ ጊዜ ስለ ጣልያን የቀድሞ ከሎኒዎች ጉዳይ በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ የደረሰው ሁኔታ አስቂኝ ነበር:: የአርጀንቲናው እና የመስኮቡ መልዕክተኛ ሊቀመንበሩን ጠይቀው በተናጋሪዎች ሊስት ተመዘገቡ:: በመካከሉ የአርጀንቲናው መልዕክተኛ አንድ ሰው ጠርቶት ከጉባኤው አዳራሽ ወጣ:: የመናገሪያው ተራ ሲደርስ የጉባኤው ሊቀመንበር አምባሳደር አርሲ (ARCE) እያለ ቢጣራ፣ የሚመልስ ጠፋ:: ወዲያው አቶ አክሊሉ ጣልቃ ገብተው፣ « አምባሳደር አርሲ ከጣልያን መንግሥት መምሪያ ለመቀበል ወጥቶ ነው ቶሎ ይመለሳል » አሉ:: በዚህ ጊዜ የስብሰባው ተካፋዮች መሣቅ ጀመሩ:: ወዲያው የጉባኤው ሊቀመንበር ለሚቀጥለው ተናጋሪ ለሶቪየት ሕብረት መልዕክተኛ መድረኩን ሰጠ:: አምባሳደር አርሲ ተመልሶ ወንበሩን ሲይዝ፣ አንድ የዞረበት የአርጀንቲና መልዕክተኞች አባል፣ አቶ አክሊሉ የተናገሩትን የመስኮቡ መልዕክተኛ ከጣልያን መምሪያ ለመቀበል ወጥቶ ነው ብሉ በማሬዝ ተናገረ አለው:: ዶክተር አርሲ በጣም ተናዶ ከሊቀመንበሩ የመናገሪያ ፈቃድ ሲያገኝ፣ በመስኮቡ መልዕክተኛ ላይ የስድብ አጉዳ አወረደበት:: አቶ አክሊሉም እሳቱን ለኩሰው ከስብሰባው አዳራሽ ወጡ:: ...... የመስኮቡ መልዕክተኛ ከአርጀንቲናው ልዑክ የወረደበት ስድብ በምን ምክንያት መሆኑ በትክክል ሳይገባው የዕለቱ ስብሰባ ተፈጸሞ ተበተነ::

ከሚያዝያ 6 ቀን እስከ ግንቦት 6 ቀን 1949 ዓ.ም ድረስ አንድ ወር ሙሉ የጣልያን መንግሥት ከፍተኛ ጥረት ያደረገው፤ ኤርትራን ለማገኘት በእስቸኳይ ለማስወሰን ነበር:: ይህንኑም የጣልያን ፍላጐት ለማስፈጸም የላቲን አሜሪካ አገሮች ለሠላሣ ቀናቶች ሳያቋርጡ ሲሞሉ ከረሙ::

# ኢትዮጵያና አራቱ ኃያላኖች

ከአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች መካከል በተለይ ኤርትራን በሚመለከት ጉዳይ፣ በከፊልም ቢሆን ኢትዮጵያን ለመርዳት የሞከሩት እንግሊዝና አሜሪካ ናቸው:: ይኸውም ከኤርትራ ግዛት ከምዕራባዊው ቆላ አውራጃዎች በስተቀር፣ ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀድ፤ አሜሪካኖች ሚያዝያ 6 ቀን እንግሊዞች ሚያዝያ 7 ቀን 1949 ዓ.ም ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን ያቀረቡት ሀሳብ ነው:: ይሁን እንጂ፤ እንግሎ አሜሪካኖች ይህን ሀሳብ ሲያቀርቡ፣ ከዚሁ ጋር አያይዘው ጣልያኖችን ይማርካል በማለት ሁለት አስተያየቶች ደንቅረዋል:: እነዚህም፣

1ኛ/ በአገሩ ላይ ተወልደው ላደጉት ለጣልያን ተወላጆች ዋስትና ያለው መብት በሕግ ተደንግጐ እንዲሰጣቸው፣

2ኛ/ ጣልያኖች አልምተው ደህና ደረጃ አድርሰዋቸዋል ለተባሉት ለአሥመራና ለምፅዋ ከተሞች በአቶኖሚ የሚተዳደሩበት ልዩ ቻርት እንዲዘጋጅላቸው የሚል ነበር::

በኢትዮጵያ በኩል መጀመሪያ የኤርትራ ግዛት በሁለት እንዲከፈል የተባለውን፣ ኤርትራውያኖቹም ሆኑ ኢትዮጵያውያኖች የማይስማሙበት ስለሆነ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ተቃውሞውን ሲቀጥል ቆይቶ ነበር:: ሁለተኛ፣ ለአሥመራና ለምፅዋ ቻርት ያስፈልጋቸዋል የተባለውንም በአንድ አገር የውስጥ ጉዳይ መግባት፣ ተገቢ አይደለም በማለት የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ክርክሩን ቀጥሏል:: ነገር ግን በእንግሊዝና በአሜሪካ ተደግፎ የቀረበውን በተለይ ኤርትራን በሁለት የመክፈል ጉዳይ አንቀበልም ብሎ መጋተሩ የሚበጅ ስላልሆነ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ቅሬታውን እያለሰለሰ፣ ለጊዜው ሌላ ምርጫ ባለመኖሩ እንስማማለን ማለት ግዴታው ሆነ::

የሶቪየት ሕብረት እንደተለመደው በእንግሎ አሜሪካኖች ተጠንስሶ የቀረበው ሀሳብ፣ ለኮሎኒያሊስቶች መጠቀሚያ የታቀደ ነው በማለት በጥብቅ ተቃወመ:: ከምዕራባውያኖች፣ በተለይም ከእንግሊዝና ከአሜሪካ የሚመነጭ ሀሳብ፣ ምንም እንኳን አልፎ አልፎ መስኩብ ከሚያስበው ጋር የሚቀራረብ ሆኖ መቃወሙ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ ስታሊኒዝምና ካፒታሊዝም በአንድ ጉዳይ ላይ ተስማምተው እንዳይታዩ፣ የሶቪየት ሕብረት እንደምንም አንድ እንከን ፈልጐ ማጥላላትና ማውገዝ ቋሚ ፖሊሲው ነበር::

በተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን ላይ፣ የሶቪየት ሕብረት መንግሥት ሚያዝያ 9 ቀን 1949 ዓ.ም ባቀረበው ሀሳብ፣ የአራቱ ሀያላን መንግሥታቶች የሞግዚት አስተዳደር በሶስቱም ቅኝ ግዛቶች ላይ ተመሥርቶ፣ ኤርትራና ሊቢያ ከአምስት ዓመት በኋላ፣ ሱማሌ ከአሥር ዓመት በኋላ፣ ነፃነታቸውን ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ ነው፤ የሚል ሀሳብ ማቅረቡ ይታወሳል:: ሶስቱም ቅኝ ግዛቶች በኃያላን መንግሥታት ሞግዚትነት በሚተዳደሩበት ጊዜ፣ ለኤርትራና ለሱማሌ ጉዳይ ኢትዮጵያ፣ ለሊቢያ ጉዳይ ግብፅ፣ ለጠቅላላው ጉዳይ ጣልያን፣ የሞግዚቶቹ ኮሚቴ አባሎች ሆነው ሊመደቡ እንደሚችሉ፣ የሶቪየት ሕብረትን ዴሞክራሲ የሚያመለክት ተጨማሪ ሀሳብ ተያይዞ ቀርቦ ነበር:: የመስኩብ መንግሥት ይህን በሚያዝያ 9 ቀን 1949 ዓ.ም ያቀረበውን ሀሳብ፣ በየአደባባዩ ደጋግሞ ቢናገርና፣ በጽሑፍም በየሥፍራው ቢበትን፣ አሜሪካና እንግሊዝ ፈረንሣይና ጣልያን እንኳንስ ሀሳቡን ለመቀበል፣ ዝርዝሩንም ለመስማት አልፈለጉም::

በኢትዮጵያም በኩል የስታሊን መንግሥት አስተያየት ጨርሶ የማይፈለግ ነበር:: እርግጥ ለኢትዮጵያ የባሕር በር ስለሚያስፈልጋት ከኤርትራ ክልል ውስጥ፣ የአሰብ አውራጃ ተቆርጦ ወደ ኢትዮጵያ እንዲደባለቅ የስታሊን መንግሥት ተስማምቷል:: ይሁን እንጂ፣ ይህንን ሀሳብ የኢትዮጵያ ዋና ጠላት የሆነውም የጣልያን መንግሥት ስለደገፈው፣ የቀ.ኃ.ሥ መንግሥት የሶቪየት ሕብረት ያደረገውን ዲስኩር የተለየ ግምት አልሰጠውም:: በ 1936 ዓ.ም የሙሶሊኒ ጣልያን ኢትዮጵያን በጦር በወጋ ጊዜ፣ የስታሊን መንግሥት የሞራል ድጋፉን የሰጠ ቢሆንም፣ ከጦርነቱ በኋላ፣ ኤርትራንና ሱማሌን ለማግኘት የ.ቀ.ኃ.ሥ መንግሥት ያቀረበውን ጥያቄ በጥብቅ ተቃውሟል:: የስታሊን መንግሥት በኢትዮጵያ ጥያቄ ላይ የወሰደውን አቋም፣ የሶቪየት ሕብረት የሥልጣን ጃንጥላ የተዘረጋባቸው የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች፣ እነ ፖላንድና እነ ቼኮስሎቫኪያ (ከዩጐዝላቮ ከቲቶ መንግሥት በስተቀር) ሁሉም ተከትለው ማጫፈር ግዴታቸው ነበር::

የኃያላን መንግሥታቶች ክበብ አራተኛይቱ አባል የሆነችው ፈረንሣይ፣ ስለ ቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ የምታቀርባቸው ሀሳቦች የጣልያንን ፍላጐት ለማርካት ስለሆነ፣ የኢትዮጵያን ጥያቄ ለማጻመዋ ጨርሶ አልፈለገችም። በ1935 ዓ.ም አነ ፒየር ላቫል (PIERRE LAVALE) ከሙሶሊኒ ጋር ተሻርከው ኢትዮጵያን እንደከዷት ሁሉ፣ ከ 1945 ዓ.ም ጀምሮ በየወራቶቹ እንደ አየሩ ሲለዋወጡ የቆዩት የፈረንሣይ ካቢኔዎችም፣ በኤርትራ ጉዳይ የኮሎኒያሊስት ጓደኛ ለማግኘት ድጋፋቸውን ሲሰጡ የከረሙት ለጣልያን መንግሥት ነበር።

ቅኝ ግዛቶች የነበሩት፣ ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ ተመልሰው ለጣልያን እንዲሰጡ፣ ፈረንሣዮች ከላቲን አሜሪካ አገሮች ጋር ሆነው በየአደባባዩ ሲጮሁ የሚያጸምጣቸው ስለአጡ፣ በ 1949 ዓ.ም በተለይ በኤርትራ ጉዳይ ፖሊሲያቸውን በመጠኑ ለመስወጥ ሞከሩ። ኤርትራ በሙሉ ለጣልያን ትመለስ የሚለውን ሀሳብ ወደ ጐን ትተው፣ የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች በጣልያን ጥበብ የተገነቡና የጊዜውን ቴክኒዎሎጂ የተከተሉ ስለሆኑ፣ እንደ አማረባቸው ለመቀጠል እንዲችሉ፣ የተለየ የአቶኖሚ ቻርት ተዘጋጅቶላቸው ጣልያንና ኢትዮጵያ ጐን ለጐን ሆነው በጋራ ሥልጣን ያስተዳድሯቸው፣ የሚል ሀሳብ ፈጠሩ። የፈረንሣዮች ዋና ዓላማ ጣልያን ከኤርትራ ጨርሶ እንዳይወጣ በአፀድ ዓይነት ዘዴ በሥልጣን ለማቆራኘት ስለነበረ፣ እንደተመኙት አልተሳካላቸውም።

ለአሥመራና ለምፅዋ ከተሞች የመተዳደሪያ ልዩ ቻርት እንዲሰጣቸው፣ እንግሊዝና አሜሪካኖች ቢስማሙም፣ ጣልያን ከኢትዮጵያ ጋር ደባል አስተዳዳሪ ሆኖ የሥልጣን ወንበር እንዲካፈል አላሰቡም። ጉዳዩ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ፣ የፈረንሣይ መልዕክተኞች መሪ ኩቭ ደ ሙርቪል (COUVE DE MURVILLES) ረቡዕ ግንቦት 4 ቀን 1949 ዓ.ም ከአኩለ ቀን በኋላ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በዋናው ኮሚሲዮን ላይ መግለጫ ለመስጠት ጠይቆ፣ በጉባኤው አጀንዳ ላይ የመመዝገቡ ዜና መጣ። በዚህ ጊዜ ፈረንሣይ ምን ዓይነት አቋም ይዛ ይሆን ? በማለት አሜሪካኖችና እንግሊዞች በተለይም የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ከፍ ያለ ስሜት አድሮባቸው ሰዓቱ እስኪደርስ በጥድፊያ ይጠባበቁ ነበር።

አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ከመልዕክተኞቻቸው ጋር ወዲያውኑ ስብሰባ አድርገው፣ ከ ኩቭ ደ ሙርቪል ንግግር በኋላ፣ በኢትዮጵያ በኩል ስለሚወሰደው እርምጃ መወያየት ጀመሩ። « ..... ኩቭ ደ ሙርቪል መግለጫ ለመስጠት የጠየቀው፣ የመንግሥቱ የፖሊሲ ለውጥ ቢኖር ነው እንጂ፣ ያንኑ ጣልያንን ለመደገፍ በየጊዜው የሚናገረውን ለመድገም አይመስለኝም። በጣልያን ኮሎኒዎች ጉዳይ በተለይ ኤርትራን በሚመለከት፣ ሮበርት ሹማን (ROBERT SCHUMAN) የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሆነ በኋላ አንዳንድ ለውጥ አይተናል። ኩቭ ደ ሙርቪልን ሁለት ጊዜ አነጋግሬው ደህና አስተያየት ሰጥቶኛል። ጨዋነትና እርጋታ የሚታይበትና የኢትዮጵያንም ችግር በቅን አስተያየት የሚመለከት ሰው መሆኑን ከዚህ ቀደም ለጃንሆይ ነግሬአለሁ። እንግዲህ ኩቭ ደ ሙርቪል ለጉባኤው ንግግር ለማድረግ ቀደም ብሎ የጠየቀው፣ ከእንግሊዝ መንግሥት የቀረበውን ረቂቅ ውሳኔ ለመደገፍ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል ? ..... የፈረንሣይ መልዕክተኛ የእንግሊዞችን ሀሳብ እደግፋለሁ ካለ፣ ጣልያኖች ወደ ኤርትራ መመለስ የለባቸውም ብለው፣ ፈረንሣዮች ቆርጠዋል ማለት ነው። ይህ በሆነ ጊዜ የላቲን አሜሪካ አገሮችም ለጣልያን ማጨብጨባቸውን ስለሚያቆሙ፣ የኤርትራ ጉዳይ በቀላሉ በዋናው ኮሚሲዮን ተደግፎ ወደ ጠቅላላው ጉባኤ ሊቀርብ ይችላል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኩቭ ደ ሙርቪል ከእንግሊዞች የቀረበውን ረቂቅ ውሳኔ መቃወሙን ከገለጸ፣

ኢትዮጵያ በከፊልም ቢሆን ትደሰትበታለች ተብሎ የሚጠበቀው ተስፋ ሊደከም ይችላል:: ..... ስለዚህ የኩቭ ደ ሙርቪል ንግግር ኢትዮጵያን የሚረዳ ሆኖ ቢገኝ፣ ወይም ባልጠበቅነው መንገድ የሚጐዳን ቢሆን፣ ምን መልስ መስጠት እንደሚያስፈልግ የእያንዳንዳችሁን አስተያየት ማግኘት ይጠቅመኛል::» በማለት፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ለሥራ ጓደኞቻቸው ጥያቄ አቀረቡ::

<u>ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን</u>:- « ..... ከአራት ሳምንት በፊት የኤርትራ ግዛት ከምዕራባዊው ቆላ በስተቀር ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል፣ የእንግሊዝ መልዕክተኛ ባቀረበው ሀሳብ ውስጥ፣ ሉማሌም በጣልያን ሞግዚትነት እንድትተዳደር ያስፈልጋል በማለቱ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኛ አዝኖ መቃወሙን የሚገልጽ ንግግር ማድረጉን እናስታውሳለን:: ከዚሁ ሁኔታ የተነሣ የእንግሊዝ መልዕክተኞች ያደረባቸው ቅሬታ እስከአሁን ጨርሶ የተሻሻለ አልመሰለኝም:: አሁን የፈረንሣዩ መልዕክተኛ በእንግሊዝ የቀረበውን ሀሳብ መደገፉን ቢያስታውቅ፣ ኢትዮጵያ አመሥጋኝ ሆና የቀረበች ጊዜ፣ ትዝብት ላይ ስለሚጥላት ነገሩን በዝምታ ማለፉ ይሻላል:: ይህንን የምለው፣ እንግሊዝ ሲያቀርበው ተቃውመን፣ ፈረንሣይ ሲደግፈው ተደስተናል፣ ማለቱ ተገቢ ስላልመሰለኝ ነው:: ነገር ግን ሚስተር ኩቭ ደ ሙርቪል የሚሰጠው መግለጫ የኛን ጉዳይ ለመቃወም ከሆነ፣ ኢትዮጵያ ወዲያውኑ ተነስታ በፈረንሣይ ላይ ያላትን ቅሬታ አምርራ ብትገልጽ፣ የእንግሊዞችንና የአሜሪካኖችን መልካም አስተያየት እናገኛለን ...... » የሚል ሀሳብ አቀረቡ::

<u>አቶ ተስፋዬ ተገኝ</u> :- በፓሪስ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር በመሆናቸው፣ በፈረንሣይና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት በወዳጅነት መንፈስ መጠንከር አለበት ብለው ያምናሉ:: አቶ አክሊሉ ላቀረቡት ጥያቄ አስተያየታቸውን ሲሰጡ፣ « ..... ኩቭ ደ ሙርቪል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፖለቲካ ዋና ዲሬክተር በመሆኑ፣ እኔም ብዙ ጊዜ አነጋግሬው ስለ ኢትዮጵያ ጥሩ የሚያስብ ሆኖ አይቼዋለሁ:: ለጉባኤው በሚያደርገው ንግግር የኤርትራን ጉዳይ እንደሚደግፍ ሙሉ እምነት አለኝ:: ክቡር ብላታ ኤፍሬም እንዳሉት ድጋፉን ስናገኝ፣ በዝምታ ካለፍነው ቅሬታ ሊያድርበት ይችላል:: በጠቅላላው ከፈረንሣዮች ጋር ያሉን ግንኙነቶች፣ በጅቡቲውም ሆነ በባቡሩ ጉዳይ ስፊ ስለሆኑ፣ በእኛ በኩል መልካም ወዳጅነታችንን ማሳየቱ እንደሚጠቅመን ማሰብ አለብን:: ስለዚህ የፈረንሣይ መልዕክተኛ ዛሬ በሚያደርገው ንግግር ከደገፈን ማመስገን አለብን እላለሁ:: የኤርትራን ጉዳይ የሚቃወም ከሆነ ግን እኛም ቅሬታችንን እንዲያውቀው መልስ መስጠት ያስፈልጋል ...... » አሉ::

<u>አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ</u> :- « ..... ፈረንሣይ ከወዳጁ ከጣልያን ተለይቶ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ሀሳብ ያቀርባል ብዬ በበኩሌ ተስፋ አላደርግም:: ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የፖለቲካን ጉዳይ መተንበይ ስለሚያዳግት፣ ከፈረንሣዩ መግለጫ በኋላ ክቡር አቶ አክሊሉ የሚሰጡት መልስ፣ በሁለት መልክ እንዲታሰብበት የተባለውን እኔም እስማማለሁ:: ኩቭ ደ ሙርቪል የኤርትራን ጉዳይ ከደገፈ ሳይበዛ በመጠኑ ቢመሰገን አይከፋም:: ይህንንም የምለው በክቡር ብላታ ኤፍሬምና በክቡር አቶ ተስፋዬ ለቀረቡት ሀሳቦች አስታራቂ ለመሆን ነው:: በስተቀረ ሙሴ ኩቭ ደ ሙርቪል እንደተለመደው የጣልያን ሀሳብ ደጋፊ ሆኖ ከቀረበ፣ ክቡር አቶ አክሊሉ ኢትዮጵያ ያዘነች መሆኗን አጠንክረው ቢመልሱለት የተገባ ነው ...... » ሲሉ አሳሰቡ::

ልጅ እምሩ ዘለቀ :- ኩቭ ደ ሙርቪል በሚሰጠው መግለጫ የኤርትራን ጉዳይ በመቃወም የጣልያን ደጋፊነቱን ካስታወቀ፤ በእኛ በኩል ፈረንሣዮችን እልካቸው ለመንገር ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ ጊዜ አይኖረንም:: ...... የዛሬ አሥራ አራት ዓመት ከሙሶሊኒ ጋር ወታደር አዝምተው ባይወጉንም፣ የፋሽስቱ መሪ ደጋፊዎች ሆነው አጥቅተውናል:: ዛሬም ከጠላታችን ጋር ተባብረው ኤርትራን እንድናጣ የጀመሩትን ጥረት እንደሚቀጥሉ ካስታወቁን፡ ክቡርነትዎ የሚሰጠው መልስ ባለፉት ሶስት ሳምንታት ለጣልያኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለኮምት ስፎርሳ ከተነገረው የሚያንስ መሆን የለበትም:: ነገሩ እስከዚህ ሳይደርስ፤ ለኤርትራ የቀረበውን ረቂቅ ውሳኔ የሚደግፍ ሆኖ ከተገኘ አቶ ሀዲስ እንዳለው መጠነኛ ምስጋና ቢሰጠው አይከፋም:: ....... »

አቶ አክሊሉ ከእያንዳንዱ መልዕክተኛ የቀረበውን ሀሳብ ሲያጠኑ ከብላታ ኤፍሬም የተሰነዘረው አንድ አስተያየት፣ ስሜታቸውን የነካ መሆኑን አልሸሸጉም:: ይኸውም፣ የሚያዝያ 7 ቀን የኤርትራን በሁለት መከፈል እንግሊዞች ሲያቀርቡት አለመደሰታችንን ገልጸን፣ አሁን ይህንኑ ሀሳብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ፈረንሣዮች ሲደግፉት ምሥጋና ብናቀርብ ትዝብት ላይ ይጥለናል ያሉት ነው:: በጠቅላላው የኢትዮጵያ መልዕክተኞች አስተያየት ሲታይ፡ የፈረንሣይ መንግሥት የኤርትራን ጉዳይ ቢደግፍ ምሥጋና ይቅረብለት ከሚለው ይልቅ፤ የተቃወመ እንደሆነ ተገቢው መልስ እንደሚገባው ሁሉም ተስማምቷል:: እንግዲህ ማናቸውንም እርምጃ ለመውሰድ መጀመሪያ የኩቭ ደ ሙርቪልን ዲስኩር ማዳመጥ አስፈላጊ ነበር::

ረቡዕ ግንቦት 4 ቀን 1949 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በዘጠኝ ሰዓት (3.P.M) የፈረንሣይ መልዕክተኞች መሪ አስተያየቱን ለመግለጽ ድምፅ ማጉሊያው ሲከፈትለት፤ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የኢትዮጵያና የእንግሊዝ መልዕክተኞች በየጠረጴዛዎቻቸው ላይ ማስታወሻዎቻቸውን ዘርግተው መጠበቅ ጀመሩ::

« ...... ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ከታላቋ ብሪታንያ የቀረበውን ረቂቅ ውሳኔ የፈረንሣይ መንግሥት በጥልቅ ከመረመረ በኋላ ለጠቅላላው ጉዳይ ትክክለኛ መፍትሔ ባለመሆኑ ድጋፉን ለመስጠት አይችልም ..... » በሚል ቃል ንግግሩን ሲከፍት፤ በኢትዮጵያ መልዕክተኞች ገጽ ላይ የሚነበበው ብስጭት በሌሎቹም በእንግሊዝና በአሜሪካኖቹም በኩል የሚታየው ቅሬታ ቀላል አልነበረም:: የፈረንሣይ መልዕክተኛ ንግግሩን በመቀጠል « ....... የእነዚህን ቅኝ ግዛቶች የወደፊት ዕድል ለመወሰን የሚያስችለው፣ መጀመሪያ የየአገሩ ነዋሪ ሕዝብ ፍላጐቱ ምን እንደሆነ ተጠይቆ ሲታወቅ፣ ሁለተኛ የሚደረገው ውሳኔ ለአካባቢው የሚያስፈልገውን ሠላም የሚያረጋግጥ መሆኑ ሲታመንበት፣ ሶስተኛ የጣልያን መንግሥት በየአገሩ ላይ ያለው ጥቅም በትክክል የሚጠብቅለት ሲሆን ብቻ ነው...... » አለ::

እንግሊዞች ለሊቢያ፣ ለሱማሌና ለኤርትራ ካቀረቡት ሀሳብ ውስጥ፤ ኩቭ ደ ሙርቪል በጣም ጥሩ ነው ብሎ የደገፈው፤ ሱማሌ በጣልያን ሞግዚትነት ቢያንስ ለአሥር ዓመታት እንድትተዳደር የተባለውን ብቻ ነው:: ኢትዮጵያ በምትጠብቀው ጉዳይ ላይ ግን፣ የፈረንሣይ መንግሥት አቋም ከጣልያን ጋር የተባበረ መሆኑን ኩቭ ደ ሙርቪል ደህና አድርጐ አስረዳ:: « ..... ስለ ኤርትራ ጉዳይ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የቀረበው መፍትሔ በአገሩ ላይ ያለውን ችግር በትክክል የሚፈታ ስለአልሆነ፣ ልንደግፈው አንችልም:: ቀደም ብለን ደጋግመን



*«.. በኤርትራ ጉዳይ፣ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለጣሊያንም ጥቅም መታሰብ አለበት.... »*

( ኩቭ ደ ሙርቪል የፈረንሣይ መልዕክተኛ)

(ግንቦት 1949) (ፎቶ U.N)

እንደአስረዳነው ሁሉ፣ መጀመሪያ የኤርትራ ሕዝብ ምርጫው ምን እንደሆነ ተመርምሮ አልታወቀም:: ሁለተኛ ለኢትዮጵያ ጥቅም ብቻ ሲታሰብ፣ የጣልያንን መንግሥት መብት ለመጠበቅ፣ በአገሩ ላይ ለተወለዱት ዜጎቹ የመኖሪያ ዋስትና ለመስጠት ብቻ መታሰቡን፣ በቂ ሆኖ አላገኘነውም:: ...... » ሲል የፈረንሣይ መልዕክተኛ የተቃዋሚ አስተያየቱን አጠነከረ:: በጠቅላላው የታላቋ ብሪታንያ ሬዞሉሽን ምንም እንኳን ስለ ሱማሌ ጉዳይ ያቀረበው ሀሳብ ተገቢ ቢሆንም፣ የሊቢያንና የኤርትራን ጉዳይ በአንድነት አጠቃልሉ፣ በአንድ መልክ የሚፈታ ሆኖ ባለመገኘቱ ፣ የፈረንሣይ መንግሥት ድጋፉን አይሰጥም ሲል፣ ሞሪስ ኩቭ ደ ሙርቪል ዲስኩሩን አከተመ::

ይህ ግንቦት 4 ቀን 1949 ዓ.ም ከፈረንሣይ መንግሥት የቀረበው አስተያየት እንግሎ አሜሪካኖችን ቅር ያሰኘ፣ በተለይ የኢትዮጵያን መልዕክተኞች ደግሞ በጣም ያሳዘነ ቢሆንም፣ የጣልያንን መንግሥትና ወገኖቹን የላቲን አሜሪካ አገሮችን እጅግ ማስደሰቱ አላጠራጠረም::

በፈረንሣይ ካልቸር በማደግ ፈረንሣዊ ስሜት ያላቸው የሚባሉት አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ አገራቸውን በሚመለከት ጉዳይ ፈረንሣይ መንግሥት የቀረበው ሀሳብ እጅግ አበሳጭቷቸዋል:: -- ኩቭ ደ ሙርቪል እርጋታና ጨዋነት የሚታይበት ነው እያሉ፤ በራፖራቸው ያመሰገኑትን ሰው፣ ሀሳቡን መቃወም ብቻ ሳይሆን የሰጠውንም አስተየየት በሙሉ ማራከስ አስፈላጊ ነው ብለው ተነሱ::

« ...... ኢትዮጵያ፤ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች እንዲገነዘቡላት የምትጠይቀው በፈረንሣይ መልዕክተኛ በቀረቡት አስተያየቶች እጅግ አድርጋ ያዘነች መሆኗን ነው:: ..... የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ለነበሩት አገሮች፣ የሁሉንም የወደፊት ዕድል በአንድነት ለመወሰን ተመሳሳይ መፍትሔ መገኘት አለበት ሲል፣ የፈረንሣይ መልዕክተኛ የተናገረው፣ ትክክለኛ ትርጉሙ ምን ለማለት እንደሆነ አላብራራልንም:: የኤርትራ፣ የሊቢያና የሱማሌ ሕዝቦች የእያንዳንዳቸው ታሪክና ባሕል፣ የእያንዳንዳቸው የሕይወት ፕሮብሌም፣ የእያንዳንዳቸው የጂኦግራፊ አቀማመጥ የተለያየና አንደኛው ከሌላው የተራራቀ ስለሆኑ፣ የሶስቱም የወደፊት ዕድል በአንድ ዓይነት መልክ ታይቶ በአንድ ዓይነት መልክ ሊወሰን አይችልም:: ...... እርግጥ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለሶስቱም አገሮች ተመሳሳይ የሆነ አንድ ውሳኔ መስጠት ያለበት ከፍተኛ ጉዳይ አለ:: ይኸውም፣ ሶስቱም አገሮች የጣልያን አስተዳደር ተመልሶ እንዳይወድቅባቸው እጣቱታቸውን በሰፊው ስለአቀረቡ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኮሎኒያሊስት ጣልያን በምንም ዓይነት መልክ እንዳይመለስባቸው መወሰን አለበት::

...... የፈረንሣይ መልዕክተኛ በሁለተኛው ነጥቡ ላይ የገለጸልን አስተያየት፣ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት በቀረበው ረቂቅ ውሳኔ፣ በኤርትራ ጉዳይ ለኢትዮጵያ ብዙ ሲታሰብ፣ ለጣልያን ጠቃሚ የሆነ ነገር አልታቀደም:: ከሁሉ በፊት የኤርትራ ሕዝብ ምርጫው ምን እንደሆነ ተጠይቆ መታወቅ አለበት ብሎናል:: ሱማሌ ግን ተመልሳ በጣልያን ሞግዚትነት እንድትተዳደር የቀረበውን ሀሳብ የፈረንሣይ መልዕክተኛ ተገቢ ነው ብሎ ሲደግፍ፣ የሱማሌ ሕዝብ ፍላጐቱ ምን እንደሆነ እንዲጠየቅ አስፈላጊ ሆኖ አልታየውም:: የኤርትራ ሕዝብ ወደ ጥንት ታሪኩና ወደ ጥንት አገሩ ወደ ኢትዮጵያ ይቀላቀል ከተባለ፣ በፈረንሣይ አስተያየት የሕዝቡ ፈቃድ እየተደጋገመ እንዲጠየቅ ያስፈልጋል ማለት ነው:: ...... ይህንን ከፈረንሣይ መልዕክተኛ የቀረበውን ሀሳብ፣ የጣልያን የውጭ ጉዳይ

ሚኒስትር ኩምት ስፎርሳ ዛሬ በመካከላችን (በታዛቢነት) ተገኝቶ ቢሰማው ኖሮ፣ ምን ያህል በፈነደቀ ነበር ? አዲሲቷ የተባለችው ጣልያን ይህንን የመሰለ ከፍተኛ እርዳታ ከፈረንሣይ ካልሆነ በስተቀር፣ ከማንም ታላላቅ መንግሥታት ልታገኝ አትችልም።

..... ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ የፈረንሣይ መንግሥት በሰፊው ሲከራከር የቆየው፣ አዲሲቷ ለተባለችው ጣልያን የቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶቿ በሙሉ እንዲመለሱላት መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የኃያላን አገሮች የውጭ ጉዳይ መማክርቶች ያስታውሳሉ። ዛሬም አቀራረቡን ለማሻሻል ይሞክራል እንጂ ግቡ አልተለወጠም። ..... ዘለፋ መስሎ እንዳይገመትብኝ አስቀድሜ ይቅርታ እየጠየኩ፣ የፈረንሣይ መልዕክተኛ ንግግር በአንድ በኩል ለሕዝብ መብት ተቆርቋሪ ለመምሰል እየሞከረ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጣልያን ነገረፈጅ እየሆነ ስለሚሟገት፣ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች በዚህ ዓይነት የተወሳሰበውን ሀሳብ በምን አኳኋን እንደሚፈቱት ለመገመት እቸገራለሁ። ...... በኢትዮጵያ መልዕክተኞች አስተያየት ግን፣ ይህ ከፈረንሣይ የተሰጠው መግለጫ የሚያሳየው፣ ከታላቋ ብሪታንያ የቀረበው ረቂቅ ውሳኔ እንዳይጸድቅ፣ በጣልያን ስም ለማስናከል ስለሆነ፣ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች በጥልቅ እንዲረዱት ያስፈልጋል። ..... የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ያቀረበው ሬዞሉሽን፣ የኢትዮጵያን ጥያቄ የሚያሟላ አለመሆኑን ከዚህ ቀደም ደጋግመን አስረድተናል። ሆኖም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ያጋጠመውን ችግር ለመፍታት ለጊዜው ሌላ መንገድ ስለጠፋ፣ ኤርትራን በሚመለከት ጉዳይ እኛም ድጋፋችንን ለመስጠት ቃል ሰጥተናል። ..... ስለዚህ፣ ድርጅታችን ያለበትን ከፍተኛ ኃላፊነት በክብርና በወግ ለመፈጸም፣ ከታላቋ ብሪታንያ የቀረበለትን ረቂቅ ውሳኔ እንዲያጸድቅ የኢትዮጵያ መልዕክተኛ አጥብቆ ያሳስባል። ...... »

ፍሬ ነገሩ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ለጉባኤው ማስረዳት የፈለጉት፣ ሞሪስ ኩቭ ደ ሙርቪል ያደረገው ንግግር ዓይኑን ጨፍኖ የጣልያንን መንግሥት ለመርዳት ብቻ መሆኑን ነው። ያልታደለች ኢትዮጵያ ፋሺስት ባጠቃትም ጊዜ ሆነ፣ ከዚያም ወዲህ ከጥንት ወዳጇ ከፈረንሣይ መንግሥት ጥቃት በስተቀር ድጋፍ ልታገኝ አልቻለችም። በዚህ በግንቦት 4 ቀን 1949 ዓ.ም ከፈረንሣይ በተሰጠው መግለጫ ከሁሉም ይልቅ አቶ አክሊሉን በጣም ያሳዘናቸው፣ «..... በኤርትራ ጉዳይ ለኢትዮጵያ ብዙ ሲታሰብ የጣልያን ጥቅም የሚጠበቅበት መንገድ አልተዘጋጀም። ..... » በማለት፣ የቀረበው ስሞታ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ኤርትራ ለጣልያን የማትመለስ ከሆነ፣ ወደ ኢትዮጵያ እንድትቀላቀል ከመወሰኑ በፊት፣ የሕዝቡ ፈቃድ መጠየቅ አለበት የተባለው አደናቃፊ ሀሳብ ነው። እንግዲህ ይህ ምን ማለት ነው ? ..... የቀድሞዎቹ ሶስቱም ቅኝ ግዛቶች ተመልሰው ለጣልያን እንዲሰጡ ከተደረገ፣ የየአገሩ ሕዝብ ትቀበላለህ? ወይስ ትቃወማለህ ? ተብሎ እንዲጠየቅ አያስፈልግም። ነገር ግን የኤርትራ ሕዝብ ወደ ጥንት አገሩ ወደ ኢትዮጵያ ይቀሳቀል ከተባለ፣ በፈረንሣይ አስተያየት የሕዝቡ ፍላጎት በድጋሚ እንዲጠየቅ ያስፈልጋል ማለት ነው። የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን በሰጠው ራፖር፣ ከምዕራባዊው ቆላ አውራጃዎች ሕዝብ በስተቀር፣ ሌላው ከመቶ ሰባ አምስቱ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል የገለጸውን ስሜት የኮሚሲዮኑ አባል ከሆነው ከፈረንሣይ ሌላ ማን ሊያስታውሰው ይችላል ? ..... እንግዲህ፣ የፈረንሣይ መንግሥት ትናንት ተስማምቶበት የነበረውን ሀሳብ ዛሬ ለውጦ፣ የኤርትራ ሕዝብ እንደገና አስተያየቱን እንዲሰጥ ያስፈልጋል የሚልበት ምክንያት ምን ይሆን ? ተብሎ ቢጠየቅ፣ ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ በተሰጠው መግለጫ

እንደተነገረው፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከታላቋ ብሪታንያ የቀረበውን ረቂቅ ውሳኔ እንዳያጸድቅ ለማጨናገፍና ከላቲን አሜሪካ አገሮች ጋር ተባብሮ ጣልያንን ለመርዳት መሆኑ ጥርጥር የለውም::

## የቤቨንና ስፎርሳ ስምምነት

ለነዚህ ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ መፍትሔ እንዲሆን ሚያዝያ 6 እና 7 ቀን 1949 ዓ.ም አሜሪካና እንግሊዝ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን ላይ ያቀረቡት ሀሳብ፣ በቂ ድጋፍ አግኝቶ ሳይጸድቅ ጊዜ ስለወሰደ፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ሥጋት አደረበት::

ከእንግሎ አሜሪካ የቀረበው ሀሳብ፣ የጣልያንን ወደ ኤርትራ መመለስ የሚያግድ ከመሆኑም በላይ ከምዕራባዊው ቆላ በስተቀር፣ ሌላው የምሥራቁ ክፍል በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል የሚጠይቅ ስለሆነ፣ የሮማ መንግሥት እጅግ አድርጐ ተቀይሞ፣ ይህ ውሳኔ እንዳይጸድቅ በወዳጆቹ በፈረንሣይና በላቲን አሜሪካ አገሮች በኩል ገትሮ ያዘ::

ከሊቢያ የትሪፖሊታንያን አውራጃ፣ ከምሥራቅ አፍሪካ ሱማሌን፤ በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ድጋፍ ቢሰጠውም፣ ከቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶቹ መካከል ዋና የደም ሥሩ አድርጐ የሚቆጥረውን ኤርትራን እንዲያገኝ ባለመደረጉ፣ የጣልያን መንግሥት አልቀበልም አለ:: ሱማሌም ትሪፖሊታንያም ቀርተውበት ኤርትራን ብቻ በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር ቢደረግለት፤ የደጋስፔሪ መንግሥት ለደስታው ወሰን አይኖረውም ነበር:: በዚያን ዘመን ጣልያን ምንም እንኳን ፋሽስት የተባለው ስሟ ተለውጦ አዲስቷ ሬፐብሊክ ብትባልም፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ለመሆን ገና አልተፈቀደላትም:: ነገር ግን የፈረንሣይ መንግሥትና የላቲን አሜሪካ አገሮች የጣልያን ደጋፊዎች ሆነው በብዛት ስለተሰለፉ፤ አሜሪካና እንግሊዝ በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሲዮን ላይ የሚፈልጉትን ለማስወሰን በቂ የድጋፍ ድምፅ ማግኘት አልቻሉም:: ከሚያዝያ 6 ቀን 1949 ዓ.ም እስከ ግንቦት 4 ቀን ድረስ በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሲዮን በተደረጉት የአራት ሳምንት ስብሰባዎች ላይ፣ በእንግሊዝና በአሜሪካ ተደግፎ የቀረበው ሀሳብ እየተጻከመ፤ ጣልያን በእጅ አዙር የሚያደርገው ተቃውሞ እየበረታ መጣ:: በዚህ ላይ ደግሞ የዓረብ አገሮችም፣ የሊቢያን አንድነት ለመጠበቅና ነፃነቷን በፍጥነት ለማስገኘት በሚያደርጉት ጥረት፣ የእስያዎችንና የእስላም አገሮችን ትብብር ለማግኘት ጊዜ አገኙ::

ይህ ሁኔታ እንደዚህ ከቀጠለ፣ ታላቋ ብሪታንያ ለስትራቴጂ በጣም የሚጠቅማትን የሲረናይከን አውራጃ ለአሥር ዓመታት በሞግዚትነት ለማስተዳደር ያላት ጽኑ ምኞት፣ የማይፈጸም መስሎ ታያት:: በዚህ ጊዜ የእንግሊዝ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ባለሞያዎች፣ ከጣልያን መንግሥት ጋር በአስቸኳይ ንግግር ተደርጐ፣ ከአንድ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ በስተቀር፣ ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት የማይቻል መሆኑን አመኑበት:: በዚህ ሀሳብ መሠረት፣ የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኧርነስት ቤቨን (ERNEST BEVIN) እና አዲሲቷ ሬፐብሊክ የተባለችው ጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮምት ስፎርሳ፣ (COMT CARLO

SFORZA) ግንቦት 6 ቀን 1949 ዓ.ም ሎንደን ላይ ተገናኝተው ውይይታቸውን ጀመሩ:: ኧርነስት ቤቨን ለጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሀሳቡን ሲገልጽ፣ በዲፕሎማሲ የተካበ ንግግር ማድረግ አስፈላጊ መስሎ አልታየውም:: የታላቋ ብሪታንያ የግርማዊ ንጉሥ መንግሥት፣ ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች፣ የመጨረሻው መፍትሔ ነው ብሎ የሚያምንበትን ዕቅድና፣ እስከ ዛሬም የጣልያን መንግሥት ሲፈጽም የቆየውን ተቃውሞ ከወቀሳ ጋር ወረወረለት::

« ..... የጣልያን መንግሥት ከቫቲካን ጋር በመተባበር የላቲን አሜሪካ አገሮችን ወገኖቹ አድርጉ በማስለፍ፣ ስለቀድሞዎቹ ቅኝ አገሮች የቀረበው መፍትሔ፤ በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሲዮን እንዳይጸድቅ፣ በሚፈጽመው ተቃውሞና ተንኮል እጅግ አድርጌ አዝኛለሁ:: የጣልያን ጋዜጦችም ከመንግሥታቸው በሚሰጣቸው ድጋፍ፣ በታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ላይ የሚነዙትን አግባብ የሌለው ወቀሳ ተመልክቻለሁ::

...... የግርማዊ ንጉሥ መንግሥት፣ ጣልያን ትሪፖሊታንያንና ሱማሌን በሞግዚትነት ተቀብላ እንድታስተዳድር ድጋፉን በሚገባ አቅርቧል:: ከዚህ ውጭ ግን የጣልያን መንግሥት እንደሚመኘው ወደ ኤርትራ ለመመለስ ምንም አይነት ዕድል የሌለው መሆኑን መገንዘብ አለበት:: የትሪፖሊታንያም ሆነ የሱማሌ ሕዝብ፣ ጣልያን እንዳይመለስበት የገለጸውን ተቃውሞ ችላ ብለን፤ ወይም እንዳልሰማ መስለን፤ የሞግዚትነት አስተዳደሩ እንዲሰጥ የተሟገትነው፣ የአዲሲቷን ሬፑብሊክ መንግሥት ለመርዳት በማሰብ ነበር። ነገር ግን በጣልያን አስተያየት ይህ እርዳታ በቂ ሆኖ ካልተገመተ፣ የግርማዊ ንጉሥ መንግሥት ምንም ማድረግ አይችልም::

....... ስለዚህ፣ ከሰሜን አፍሪካ ትሪፖሊታንያን፣ ከምሥራቅ አፍሪካ ሱማሌን፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኃላፊነት የሞግዚት አስተዳዳሪነት እንዲሰጣችሁ የምንደግፈውን ተቀብላችሁ ለአፈጻጸሙ መጣር አለባችሁ:: ይህንን አንቀበልም የምትሉ ከሆነ፣ ታላቋ ብሪታንያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቀርቦ መፍትሔ ላልተገኘለት ጉዳይ፣ ሌላ ዘዴ በሌላ አቅጣጫ መጠቀም ይኖርባታል ....... »

ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው፤ ኧርነስት ቤቨን ለኮምት ስፎርሳ ያቀረበው ሀሳብ ከዛቻ ጋር የተጣመረ በመሆኑ፣ የጣልያን ዋና ፍላጎት ኤርትራን ነው ብሎ መከራከሩ፣ ምንም እንደማይጠቅም የአዲሲቷ ጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተገነዘበ:: ኮምት ስፎርሳ ከሎንደን ወደ ሮማ ሲመለስ «ኤርትራን አስወስደህ መጣህ» ተብሎ በፋሽስቶች እንዳይወቀስ፤

ሀ/ በኤርትራ የሚኖሩ ጣልያኖች መብታቸውን ለማስከበር በቂ ዋስትና እንዲሰጣቸው፣

ለ/ የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች የብዙዎቹ የጣልያን ዜጋዎች መኖሪያ ስለሆኑ፣ የሚተዳደሩበት የኦቶኖሚ ቻርተር፣ በተባበሩት መንግሥታትና በአዲሲቷ ጣልያን መንግሥት ትብብር እንዲዘጋጅ፣ የታላቋ ብሪታንያን ድጋፍ ጠየቀ::

በዚህ ሀሳብ ላይ ቀደም ሲል እንግሊዝና አሜሪካ ተነጋግረው አንድ የደረሱበት ስምምነት ስለአለ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቤቨን ዝርዝሩ ውስጥ

ሳይገባ፣ በደፈናው የኮምት ስፎርሳን ፍላጐት ስማርካት እስማማለሁ ብሎ ተስፋ ሰጠው:: በመሠረቱ የሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፣ ቤቨን እና ስፎርሳ፣ ሎንዶን ላይ ግንቦት 6 ቀን 1949 ዓ.ም ተገናኝተው በሰፊው ከተወያዩ በኋላ የተስማሙባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ::

1ኛ. <u>የሊቢያ አውራጃዎች ፤</u>

ሀ/ ሲረናይካ፣ በታላቋ ብሪታንያ፤
ለ/ ፌዛን፤ በፈረንሣይ፤
ሐ/ ትሪፖሊታንያ፤ በጣልያን፤

የሞግዚትነት አስተዳደር ለአሥር ዓመታት ከቆዩ በኋላ፣ ሶስቱም አውራጃዎች በአንድነት ተዋህደው የሊቢያ ነፃ መንግሥት ይቋቋማል::

2ኛ. <u>የኤርትራ ግዛት በሁለት ይከፈላል፤</u>

ሀ/ አብዛኛው የክርስቲያኑ ሕዝብ የሚኖርበት የምሥራቁ አውራጃዎች፣ አሥመራ፣ ምፅዋና አሰብ ጭምር ከኢትዮጵያ ጋር ይቀላቀላሉ::

ለ/ በኤርትራ ለተወለዱትና ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ሕይወታቸውን በአገሩ ላይ ለመሠረቱት የጣልያን ዜጐችና ከጣልያን ለተወለዱ ክልሶች፣ መብታቸው እንዲከበር የኢትዮጵያ መንግሥት ዋስትና ይሰጣቸዋል::

ሐ/ የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች የተለየ የአቶኖሚ መተዳደሪያ ቻርት እንዲሰጣቸው ይደረጋል:: ይህም የመተዳደሪያ ቻርት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በጣልያን መንግሥት ሕብረት ሊዘጋጅ ይችላል:: አብዛኛው እስላም የሆነው ሕዝብ የሚኖርበት የኤርትራ የምዕራባዊው ቆላ አውራጃ፣ በሀይማኖቱና በባሕሉ ከሚቀራረበው ከሱዳን ጋር ይዋሀዳል::

3ኛ. <u>የጣልያን ሱማሌ</u>

ለአሥር ዓመታት የጣልያን መንግሥት በሞግዚትነት ካስተዳደረው በኋላ፣ ነፃነቱን ይቀበላል::

ከሚያስፈልግ በላይ ፕሮፓጋንዳ ያቃበጠው ይህ የቤቮንና ስፎርሳ ስምምነት፣ ከዚህ ቀደም በሚያዝያ ወር 1949 ዓ.ም ታላቋ ብሪታንያ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን ካቀረበችው ሀሳብ ጋር ሲተያይ፣ ትሪፖሊታንያ ለጣልያን እንዲሰጥ በግልጽ ከመጠቀሱ በስተቀር፣ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ አይገኝበትም:: ነገር ግን ጉዳዩን እንደ አዲስ የሚያደርገው፣ 1ኛ/ የጣልያን መንግሥት በግዴታም ሆነ በውዴታ የታላቋ ብሪታንያን ሀሳብ አሜን ብሎ መቀበሉ ነው:: 2ኛ/ ደግሞ፣ ለአሥመራና ለምፅዋ ከተሞች የተለየ አቶኖሚ እንዲኖራቸው፣ ቻርቱ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በጣልያን መንግሥት ሕብረት ይሰናዳል የሚለው ቃል ነው::

ይህ ለአሥመራና ለምፅዋ ከተሞች የተለየ አስተዳደር ይመሠረታል ተብሎ በመጨረሻ የተደነቀረው ሀሳብ፣ የኢትዮጵያን ክብር የሚነካ በመሆኑ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት በብርቱ እንደሚቃወመው ኧርነስት ቤቨን እና የውጭ ጉዳይ ረዳቶቹ ደህና አድርገው ያውቃሉ:: ከዚህም በቀር ገና ከመጀመሪያው ኤርትራን በሁለት የሚከፍል ሀሳብ በቀረበ ጊዜ፤ ኢትዮጵያ ለመስማማት ከባድ ችግር እንደገጠማት የእንግሊዝ መንግሥት ያስታውሳል:: ለአሥመራና ለምፅዋ ከተሞች ስለሚታሰበው የኦቶኖሚ ቻርት ጉዳይ፤ እነ ኮምት ስፎርሳ ጣልያን የአስተዳደሩን ሥልጣን ታገኛለች ብለው ቢፎልሉም፣ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን ላይ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ፣ የኢትዮጵያን ነፃነትና ክብር የሚነካ ይሆን የመሰለ ውሳኔ፣ አባል መንግሥታቶቹ ላይቀበሉት ይችላሉ ብለው የታላቋ ብሪታንያ ዲፕሎማቶች ገምተው ነበር::

በጠቅላላው በኤርትራ ጉዳይ ለኢትዮጵያ ጥሩ ዕድል የሚኖራት አገሩ በሁለት ሲከፈል ብቻ ነው ብለው እንግሊዝና አሜሪካ በብርቱ አምነውበታል:: በዚህ ሀሳብ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ደጋግሞ በማስረዳት እንዲያሳምናቸውና፣ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ በሀሳብ እያፌነገጠ የሚያስቸግረው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ከታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች ጋር እየተመካከረ እንዲሠራ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ እንዲሰጡ፤ አዲስ አበባ ያለው የታላቋ ብሪታንያ አምባሳደር አደራ ተባለ:: የቤቨንና ስፎርሳ ስምምነቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ፣ ነጥብ በነጥብ የሚወስደውን እርምጃ የእንግሊዝ የዲፕሎማሲ ኤክስፐርቶች፤ ኮምት ስፎርሳ ወደ ሮማ ከመመለሱ በፊት አዘጋጅተው ዝርዝር ፕሮግራም አቅርበዋል::

1. ስለ ቤቨን ስፎርሳ የሎንዶን ንግግር፣ ለጋዜጠኞች የሚሰጠው መግለጫ፣ በደፈናው « ..... በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሲዮን ቀርቦ ንግግር የሚደረግበት የቀድሞዎቹ የጣልያን ኰሎኒዎች ጉዳይ በቶሎ ፍጻሜ እንዲያገኝ፤ አብዛኛዎቹ አባሎች የሚደግፉትን መፍትሔ የሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ለመቀበል ተስማሙ .... » የሚል ሆኖ፣ በዚሁ መንፈስ እንዲቆምና ዝርዝሩ በምሥጢር ተይዞ እንዲቆይ፣

2. የጣልያን መንግሥት ደጋፊዎቹን የላቲን አሜሪካ አገሮችና የፈረንሣይን መንግሥት በቶሎ አነጋግሮ፣ በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሲዮን ላይ፤ ከታላቋ ብሪታንያ የሚቀርበውን የውሳኔ ሀሳብ እንዲደግፉ ማድረግ፣

3. የጣልያን መንግሥት ከአንዳንድ የዓረብ አገሮች ጋር ወዳጅነት ዘርግቶ፣ ለቀረበው ሀሳብ፤ የዓረቦችን ተቃዋሚነት ለማብረድ እንዲጥር፤ የሚል ነበር::

እነዚህን ከእንግሊዝ የዲፕሎማሲ ሊቃውንቶች የተሰጡትን ማሳሰቢያዎች የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና ረዳቶቹ፣ ለማዳመጥ አልፈለጉም:: ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል እንደሚባለው፣ የሰባ ሰባቱ ዓመት ሽማግሌ በሩጫ ሎንዶን ሄዶ፣ ከታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማሲ መሪ የተሰጠውን ሀሳብ፤ በሩጫ ተቀብሎ ሮማ ሲመለስ፣ ያደረገው ስምምነት ምሥጢርነቱ እስከምን ድረስ ተጠብቆ መቆየት እንዳለበት በትክክል አልተረዳም:: ከሮማ አውሮፕላን ጣቢያ ጀምሮ ለከበቡት ጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ፣ « ትሪፖሊታንያንና ሱማሌን ለጣልያን ለመመለስ ከታላቋ ብሪታንያ ጋር ስምምነት ተደረገ » የሚል በእንግሊዞች በኩል

ያልተጠበቀ አጉል ቦንብ አፈነዳ:: ጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪ እና ብዙዎቹ ሚኒስትሮቹ፣ የቤቪንና የስፎርሳ ስምምነት የጣልያንን ወደ ኤርትራ የመመለስ ዕድል በመዝጋቱ ማዘናቸውን ሲገልጹ፣ ኮምት ስፎርሳ ለዚህም ማካካሻ ሌላ ዘዴ ተገኝቷል አለ:: « ..... የጣልያን ዜጐች በብዛት የሚኖሩባቸው የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በጣልያን ሕብረት ልዩ የመተዳደሪያ ቻርት ተዘጋጅቶላቸው፣ አስተዳዳሪዎቹም ጣልያኖች እንዲሆኑ ተስማምተናል:: ...... » የሚል ከእውነተኛው መስመር የራቀ የፕሮፓጋንዳ ዲስኩር አደረገ::

የጣልያን የፖለቲካ መሪዎችና ሕዝቡ፤ ከትሪፖሊታንያና ከሱማሌ ይልቅ፣ ኤርትራን ማግኘት እንደሚመርጡ፣ ኮምት ስፎርሳ ስለሚያውቅ፣ የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች በጣልያኖች እንዲተዳደሩ ተስማምቼ መጣሁ ማለቱ፣ የውስጡን ችግር ለማዳከምና ሠላም ለማግኘት ይረዳኛል ብሎ ነው:: ነገር ግን፣ በጣም አሳዛኝ ሆኖ የብዙዎቹን አገሮች መንፈስ በቁጣ የቀሰቀሰው፣ የጣልያን መንግሥት ወደ ሊቢያና ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በራዲዮ የሚያስተላልፈው ፋሽስታዊ ፕሮፓጋንዳ ነበር:: « .... አዲሲቷ ሬፑብሊክ ትሪፖሊታንያን እና ሱማሌን አስመለሰች:: ..... ከኤርትራም የጣልያን ከተሞች የሆኑትን አሥመራንና ምፅዋን ለማስተዳደር ጣልያን ተጠየቀች:: .... በትሪፖሊታንያ፣ በሱማሌና በኤርትራ ለብዙ ዘመናት የአስተዳደሩ የሥራ ልምድ ያላቸው የጣልያን ዜጐች ሁሉ በቅርቡ በየሥራ መስካቸው ይመደባሉ:: ...... » የሚል ፕሮፓጋንዳ በየአገሩ ቋንቋ ከሮማ ይሠራጭ ጀመር:: ይህ ሁሉ የሆነው የቤቨን ስፎርሳን ስምምነት ያዘለው ረቂቅ ውሳኔ፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በዋናው ኮሚሲዮን ከተመረመረ በኋላ ወደ ጠቅላላው ጉባኤ ቀርቦ ከመታየቱ በፊት ነበር:: በዚህ ዓይነት የተሠራጨው ፕሮፓጋንዳ፤ በኒውዮርክ የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት ንግግር በሚደረግበት ሰዓት፣ ምን ያህል ጉዳት እንደሚያስከትል የጣልያን የፖለቲካ መሪዎች አርቀው አልተመለከቱም::

-- የዓረብ አገሮች በግብፅ ግንባር ቀደምትነት አንድ ዓይነት ሕብረት መሥርተው፣ የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት የሊቢያን አንድነት የሚያፈርስና፣ የትሪፖሊታንያን ሕዝብ ለጣልያን አሳልፎ የሚሰጥ ስለሆነ፤ ተቃውሞአቸውን ለማጠንከር የእስላም አገሮችን፤ እንዲሁም የአፍሪካውያንና የእስያውያንን እርዳታ ጠየቁ::

-- መስኮብና አጃቢዎቹ፣ የምዕራባውያን ካፒታሊስቶችና ኰሎኒያሊስቶች በተባበሩት መንግሥታት ጀርባ እየተማከሩ፣ የድሆች አገሮችን ነፃነትና መብት በመግፈፍ፣ የየራሳቸውን ጥቅም ለማዳበር የሚፈጽሙት ግፍ እንዴት እንደሆነ፤ ከቤቨንና ስፎርሳ ስምምነት የበለጠ ምን ማስረጃ ያስፈልጋችኋል ? ...... እያሉ፣ ታናናሽ አገሮችን በዚህ ሀሳብ ማርኮ ተቃዋሚ ለማድረግ ዝግጅታቸውን ቀጠሉ:: አንዳንዶቹም የአውሮፓ አገሮችና በተለይም ፈረንሣይ፣ ቤቨንና ስፎርሳ ላደረጉት ስምምነት ያልመከሩበት፤ ወይም የየግል አስተያየታቸውን ያልሰጡበት በመሆኑ ቅሬታ አሰምተዋል::

ከዚህ በላይ እንደታየው ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች የወደፊት ሕይወት መፍትሔ ለመስጠት፣ ቤቨንና ስፎርሳ ሎንዶን ላይ የጐነጐኑት ስምምነት፣ የሊቢያ፣ የኤርትራና የሱማሌ ሕዝብ ይደስታል ወይስ ያዝናል ?

ይቀበላል ወይስ ይቃወማል ? ብለው አልተጨነቁም:: ለጉዳዩ መፍትሔ የተፈለገውም ለእነርሱ በሚጠቅም ጉዳና ተጠንቶ እንጂ፣ ለተጨቆኑት ሕዝቦች ታስቦ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ታላቋ ብሪታንያ፣ ለምዕራባውያኖች የጦር ዝግጅት በጣም ጠቃሚ ቦታ የሆነውን ሲረናይከን ለአሥር ዓመታት በሞግዚትነት ማስተዳደር አጥብቃ ትፈልጋለች:: የጣልያን፣ መንግሥት በግራ በኩል ከሚኒስቶችን፣ በቀኝ በኩል የኒዎፋሽስቶችን እየተዋጋ፣ ከምዕራባውያን ጋር ለመሰለፍና የአትላንቲክ ፓክት አባል ለመሆን እንዲችል፣ ከሊቢያ ትሪፖሊታንያን፣ ከምሥራቅ አፍሪካ ሱማሌን፣ በሞግዚትነት መረከብ ይገባዋል ተብሎ ታምኖበታል:: ፈረንሣይ፣ ምንም እንኳን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዘመን ያደረገችው ተጋድሎ ከሌሎቹ ኃያላኖች ጋር የሚለካ ባይሆንም፣ በሰሜን አፍሪካ ያሏትን ቅኝ ግዛቶቿን ሊቢያ ላይ የሚተራመሰው የነፃነት እንቅስቃሴ እንዳያደፈርስባት፣ የፌዘንን አውራጃ በሞግዚትነት እንድታስተዳድር ታስቦላታል::

በዚህ ጥንስስ ውስጥ ኢትዮጵያ፣ የፋሽስት ጥቃት የደረሰባት አገር በመሆኗ እንድትካስ ያስፈልጋል በሚል አስተያየት ከኤርትራ ግዛት አብዛኛው ክፍል ሊሰጣት ይገባል ተባለ:: ኢትዮጵያ ግን የኤርትራን ጥያቄ ያቀረበችው በፋሽስት ለደረሰባት ግፍ ካሣ ይገባኛል ብላ አልነበረም:: ለኢትዮጵያ ካሣ እንዲሆን ኤርትራን ማግኘት ይገባታል እያሉ ለሚናገሩት አገሮች አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ደጋግመው ሲያስረዱ፣ « ... በግፍ የጦር ጥቃት የደረሰበትን አገር ለመካስ፣ ተጨማሪ ግዛት እንዲሰጠው ያስፈልጋል የሚል የተባበሩት መንግሥታት ሕግ የለም:: ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታትን ፍርድ የጠየቀችው ኮሎኒያሊስት ጣልያን የወሰደባት አገር እንዲመለስላት ብቻ ነው ...... » ብለው ነበር::

በቤቨን ስፎርሳ ስምምነት መሠረት፣ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን በእንግሊዞች ተዘጋጅቶ የቀረበውን ረቂቅ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል፣ በኒውዮርክ ለተሰለፉት ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልዕክተኞች ትልቅ ችግር ሆነ:: እንኳንስ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራው የማህበረ ፍቅሪ ሀገር ሕዝብ ይቅርና፣ ተቃዋሚ ናቸው የተባሉት የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ወገኖችም ቢሆኑ፣ የኤርትራን በሁለት መከፈል እንደማይስማሙ ተረጋግጧል:: የቀረበውን ረቂቅ ውሳኔ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልዕክተኛ አልቀበልም ብሎ በጥብቅ ቢቃወምና እስከ መጨረሻው ልጋተር ቢል፣ እንግሊዞች ባላቸው አቅምና ሥልጣን፣ የኢትዮጵያን ጥያቄ ከኤርትራ ጉዳይ ውስጥ አውጥቶ ለመጣል ምንም አያዳግታቸውም:: የአንግሎ አሜሪካኖች ድጋፍ ከጠፋ፣ ሌሎቹ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች ለኢትዮጵያ ይቆሙላታል ብሎ ለማለም አይቻልም:: <u>ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት፣ በዚያን ሰዓት የቤቨን ስፎርሳን ስምምነት ከመቀበል በስተቀር ሌላ ምንም ምርጫ አልነበረውም::</u>

በቤቨን ስፎርሳ ስምምነት መሠረት በቀረበው ረቂቅ ውሳኔ ላይ ጉባኤው በሚነጋገርበት ጊዜ፣ ኢትዮጵያ የምትወስደው አቋም ምን መሆን እንደሚገባው በአራት ዋና ዋና ነጥቦች አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ለንጉሠ ነገሥቱ በማስረዳት፣ ለአፈጻጸሙ ሥልጣን እንዲሰጣቸው ያመለከቱት በሚከተለው መልክ ነበር::

1. የኤርትራን በሁለት መከፈል የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት የበለጠ ስለእጠነከረው፣ ኢትዮጵያ ይህንኑ የታሰበላትን ግማሹን አገር እጇ አድርጋ ለቀሪው ትግሏን ብትቀጥል ይሻላል::

2. ለአሥመራና ለምፅዋ ከተሞች የኦቶኖሚ መቀዳደሪያ ቻርት በተባበሩት መንግሥታት በኩል እንዲዘጋጅላቸው ያስፈልጋል፤ የተባለው ሀሳብ፣ በውስጥ ጉዳያችን መግባት ስለሆነ በስፊው ለመከራከር እንዘጋጃለን::

3. ሱማሌና ትሪፖሊታንያ ለጣልያን መንግሥት በሞግዚትነት እንዲሰጡ የቀረበውን ሀሳብ በጥብቅ እንቃወማለን::

4. ከሊቢያ አውራጃዎች ውስጥ፣ ሲረናይከ በእንግሊዝ፣ ፌዘን በፈረንሣይ፣ አስተዳደር እንዲቆዩ በተባለው ጉዳይ ምን አቋም መውሰድ እንደሚሻል ብዙ ተጨንቄያለሁ:: -- ደጋፊዎች ሆነን በይፋ ድምፃችንን ብንሰጥ፤ ኢትዮጵያ ከቅኝ ገዥዎች ጋር ተሰልፋ ነበር. ተብሎ፣ በነገው ታሪክ ወቀሳ ይደርስባታል:: -- ጣልያንን እንደተቃወምነው፣ እንግሊዝንና ፈረንሣይን ብንቃወም፣ በኤርትራ ጉዳይ ተባብረው የሚያደርሱብን በደል በጣም ሊጐዳን ይችላል:: ከዚህ ሁሉ ጣጣ በመጠኑ ለመሸሸ፣ ትሪፖሊታንያ ለጣልያን እንዳትሰጥ እየተቃወምን፣ እንግሊዝንና ፈረንሣይን በሚመለከትው ጉዳይ አብስቴንሽን ብናደርግ ይሻላል::

ግርማዊነትዎን ለማሳሰብ የምፈልገው፣ ይህ አሁን ነድፌ የሚቀርበው ሀሳብ ሁኔታው በዚሁ መልክ ለመከናወኑ በቂ ማረጋገጫ ይገኛ አይደለም:: ጃንሆይ እንደሚያውቁት በመንግሥታት አባሎች የሚካሄድ ጉባኤ ሁልጊዜ አዳዲስ ሀሳቦች በየጉዳዩ ላይ መፍለቃቸው አይቀርም:: ስለዚህ፣ ለታላቋ ብሪታንያ መንግሥት በቀረበው ረቂቅ ውሳኔ፣ ነጥብ በነጥብ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ፣ ለኢትዮጵያ የሚጠቅመውን በማሰብ እንደ ጉዳዩ አዝማሚያ ለመደገፍም ሆነ ለመቃወም እንድችል የግርማዊነትዎን ልዩ ፈቃድና ትእዛዝ በታላቅ ትህትና እለምናለሁ:: ...... »

የአቶ አክሊሉ ቴሌግራም ለጃንሆይ ከመድረሉ በፊት፣ ኢትዮጵያ የቤቨንና የስፎርሳን ስምምነት ተቀብላ ድጋፏን ከመስጠት በስተቀር፤ በኤርትራ ጉዳይ ሌላ ዕድል እንደማይኖራት የእንግሊዝ መንግሥት ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ልዩ መልዕክት ልኮ ነበር:: አዲስ አበባ ያለው የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር መልዕክቱን ለጃንሆይ ሲያቀርብ፣ የቤቨንና ስፎርሳ ስምምነት ያስገኘው ውጤት፣ በተባበሩት መንግሥታት እንዲጸድቅ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በኒውዮርክ ከታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች ጋር በሕብረት እንዲሠሩ አጠንክሮ ጠየቀ::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በኒውዮርክ ላለው ዋና መልዕክተኛቸው በላኩት መምሪያ፣ የአምባሳደር ላሴል ጥያቄ እንዲጠቀስ አልፈቀዱም:: የንጉሡ ነገሥቱ ልዩ ጸሐፊ አቶ ተፈሪወርቅ ግን ለእንግሊዙ እምባሳደር ስልክ ደውለው፤ በተጠየቀው መሠረት ግርማዊ ጃንሆይ ለኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ አስፈላጊውን ትዕዛዝ የላኩ መሆናቸውን ገልጸዋል::

<u>ከግርማዊ ጃንሆይ፤ ላቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የተላከ መምሪያ፤</u>

« በ ...... ቁጥር ቃል በረዥሙ የላከው መልዕክት ደርሶን ተመልክተነዋል:: መችም <u>በኤርትራ ዋና ጉዳያችን ይኸ ቤቨን ስፎርሳ መስማማት</u>

ተባለው ነገር ልባችን ሙሉ በሙሉ አለመደሰቱን ታውቃለህ:: ሆኖም ግማሹን ጆሮችን አድርገን ሌላውን ወደፊት ማታገል ይሻላል ብለህ ያቀረብከውን ሀሣብ ቁመልክተን እንድትገፋበት ፈቅደንልሀል:: ...... ያንተ ቴሌግራም ከመድረሱ በፊት ገርማዊ የታላቋ ብሪታንያ ንጉሥ በላኩልን ልዩ መልዕክት፣ ቤቨን ስፎርሳ የተባለው ስምምነት፣ በተባበሩት መንግሥታት ሲጸድቅ፣ ጥቅሙ ለኢትዮጵያም ለእንግሊዝም ስለሆነ፣ የኛ መልካም ፈቃድ ተጨምሮበት ጉዳዩ እንዲሳካ ልመና አቅርበውልናል:: አንተ እንደገለጽክልኝ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የቀረበውን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ መቃወሙ ጉዳት ማስከተሉን ስታረጋግጥ፣ ሙሉ በሙሉ መቀበሉም በታሪክ ክብራችንን መንካቱ እንደማይቀር አመልክተሃል:: ...... ይኸ የቤቨን ስፎርሳ የተባለው ስምምነት ብዙ ጉዳዮችን አንድ ላይ ይዞ የቀረበ ስለሆነ፣ ከውስጡ የሚጠቅሙንንና የሚጐዱንን መለየት ያስፈልጋል ያልከው የተገባ ነው:: ...... ይኸ በሚሆንበት ጊዜ ግን፣ ከገርማዊ የታላቋ ብሪታንያ ንጉሥና ሕዝብ ጋር ያለንን መልካም ግንኙነት የሚያበላሽና ሌላ ጣጣ የሚያስከትልብን እንዳይሆን በብርቱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ...... በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሲዮን ላይ በሚደረገው ንግግር፣ ዝርዝር ሁኔታውን እየመዘንክ እንደ አግባቡ ለመቃወምም ሆነ ለመደገፍ እንዲፈቀድልኝ ብለህ ያመለከትከው የተገባ ነው:: ያገራችን ክብርና ጥቅም የማይቀንስበትን መንገድ እየተከተልክ፣ ከወዳጆቻችን ጋር ያለን ግንኙነት በፍቅር የሚሄድ መሆኑን እያረጋገጥክ፣ ከዚህ ቀደም የነገርንህንም እያስታወስክ፣ አስፈላጊውን እንድታደርግ ይሁን ...... »

ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው የንጉሠ ነገሥቱ መምሪያ ትክክለኛው ሀሳብ ምን እንደሆነ አቶ አክሊሉ በቶሎ ሊብራራላቸው አልቻለም:: በአራት ነጥቦች እየለዩ ያቀረቡት ሀሳብ የትኛው ተፈቅዶ የትኛው እንደተከለከለ ለማወቅ ግራ ገብቷቸው በማሰብ ላይ እንዳሉ፣ ከጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ አንድ ሌላ ቴሌግራም ደረሳቸው::

ለወዳጄ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፤ እንደምን ከርመሃል? እኔ በእግዚአብሔር ቸርነት ደህና ነኝ::

ቤቨንና ስፎርሳ የተባሉት የአውሮፓ የፖለቲካ ሰዎች በኤርትራ፣ በሱማሌና በሊቢያ ጉዳይ ለየጥቅማቸው የተበተቡት ስምምነት፤ የሚጐዳንን ለመቃወምና የሚጠቅመንን ለመደገፍ ትልቅ ችግር ላይ መሆንህን ሰምቼ አዘንኩልህ:: በዚህ ላይ ደግሞ ከጌቶቹ የተሰጠህን መምሪያ ስናዘጋጅ፣ ለአንተ በሚሆን አነጋገር ሳናሰናዳው በመቅረታችን፣ ያለብህን ጣጣ በማቃለል ፋንታ ጭንቁን የሚያበዛብህ መሆኑን፤ ዘውዴ ገብረሕይወት አስቦ ስላስታወሰኝ፤ ወዲያውኑ የኔ ማብራሪያ ይረዳህ ይሆናል ብዬ ይህችን መልዕክት ልኬልሃለሁ::

ጌቶቹ፣ አንተ ሀሳብ ላይ እንዳትወድቁ በማለት፤ ከእንግሊዝ መንግሥት የደረሳቸውን መልዕክት እንድታውቀው አልፈቀዱም ነበር:: በኔ ግምት ግን አንተ በቀላሉ ሞራልህ የሚነካ ስላልሆነ ማወቅ ይገባሃል እላለሁ:: ወዳጆቻችን የሚሉት ዋናው ነገር፣ ቤቨንና ስፎርሳ የተስማሙበት የኤርትራ ጉዳይ እንዲጸድቅ፣ ከኛንሆይ ዋና መልዕክተኛ እስካሁን ትብብር አላገኘንም ነው:: ይኸ ጉዳይ በተባበሩት መንግሥታት ሳይጸድቅ ቢቀር፣ ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ መተባበር ጉድለት ይሆናል የሚል ሀሳብ ሰንዝረዋል:: ይህ አባባል ምን ፍሬ እንደሆነ ከማንም የበለጠ አንተ ማወቅ አለብህ:: እኔ እንደገባኝ እነዚህ የኔና ያንተ የልብ ወዳጆች፣ የኤርትራን አንዱን አካል ቆርጠው ከሱዳን በማቀላቀል፣ ከሊቢያም ለጦር ማከማቻ

የሚያስፈልጋቸውን ሲረናይከን ይዘው ለመኖር ስለቆረጡ፣ ምኞታቸው እንዲፈጸምላቸው በጉባኤው ላይ በሞቀ ዲስኩር እንድትደግፋቸው ነው:: መቸም አንተ የማትወደው ለእንግሊዞች ተብሎ በሊቢያ ጉዳይ የምትሰጠው ድጋፍ፣ ጣልያንም ትሪፖሊታንያን እንዲያገኝ የሚረዳ ይሆንብኛል ብለህ ነው:: ..... ከኛንሆይ የተላከልህ መምሪያ ትክክለኛ ትርጉሙ የሚከተለው ነው::

« ...... በጉባኤው ላይ ክርክሩ በሚደረግበት ጊዜ ወዳጆቻችንን በቀጥታ የማነቅፍ ወይም የእነሱን ጥቅም በቀጥታ የሚያበላሽ ነገር በአንተ ግንባር ቀደምትነት እንዳይፈጠር ብቻ ነው:: ..... » ከዚህ በተረፈ ባለህ የፖለቲካ ጥበብ ለኢትዮጵያ የሚጠቅመውንና የሚጐዳውን እዚያው እያየህ፣ መወሰንና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ነው:: ጌቶቹን በጣም አሳስቧቸው የነበረው፣ ስለ አሥመራና ስለ ምፅዋ ከተሞች ጉዳይ ነበር:: ለዚህም በብርቱ ለመሟገት መቁረጥህን ስለነገርካቸው ተደስተዋል:: እንግዲህ እንደምታውቀው፤ እዚህ ባለን አቅም ሁሉ ሥራህ እንዲቃናልህ እንጥራለን:: እግዚአብሔር ውጤቱን ያሳምርልህ በሠላም ይግጠመን:: ..... »

በዘውዱ ገብረሕይወት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር አሳሳቢነት ከጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ አቶ እክሊሉ የደረሳቸው ማብራሪያ በጣም ጠቃሚ ስለሆነ፣ በጉባኤው ላይ ለሚወስዱት እርምጃ ደህና መንገድ ከፈተላቸው::

ይህ የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት፣ መጀመሪያ በዋናው ኮሚሲዮን፣ ቀጥሎ በንዑስ ኮሚቴ፣ እንደገና ወደ ዋናው ኮሚሲዮን፣ ከዚያ ለጠቅላላው ጉባኤ፣ እየተላለፈ ንግግር ሲደረግበት እንደቆየ፣ በመጨረሻም ውጤቱ ምን እንደሆነ ወደፊት እናየዋለን::

## የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት በንዑስ ኮሚቴ «15»

በተባበሩት መንግሥታት ዘንድ ያለው የታላቋ ብሪታንያ ዋና መልዕክተኛ፣ ቤቨንና ስፎርሳ በተስማሙበት መሠረት ረቂቁን ውሳኔ አስተካክሎ ለዋናው ኮሚሲዮን ሲያቀርብ፣ በተጨማሪ ከሕንድ፣ ከአውስትራሊያና ከኢራቅ መንግሥታት፣ ለእነዚሁ ለቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች መፍትሔ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ ሀሳቦች መጉረፍ ጀመሩ::

የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካርሎ ስፎርሳ በሎንዶን ያደረገውን ስምምነት በይፋ እንዲደግፉለት፣ ለወዳጁ ለፈረንሣይ መንግሥትና ለታዛገቹ የላቲን አሜሪካ አገሮች ለማስረዳት ጥቂት ቀናቶች አስፈልገውት ነበር:: ላቲኖቹም ሎንዶን ላይ ስለተደረገው ስምምነት መምሪያው ከጣልያን መንግሥት ተፋጥኖ ስላልደረሳቸው፣ ከታላቋ ብሪታንያ ዋና መልዕክተኛ የተዘጋጀውን አዲሱን ረቂቅ ውሳኔ ለማደናቀፍ፣ በስፊው ማምታታት ጀመሩ:: በእሥራ ስምንቱ የላቲን አሜሪካ አገሮች ስም « ..... የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች በኢንተርናሽናል ድርጅት ሞግዚትነት (አስተዳዳሪው ጣልያን ሆኖ) ተመድበው፤ ሊቢያ ከአሥር ዓመት በኋላ ነፃነቷን እንድትቀበል፣ ኤርትራና ሱማሌ ግን ነፃ የመሆናቸው ጊዜ ሳልተወሰነ ዘመናት እንዲቆይ ..... » የሚል ሀሳብ ነደፉ::

<u>ከሕንድ ከአውስትራሊያና ከኢራቅ</u> በቀረቡት ረቂቅ ውሳኔዎች ላይ፣ በተለይ ኤርትራን በሚመለከት ጉዳይ ሶስቱ አገሮች ተመሳሳይ የሆነ አቋም አሳይተዋል። ይኸውም የኤርትራ ሕዝብ ፍላጐቱ ምን እንደሆነ በትክክል እንዲታወቅ፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የራሱ የሆነ መርማሪ ኮሚሲዮን ልኮ ማጣራት አለበት ሲሉ ያሳሰቡት ነው።

ከተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች የሚቀርቡት የተለያዩ ሀሳቦች፣ የቤቨን ስፎርሳን ስምምነት እያወናበዱ የእንግሊዝን ዕቅድ የሚተናኮሉ በመሆናቸው፣ የአሜሪካ ዋና መልዕክተኛ ጆን ፎስተር ደለስ እንድ ዘዴ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ታየው። ግንቦት 9 ቀን 1949 ዓ.ም ለዋናው ኮሚሲዮን ባቀረበው ሀሳብ፣ አሥራ አምስት (15) አባል አገሮች ያሉበት (ኢትዮጵያ ጭምር) አንድ ንዑስ ኮሚቴ በአስቸኳይ ተቋቁሞ፣ እነዚህን ከልዩ ልዩ አገሮች የቀረቡትን ረቂቅ ውሳኔዎች <u>በሁለት ቀን ውስጥ</u> አጣርቶ ብዙ ድጋፍ ያገኘውን ሀሳብ መርጦ፣ ለዋናው ኮሚሲዮን እንዲያቀርብ ጠየቀ። ወዲያውም የአሜሪካ ሀሳብ በ34 ድምፅ ብልጫ ተደግፎ፣ የመለያ ቁጥሩ «15» የሆነው ይህ ንዑስ ኮሚቴ በፍጥነት ተቋቁሞ ሥራውን ጀመረ።

በቤቨን ስፎርሳ ስምምነት መሠረት ከታላቋ ብሪታንያ ተሻሽሎ የቀረበውን ረቂቅ ውሳኔ እንዲደግፋለት፣ የጣልያን መንግሥት ወገኖቹ የሆኑትን ሁሉ አዘጋጅቷቸው ስለነበረ፣ ንዑስ ኮሚቴ «15» ሥራውን ሲጀመር ብዙ ችግር አላጋጠመውም። ከሶቪየት ሕብረትና ከአንዳንድ አገሮች የቀረቡትን የተለያዩ ሀሳቦች በድምፅ ብልጫ አስወግዶ፣ ከታላቋ ብሪታንያ በቀረበው ረቂቅ ውሳኔ ላይ ብቻ ለመነጋገር፣ የንዑስ ኮሚቴው የሥራ መመሪያ ሆነ።

ኤርትራን በሚመለከት፤ በኮሚቴውና በኢትዮጵያ መልዕክተኛ መካከል ከፍ ያለ ክርክር የተፈጠረው፣ ለአሥመራና ለምፅዋ ከተሞች የተለየ የመተዳደሪያ ቻርት ይዘጋጅላቸዋል በሚለው ቃል ነበር። ኮምት ካርሎ ስፎርሳ ያሳደረው ተስፋ፣ ሁለቱ ዋና ዋናዎቹ የኤርትራ ከተሞች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የታወቀ የአተኖሚ ቻርት ሲኖራቸው፣ ከንቲባዎቹ የሚመረጡት በነዋሪዎቹ ድምፅ ስለሆነ፣ የጣልያን ዜጐች በገንዘብ ኃይል ምርጫውን ለማግኘትና የአስተዳዳሪነቱን ወንበር ለመያዝ ይችላሉ የሚል ነው። የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኧርነስት ቤቨን ግን፣ የስፎርሳ ሕልም በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሲዮን ለመጽደቅ ዕድል እንደማይኖረው ያውቅ ነበር። በንዑስ ኮሚቴ «15» ከተመደቡት አባል አገሮች ውስጥ፣ ፈረንሣይና ላቲኖቹ፣ የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች የአተኖሚ ቻርት እንዲሰጣቸው ብቻ ሳይሆን፤ ቻርቱ የሚሰናዳው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በጣልያን መንግሥት ተራድኦ ነው ብለው ጩኸታቸውን ቀጠሉ። የኢትዮጵያ መልዕክተኛም « ..... ይህን የመሰለ የአንድን ነፃ መንግሥት መብቱንና ክብሩን በቀጥታ የሚነካ፣ ከኢንተርናሽናል ሕግና ሥርዓት ውጭ የሆነ ፋሽስታዊ ሀሳብ፣ የማንቀበለው ብቻ ሳይሆን አጥብቀን የምቃወመው ነው ...... » በማለት ተከራከረ። በኢትዮጵያ መልዕክተኛና በጣልያን ወገኖች መካከል የጋለ ክርክር በሚካሄድበት ሰዓት፤ አዲስ አበባ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ስለ አሥመራና ምፅዋ ከተሞች ጉዳይ በቀረበው ሀሳብ፣ የእንግሊዝን አምባሳደር ጠርተው ቅሬታቸውን ገለጡ። በዚህ ጉዳይ፣ የታላቋ ብሪታንያ አምባሳደር ዳንኤል ላሴልስ (LASSELLES) ከአዲስ አበባ ወደ ሎንዶን ባስተላለፈው ሰፊ ራፖር ውስጥ የገለጸው አስተያየት የሚከተለው ነው።

« ...... ንጉሠ ነገሥቱ የኤርትራን በሁለት መከፈል ግዴታ ሆኖባቸው የተቀበሉ ቢሆንም፣ ለአሥመራና ለምፅዋ ከተሞች በተባበሩት መንግሥታትና በጣልያን ሕብረት የመተዳደሪያ አቶኖሚ ቻርት ይዘጋጅላቸዋል ተብሎ በቀረበው ሀሳብ ከፍ ያለ ቅሬታ ተሰምቷቸዋል። አማካሪዎቻቸው በየጊዜው የሚያቀርቡላቸው ራፖር፣

...... የኤርትራን የምዕራቡን አውራጃ ቆርጠው ወደ ሱዳን ለማቀላቀል የፈለጉት እንግሊዞች ናቸው።.........

...... የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች ነፃ የአስተዳደር አቶኖሚ እንዲኖራቸው የሚለውን ሀሳብ በተንኮል የጸነሱት እንግሊዞች ናቸው። ...

...... ኢትዮጵያ ሠላም እንዳይኖራት፣ ጣልያን ሱማሌን በሞግዚትነት እንድታስተዳድር ሀሳቡን ያመነጩት እንግሊዞች ናቸው። .....

በሚል የተሳሳተ አስተያየት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ደርሰንበታል።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲያውቁት በበኩሌ ጊዜ ወስጄ በዝርዝር አስረድቻቸዋለሁ። ..... ከኤርትራ ግዛት የምዕራባዊው ቆላ ወደ ሱዳን እንዲቀላቀልና ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀድ ሀሳቡ የመነጨው በመጀመሪያ ከአሜሪካ መንግሥት መሆኑን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርዎ አክሊሉ ሀብተወልድ ደህና አድርጐ ያውቃል። አሜሪካኖችም ይህንን ሀሳብ ሲያቀርቡ፣ ኢትዮጵያን ለመርዳት በማሰብ መሆኑ ጥርጥር የለውም።

...... ግርማዊነትዎ እንደሚፈልገው፣ መላው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ይቀላቀል የሚል ሀሳብ ቢቀርብ፣ የጣልያን ደጋፊዎች የሆኑት ፈረንሣይና የላቲን አሜሪካ አገሮች፣ ዓረቦቹና እስላሞቹ፣ የሶቪየት ሕብረትና ሳቴሊቶቹ በሙሉ ስለሚቃወሙ፤ ጉዳዩ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለመጽደቅ ጨርሶ ተስፋ የለውም። ነገር ግን እስላም የሆነው ሕዝብ የሚኖርበት የምዕራቡ አውራጃ በሀይማኖቱና በባሕሉ ከሚቀራረበው ከሱዳን ጋር ተቀላቅሎ፣ ሌላው የክርስቲያኑ ወገን ከኢትዮጵያ ጋር ይሁን ሲባል፤ የዓረቦቹንና የእስላም አገሮቹን ተቃውሞ ማስወገድ ይቻላል። .... በመሠረቱ ትልቁ ትግል፤ የጣልያን ወገኖች የሆኑት ፈረንሣይና አስራ ስምንቱ የላቲን አሜሪካ አገሮች፤ ከተቃዋሚነት ወደ ደጋፊነት እንዲለወጡ ማድረጉ ነው። የእነዚህን አገሮች የድምፅ ድጋፍ ለማግኘትና የቀረበው ረቂቅ ውሳኔ ሊጸድቅ የሚችለው፤ ጣልያን ሲስማማ ብቻ ነው። ባለፈው ጊዜ ለግርማዊነትዎ እንዳስረዳሁት፣ « ቤቨን ስፎርሳ » የተባለው ፎርሙላ የተፈጠረው፣ ጣልያንን ይዘን የሌሎቹን ተቃዋሚነት ለማስጣል ነው።

...... የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች የተለየ የአቶኖሚ መተዳደሪያ ቻርት ቢዘጋጅላቸው ይሻላል የሚል ሀሳብ የተጫረው፤ ከታላቋ ብሪታንያ ሳይሆን፣ አሁንም ከአሜሪካ መልዕክተኛ በኩል ነው። ይህንንም አክሊሉ ሀብተወልድ የሚያስታውሰው መሆን አለበት። ...... የጣልያን ወደ ኤርትራ የመመለሱ ዕድል የተዘጋው፣ በታላቋ ብሪታንያ ኃይልና ፍላጐት ነው እንጂ፣ በሌሎቹ ታላላቅ መንግሥታቶች አቋም አይደለም። ነገር ግን ለእነዚህ ዘመናዊ ለሆኑት ለአስመራና ለምፅዋ ከተሞች፣ የመተዳደሪያ ቻርት እንዲኖራቸውና፣ በኤርትራም የሚኖሩት የጣልያን ዜጐች መብትና ግዴታ በሕግ የተወሰነ እንዲሆን፣ የታላቋ ብሪታንያ

መንግሥት አስተያየት ቢሰጥ፣ ኢትዮጵያን የሚጐዳ ነው ተብሎ መተርጐም የለበትም:: ...... » በማለት አሰረድቻለሁ::

ንጉሠ ነገሥቱ ያቀረብኩላቸውን ሰፊ ማብራሪያ በጥሞና ካዳመጡ በኋላ፣ የሰጡኝ መልስ እጅግ የሚከበር ሆኖ አግኝቼዋለሁ::

« ...... ከብዙ ዓመታት በፊት መላው ኤርትራ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል፤ ለዓለም ታላላቅ መንግሥታቶች ያቀረብነው ጥያቄ ግዛታችንን ለማስፋፋት፣ የኛ ያልሆነውን የባዕድ አገር ካልተሰጠን፣ በማለት አይደለም:: ከእግዚአብሔር የተቀበልነው አደራ፣ ከአባቶቻችን የወረስነው ኃላፊነት፣ ለሕዝባችን የገባንለት ቃል፣ የኢትዮጵያን ነፃነትና የሕዝቧን አንድነት ለመጠበቅ፣ በውጭ ኃይል ተለያይቶ የነበረውን ሕዝብ ለማገናኘትና ታሪክን እበታው ለመመለስ ነው:: ይህንንም የቆምንበትን መሠረታዊ ዓላማ፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ደህና አድርጐ እንደሚረዳልን ተስፋችን ጽኑ ነው::

...... ዛሬ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ የአባል አገሮች በፖለቲካ ጥቅም መከፋፈልና የተለያዩ ወገኖች መፈጠር፣ ትክክለኛ ፍርድ ሊያስገኝ እንደማይችል ብናውቅም፣ ኤርትራን በሁለት መክፈል ተገቢ ነው ብለን መቀውንም አናምንም:: ...... ከዚህ በቀር ደግሞ የጣልያን ወደ ትሪፖሊታንያ እና ወደ ሱማሌ መመለስ፤ በጣም ያስገረመን ብቻ ሳይሆን፣ እጅግ ያሳዘነን መሆኑንም አንሸሽግም:: ከጦርነቱ በኋላ፣ የዓለም ሠላም ሲመሠረት፤ ፋሽስት ጣልያን ያደረሰችው ጥፋት ታውቆ፣ የቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶቿ በሙሉ እንዲወሰዱባት የተፈረደባትን፣ አዲሱ የጣልያን መንግሥትም ተስማምቶ ውሉ በተፈረመ ማግሥት፤ ትሪፖሊታንያ እና ሱማሌ ተመልሰው ለጣልያን እንዲሰጡ የታሰበው፣ ከእውነተኛ ፍርድ ይልቅ፣ የግል ጥቅም የሚበልጥ መሆኑን፣ የዓለም ታሪክ ትዝብቱን፣ ለሚተካን ትውልድ እንደሚያቀርብልን እርግጠኞች ነን::

...... እንግሊዝ አገር በታተሙ አንዳንድ ጋዜጦች ላይ፣ ጣልያን ወደ ሱማሌ እንድትመለስ በመታሰቡ ኢትዮጵያ በጣም ፈርታለች፤ ተብሎ የተጻፈውን ተመልክተን ተገርመናል:: እንደሚያውቁት ሥጋትና ፍርሃት የተለያዩ ናቸው:: ያለፉት ታሪኮች እንደሚያሳዩት፣ በጣልያን በኩል ተደጋግመው የደረሱብንን ብዙ ጦርነቶች ሁሉ የመከትን ስለሆነ፤ ለፍርሃት ቦታ አንሰጠውም:: እንሰጋለን ስንል፣ ለሠላም እምነት የለንም ማለታችን ነው:: በኒውዮርክ የመደብነው ዋና መልዕክተኛችን አክሊሉ ሀብተወልድ እንዳስረዳው፤ ኢትዮጵያ ለነፃነቷ ታጥቃ መኖር ስለአለባት፣ የጣልያንን ሱማሌ መመለስ በሠላም መልክ አትመለከተውም::

...... አሁን ወደ መጨረሻው ጉዳይ እንመለስና ኮሚቴ 15 በተባለው ጉባኤ ላይ፤ ንግግር የሚደረግበት የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች ጉዳይ፣ ለመተዳደሪያቸው ያስፈልጋል የተባለው አቶኖሚ፣ የውጭ እጅ ሳይገባበት በኛ መልካም ፈቃድ የሚፈጸም ከሆነ፤ ልንቀበለው እንችል ይሆናል:: ለማናቸውም ዋና መልዕክተኛችን አክሊሉ ሀብተወልድ የሚጠቅመንን እና የሚጐዳንን እየለየ እንዲወስን አዘነዋል... »

ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው ንጉሠ ነገሥቱ የተናገሩት የሚያምኑበትን ትክክለኛውን አስተያየታቸውን ነው:: ትልቁ ባለሥልጣን ወልደጊዮርጊስና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ የታላቋ ብሪታንያን መንግሥት የማይወዱ በመሆናቸው፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ብዙ ችግር አለባቸው:: በጠቅላላው ለቀድሞዎቹ

የጣልያን ኮሎኒዎች የወደፊት ዕድል ለመወሰን፣ ከታላቋ ብሪታንያ የቀረበውን ሀሳብ፣ ለነዚህ ለሁለቱ የኤርትራ ከተሞች ስለታሰበው አቶኖሚና፣ እንዲሁም ስለ ጣልያን ወደ ሱማሌ መመለስ ነው እንጂ፣ በሌሎቹ ጉዳዮች ላይ ንጉሠ ነገሥቱ አልተጨነቁም:: ሆኖም የቤቨን ስፎርሳ ፎርሙላ በተባበሩት መንግሥታት መጽደቅ የኢትዮጵያ ጥቅም መሆኑን በማስረዳት፣ ዋናው መልዕክተኛ አክሊሉ ሀብተወልድ ከታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች ጋር እየተመካከረ እንዲሠራ ለንጉሠ ነገሥቱ አመልክቼ፣ ይኸው ትእዛዝ መተላለፉን ልዩ ጸሐፊያቸው ተፈራወርቅ አረጋግጠልኛል::

አክሊሉ ሀብተወልድ ከንጉሠ ነገሥቱ በተላለፈለት መምሪያ መሠረት ከታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች ጋር እየተመካከረ መሥራት አለመሥራቱን በአስቸኳይ እንዲገለጽልኝ በማለት አምባሳደር ላሴል (LASSCELLES) ራፖሩን ዘግቷል::

በዚህ ጊዜ ውስጥ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ንዑስ ኮሚቴ «15» የተቀጣጠለው የክርክር እሣት አልበረደም:: በአሥመራና በምፅዋ ከተሞች ጉዳይ የተደነቀሩትን ሀሳቦች፣ ኮሚቴው በድምፅ ብልጫ ለማለፍ ቢሞክርም፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ እስከ ምን ጊዜውም እንቀበለውም የሚል መግለጫ ሰጡ:: ጉዳዩ እየከረረ ጊዜውም እያለቀ መሄዱን አይቶ የአሜሪካ ዋና መልዕክተኛ ጆን ፎስተር ደለስ፣ « ..... ይህ የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች አቶኖሚ ጉዳይ፣ አቀራረቡ በኢትዮጵያ መንግሥት የውስጥ ጉዳይ እንደመግባት የሚያስቆጥር ስለሚያስመስል ቢሰረዝ ይሻላል ..... » የሚል ሀሳብ አቀረበ:: ሀሳቡ በሙሉ ከተሰረዘ፣ የጣልያን ወገኖች የቀረቡትን መፍትሔዎች በሙሉ ስለሚያደናቅፉት፣ አስታራቂ የሆነ መንገድ ለመፈለግ እንግሊዞች ውስጥ ውስጡን መሥራት ጀመሩ:: በመጨረሻው « ለአሥመ ራና ለምፅዋ ከተሞች የመተዳደሪያ ቻርት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት እንዲያዘጋጅላቸው » ግዴታ ሳይሆን በማሳሰቢያ መልክ እንዲቀርብ ኮሚቴው በሙሉ ተስማማ::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግንቦት 10 ቀን 1949 ዓ.ም ለእንግሊዝ አምባሳደር በገለጹት አስተያየት፣ « ...... የውጭ እጅ ሳይገባበት በኛ መልካም ፈቃድ የሚዘጋጅና የሚፈጸም ከሆነ ልንቀበለው እንችል ይሆናል ...... » ማለታቸው ይታወሳል:: ንዑስ ኮሚቴውም ከጃንሆይ ፍላጐት ጋር የሚመሳሰል ውሳኔ ቢያሳልፍም፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ንትርኩን አበረደ እንጂ ተቀብያለሁ ብሎ ድምጹን አልሰጠም::

አሥራ አምስት አባል አገሮች የተሰየሙበት ንዑስ ኮሚቴ ሁለት ቀንና ሌሊት በሰፊው የተነጋገረበትና በመጨረሻም በድምፅ ብልጫ ተስማምቶ ለዋናው ኮሚሲዮን ያስተላለፈው ውሳኔ፣ ያንኑ « የቤቨን ስፎርሳን ስምምነት » የተከተለ ሆነ::

1. ሊቢያ በሶስት ተከፍላ፣

ሲሬናይክ፣ በታላቋ ብሪታንያ፣
ፌዘን፣ በፈረንሣይ፣
ትሪፖሊታንያ በጣልያን አስተዳደር ለአሥር ዓመት ከቆዩ በኋላ፣
የሊቢያ አንድነት ተጠብቆ ነፃነቷን እንድታገኝ፣

2. ሱማሌ፣ ላልተወሰነ ጊዜ በጣልያን የሞግዚት አስተዳደር እንድትቆይ፤

3. ኤርትራ፣ ከምዕራባዊው ቆላ በስተቀር፤ ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀድ፤ የምዕራቡ ቆላ በህይማኖቱ ከሚመሳሰለው ከሱዳን ጋር እንዲቀላቀል፤ የንዑስ ኮሚቴው ውሳኔ ለዋናው ኮሚሲዮን ተላለፈ።

# የዋናው ኮሚሲዮን ውጤት

አሥራ አምስት አባል አገሮች የተካፈሉበት ንዑስ ኮሚቴ ያዘጋጀው ረቂቅ ውሳኔ ለዋናው ኮሚሲዮን ሲቀርብ፤ የቤቨን ስፎርሳን ስምምነት የሚቃወሙት ወገኖች ሁሉ በየፊናቸው ልዩ ልዩ ሀሳብ እየተበተቡ የጉባኤውን አጀንዳ ማደፍረስ ጀመሩ።

ዓረቦቹ፣ የእስላም አገሮችን ድጋፍ ይዘው በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ለሙግት የታጠቁት፣ ሊቢያ በሶስት አውራጃ መከፈሏ ቀርቶ አንድነቷ እጥንቱ በታው እንዲመለስና፣ ሳይውል ሳያድር ነፃነቷ እንዲታወጅላት መሠረታዊ ዓላማቸው ሲሆን፣ በተለይ ጣልያን ተመልሳ ትሪፖሊታንያን እንዳትይዝ ለማገድ ነበር።

ኤርትራን በሚመለከት ግን፣ ከመስኮብና ከሳቴሊቶቹ በስተቀር፣ የዓረቦችና የእስላም አገሮች ቡድኖች ተቃዋሚ አልነበሩም። ይልቁንም ሳውዲ ዓረቢያና ግብፅ በሰጡት መግለጫ፣ የኤርትራ የክርስቲያኑ ወገን ወደ ኢትዮጵያ እንዲቀላቀል መደረጉንና የእስላሙ ክፍል ከሱዳን ጋር እንዲዋሀድ መታሰቡን ደግፈዋል። ከአንግሎ አሜሪካኖች ቁጣ ይልቅ ከዓረቦች የሚሰነዘርብን ጥቃት የበለጠ ሊጎዳን ይችላል በማለት፤ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ በፓሌስቲን የእሥራኤልን መንግሥት መፈጠር መቃወማቸው ለዚህ ጊዜ የሚረዳ ሆኗል።

ሱማሌን ጣልያን በሞግዚትነት እንድታስተዳድር የቀረበውን ሀሳብ፤ ዓረቦቹ እንደ ሊቢያ ጉዳይ በጠንከረ መንፈስ ባይሆንም ተቃውሞአቸውን ገልጸዋል። በጠቅላላው ሲመዘን ጣልያን ተመልሳ ሱማሌን እንዳትይዝ ከዓረቦቹ ይልቅ ከፋኛ ያመኈረችና የጮኸች ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች። አንዳንድ የእስያ አገሮች ከዓረቦች ጋር ለመተባበር፣ ጣልያን ወደ ቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿ መመለስ የለባትም ብለዋል። ሆኖም እንደ ዓረቦቹ፣ ሊቢያ በቀጥታ አንድነቷ ተመሥርቶ ነፃነቷን መቀበል አለባት አላሉም። የሕንድና የፓኪስታን አስተያየት፣ እነ ዚህ የቀድሞ ኰሎኒዎች ለነፃነት እስኪደራጁ ድረስ፣ በጣልያን ሳይሆን በኢንተርናሽናል ድርጅት የሞግዚት አስተዳደር መቆየት ያስፈልጋቸዋል የሚል ነበር። በተለይ የሕንድ መልዕክተኛ፤ ኤርትራን ሳይጠቅስ፣ ሊቢያና ሱማሌ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሞግዚትነት ቢያንስ ለአሥር፣ ቢበዛ ለሀያ ዓመታት መቆየት ያስፈልጋቸዋል ብሏል። ከዚህም እያይዞ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሞግዚት ሆኖ ሲያስተዳድራቸው፤ ዕውቀታቸው በቂ የሆኑ ሰዎች ስለሚያስፈልጉት፣ ብዙ የተማረ ሕዝብ ያላት ሕንድ፣ በሰለጠኑ ሠራተኞች በኩል ብዙ እርዳታ ለማቅረብ ትችላለች በማለት፤ ለማህተመ ጋንዲ አገር ሰዎች የሥራ ገበያ ለማምረት ሞክሮ ነበር። ከዚህም እያይዞ ስለ ኤርትራ በሰጠው አስተያየት፣ አገሩ በሁለት ከሚከፈል፣

ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል የሚፈልገው የኤርትራ ነዋሪ ሕዝብ ስንት በመቶ እንደሆነ ለማወቅ፤ ልዩ መርማሪ ኮሚሽን ተልኮ ቢጣራ ይሻላል የሚል ሀሳብ ደንቅሯል::

ሶቪየት ሕብረትና ሳቴሊቶቹ (ቤይሎሩሲያ፣ ቼኮስሎቫኪያ፣ ፖላንድ፣ ኡክሬን) በድምሩ አምስቱ አገሮች፣ ለነዚህ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መስኩብ አባል የሆነበት፣ በተባበሩት መንግሥታት ስም የሚካሄድ የሞግዚት አስተዳደር ለተወሰነ ጊዜ ካልተቋቋመ፣ እነዚህ ድሆች አገሮች፤ የኮሎኒያሊስቶች አስተዳደር ከወደቀባቸው፣ ምንጊዜም ነፃነትን እንደማያገኙ፤ ትክክለኛ ፍርድና ዴሞክራሲ እንደሚነፈጋቸው፤ እየደጋገሙ የሚያሰሙትን ጩኸት አላቋረጡም:: ትልቁ ችግር የሶቪየት ሕብረት ረቂቅ ውሳኔ በጉባኤው ላይ በቀረበ ቁጥር፣ ደጋፊዎቹ ያው እንደተለመደው ከራሱ ከመስኩብና ከአራቱ ሳቴሊቶቹ በስተቀር ሌላ አጃቢ ማጣቱ ነው::

የአሜሪካ ዋና መልዕክተኛ ጆን ፎስተር ደለስ፤ ከሶስት ቀናት በፊት ንዑስ ኮሚቴ «15» እንዲቋቋም ያስደረገው፣ ከልዩ ልዩ አባል አገሮች የጐረፉትን ልዩ ልዩ ሀሳቦች በድምፅ ብልጫ እያስወገደ፣ የቤቨን ስፎርሳን ፎርሙላ የተከተለ ረቂቅ ውሳኔ እንዲያቀርብና ዋናው ኮሚሲዮን በዚሁ ላይ ብቻ ተነጋግሮ የራሱን ውሳኔ ለጠቅላላው ጉባኤ እንዲያስተላልፍ ነበር:: ንዑስ ኮሚቴው የተሰጠውን ተግባር በሚገባ ፈጽሟል:: ነገር ግን መላው የተባበሩት መንግሥታት አባሎች በሚካፈሉበት በዋናው ኮሚሲዮን ላይ፣ የንዑስ ኮሚቴውን ሥራ እንቃወማለን ብለው የሚነሱትን አባል መንግሥታት ማገድ እንደማይቻል፤ ጆን ፎስተር ደለስ ጊዜ እግኝቶ አላተኮረበትም:: ከዚህ በላይ ደግሞ በዚሁ ሰሞን የአሜሪካ የመልዕክተኞች ጓድ በፓሌስቲን መሬት አዲስ የተቋቋመችው እሥራኤል፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል እንድትሆን ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ስለሆኑ፣ የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ በጥብቅ የሚከታተሉት እንግሊዞች ብቻቸውን ነበሩ:: በዋናው ኮሚሲዮን ስብሰባ ከተካፈሉት ሃምሣ ስባት አገሮች መካከል፤ የቤቨን ስፎርሳን ፎርሙላ ስንቶቹ ደጋፊዎች፣ ስንቶቹ ተቃዋሚዎች፣ ሊሆኑ እንደሚችሉ እንግሊዞች ባደረጉት ክትትል፣ በሁለት ሶስተኛው የድምፅ ብልጫ ውሳኔው እንዲጸድቅ ለማድረግ የሁለት አገሮች ድጋፍ እንደሚጐድል ተረዱ:: ቀደም ሲል እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ጣልያንን ለመቃወም የቆረጠች መሆኗ ይታወሳል:: በዚህ ሰዓት በታላቋ ብሪታንያ እና በኢትዮጵያ መልዕክተኞች መካከል አለመግባባት መፈጠር ጀመረ::

ሄክቶር ሚክኒል (HECTOR McNEIL) ከአዲስ አበባ የደረሰው ራፖር፤ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ከታላቋ ብሪታንያ ዋና መልዕክተኛ ጋር በቅርብ እየተመካከሩ እንዲሠሩ ከንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ተልኮላቸዋል የሚል ነው:: የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ግን፣ ቀድሞ እንደሚያደርጉት በራሳቸው ሥልጣንና ነፃ በሆነ አስተሳሰብ የሚሠሩ መስለው ስለሚታዩ፣ ለእንግሊዞቹ ግራ የሚያጋባ ነገር ሆነ:: ጊዜም እያጠረ ስለሄደ ሚስተር ሚክኒል ከአክሊሉ ጋር በቀጥታ መነጋገር ይሻለኛል ብሎ ወሰነ:: «... አንተና እኔ በቅርብ እየተመካከርን ለነዚህ ለሶስቱ አገሮች የቀረቡት ረቂቅ ውሳኔዎች፤ ሁለት ሶስተኛውን የድምፅ ብልጫ አግኝተው እንዲጸድቁ ብናደርግ፣ ጥቅሙ የጋራችን ይሆናል .. » በሚል ቃል የታላቋ ብሪታንያ ዋና መልዕክተኛ ለኢትዮጵያ ሚኒስትር ማሳሰቢያ ሰጠ:: አቶ አክሊሉም በበኩላቸው ለመተባበር ያላቸውን ፈቃደኛነት ከገለጹ በኋላ፤ በኢትዮጵያ በኩል ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ የቁት::

« ...... ለሰስቱ ቅኝ ግዛቶች በንዑስ ኮሚቴ 15 የተዘጋጁት ረቂቅ ውሳኔዎች በዋናው ኮሚሲዮን ሁለት ሶስተኛውን ድምፅ አግኝተው ለማለፍ፣ የኢትዮጵያና የህይቲ ድጋፍ ማስፈለጉን ደርሰንበታል። ይኸውም በሊቢያና በሱማሌ ጉዳዮች ነው። የህይቲ መንግሥት እንዲደግፍ፣ ይህም ባይቻል አብስቴን እንዲያደርግ፣ በፈረንሣይና በአሜሪካ በኩል ተፅዕኖ ይደረጋል። ኢትዮጵያ ግን የራሷ የሆነ ከፍተኛ ጥቅም አላት። ጣልያንን ለማጥቃት በማሰብ ብቻ በትሪፖሊታንያ እና በሱማሌ ጉዳይ ከተቃወመች፣ ኤርትራን የማግኘት ዕድሏ መበላሸቱ መታወቅ አለበት። ከሊቢያና ከሱማሌ ጉዳይ ተነጥሎ፣ የኤርትራ ጉዳይ ለብቻው የሚጸድቅበት መንገድ ይኖራል ለማለት ያስቸግራል። ስለዚህ፣ ኢትዮጵያ የዘላቂ ጥቅሟን በማሰብ፣ በትሪፖሊታንያ እና በሱማሌ ጉዳይ ተቃዋሚነቷን በደጋፊነት መለወጥ ይሻላታል። ምርጫው ያንተ ነው ...... » ሲል የእንግሊዙ ዋና መልዕክተኛ አቶ አክሊሉን አስጠነቀቀ።

አቶ አክሊሉ በሰጡት መልስ፣ « ..... ኢትዮጵያ የሚጠቅማትንና የሚጎዳትን ለይታ የመወሰን መብቷ የተጠበቀ ስለሆነ፣ የማንም አገር ተፅዕኖ አቋሟንና እምነቷን ሊለውጠው አይችልም ..... » አሉ። « ..... በተባበሩት መንግሥታት አባሎች ሁለት ሶስተኛውን ድምፅ አግኝቶ ለማለፍ ችግር የሚገጥመው፣ የጣልያን ኮሎኒያሊስት አስተዳደር በትሪፖሊታንያ እና በሱማሌ እንዲመለስ የተዘጋጀው ውሳኔ ብቻ ነው። ኢትዮጵያን በቀጥታ የሚመለከተው ለኤርትራ የታሰበው መፍትሔ ግን፣ ከሶቪየት ሕብረትና ከአራቱ አጫፋሪዎቹ በስተቀር ሌላ ተቃዋሚ ስለማይኖር፣ ከሁለት ሶስተኛው ድምፅ በሚበልጥ ቁጥር ውሳኔው እንደሚጸድቅ በበኩላችን አርግጠኞች ነን። ....... የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ባደረግነው ጥናት፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች እያንዳንዳቸው፣ በጂኦግራፊም አቀማመጣቸው ሆነ በታሪካቸው፣ የተለያዩ ስለሆኑ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች ውሳኔ የሚሰጡት ለእያንዳንዱ አገር በቀረበላቸው መፍትሔ ላይ ነው እንጂ፤ የሶስቱንም አገሮች ጉዳይ በአንድነት አጣምረን ማየት አለብን ማለት አይገባቸውም። ይሁን እንጂ ኃያላን መንግሥታት ለሚፈልጉት ነገር የመውጫ ዘዴ ማግኘት ስለማይሳናቸው፤ የሊቢያና የሱማሌ ጉዳይ ካልተወሰነ፣ የኤርትራ ጉዳይ ተነጥሎ መጽደቅ የለበትም ብለው መንገዱን ለመዝጋት አይችሉም ብዬ አልከራከርም። አሁን ከተነገረኝ እንደተረዳሁት፣ ይህ ዓይነቱ ችግር እንዳይደርስና የተዘጋጀልን የኤርትራ ጉዳይ እንዲጸድቅልን፤ ትሪፖሊታንያ እና ሱማሌ ለጣልያን እንዲሰጡ ድጋፋችንን ማቅረብ አለብን ማለት ነው። ...... የታላቋ ብሪታንያ መንግሥትና ሕዝብ ደህና አድርጎ እንደሚያውቀው፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ካለፈ ታሪካችን ብዙ ነገሮች እየተማርን የመጣን ነን። ለነፃነትና ለመብት መዋጋት ዋጋው ምን እንደሆነ፣ በውጭ ጠላት የግፍ መከራን መቀበል ምን ያህል እንደሚያስቃይ፣ በዓለም ሸንጎ ላይ ዳኝነትና ፍርድ ማጣት ምን ያህል እንደሚያሳዝን፣ ከማንም አገርና ሕዝብ የበለጠ ደርሶብን አይተናል። ..... በኤርትራ ጉዳያችን የጠየቅነው ዳኝነት በተገቢው መንገድ ታይቶ ተገቢ በሆነው ደንብ ቢፈረድልን ደስ ይለናል። ነገር ግን ኢትዮጵያ በምንም ዓይነት፤ በየጊዜው የጦር እሳት እያዳፈነ ለማጥቃት የሚዘጋጅላት ጠላቷ፤ ሱማሌ ላይ ተመልሶ እንዲነግሥ፣ ድጋፍ ትሰጣለች ብሎ መጠበቅ የማይታሰብ ጉዳይ ነው። ሁለተኛም፣ ከቅኝ አገዛዝ የተላቀቀ አገር የወደፊት ዕድሉ እንዲወሰንለት የኢንተርናሽናል ዳኞች በተሰየሙበት አደባባይ ላይ፣ ጣልያን ተመልሶ የኮሎኒ አስተዳደሩን እንዲቀጥል ኢትዮጵያ ካልደገፈች፣ ኤርትራን አታገኝም ከተባለ፣ አገሬ ጸጸት አያድርባትም። ባመነችበት እስከ መጨረሻው ጸንታ ትቆማለች። ..... የጄኔቩ የመንግሥታት ማህበር እንዳደረገው ሁሉ፣ አሁንም በተራው የተባበሩት

መንግሥታት ፍርድ የሚነፍገንና ጥቃት እንዲደርስብን ዝም ብሎ የሚመለከት ከሆነ፤ ለነፃነታችን እና ሠላም ለሚያስፈልገው ሕይወታችን የተለመደውን መስዋዕትነት እንቀበላለን:: ...... ኢትዮጵያ ከፋሽስት ቀንበር ተላቅቃ ነፃነቷ እንዲመለስ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥትና ሕዝብ የተደረገላትን እርዳታ ምን ጊዜም አትረሳም:: ..... ዛሬም በኮሎኒያሊስት ጣልያን ተወስዶብን የነበረው አገራችን ኤርትራ እንዲመለስልን፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የሚያደርግልንን ድጋፍ በውለታ እንመዘግባለን:: ...... ኢትዮጵያ ለነፃነቷና ለሠላም ሕይወቷ ዋስትና እንዲኖራት በማድረግ ፋንታ፤ ምንጊዜም የማይተኛላት ጠላቷ ተመልሶ ሱማሌ ላይ እንዲሰፍር የታቀደውን ሀሳብ፣ እገሬ አጥብቃ ብትቃወም፣ የታላቋ ብሪታንያን መንግሥት ቅር ያሰኛል ብዬ አላስብም..... »

ከዚህ በላይ የተገለጸውን የአቶ አክሊሉን ሰፊ ማብራሪያ የእንግሊዝ ዋና መልዕክተኛ ያዳመጠው፣ በትእግስትና እርጋታ በተቀላቀለበት መንፈስ ነበር:: ፅለ ኢትዮጵያ አቋም የተናገሩት ሁሉ ትክክል መሆኑን ቢያምንም፣ ሄክቶር ሜክኒል የታላቋ ብሪታንያ ዋና ዓላማ የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት የሚጸድቅበትን ዋስትና ለማግኘት ስለሆነ፣ ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ አንድ ዓይነት እርዳታ ይጠብቃል::

አቶ አክሊሉ በሰጡት መግለጫ በሱማሌ ጉዳይ ጨርሶ የማይበገሩ ቢሆንም፣ ትሪፖሊታንያን በሚመለከት ለመግባባት የሚያስችል፤ ያልተዘጋ ገርበብ ያለ በር መተዋቸው ይታያል:: የኢትዮጵያ አቋም የታላቋ ብሪታንያን ጥቅም የሚጐዳ እንዳይሆን፤ ቀደም ሲል ጆን ስፔንሰር የአቶ አክሊሉ አማካሪ፤ በሊቢያ ጉዳይ አብስቴን ማድረግ ይሻላል ሲል ሀሣብ አቅርቦ ነበር:: አቶ አክሊሉ ግን እኛ ቀድመን ድምፅ ለመስጠት ከመወሰናችን በፊት፣ ከእንግሊዞች በኩል በእርዳታ መልክ እስክንጠየቅ መጠበቅ ይሻላል ብለው አቆዩት:: በመጨረሻው የታላቋ ብሪታንያ ዋና መልዕክተኛ ለአቶ አክሊሉ ባቀረበው ሀሳብ፣ በሱማሌ ጉዳይ ኢትዮጵያ ተቃዋሚነቷን ለመቀጠል ከወሰነች፣ ቢያንስ በሊቢያ ጉዳይ ድምፅ ከመስጠት ብትቆጠብልን (አብስቴን ብታደርግ) እንደ እርዳታ እንቆጥረው ነበር አለ:: እዚህ ላይ አቶ አክሊሉ ጥሩ ዕድል አጋጠማቸው:: በሊቢያ ጉዳይ አብስቴን በማድረግ፤ 1ኛ/ ከእንግሊዞች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ስለሚያሻሽልላቸው፣ 2ኛ/ ዓረቦቹና ወገኖቻቸው በሊቢያ ጉዳይ የኢትዮጵያን አብስቴንሽን እንደ ድጋፍ አድርገው ስለሚቆጥሩላቸው፣ 3ኛ/ ሊቢያ ከአፍሪካ ይልቅ የዓረቦች ጉዳይ ስለሆነ፤ ኢትዮጵያ ለምን ሳትቃወም ቀረች? ተብላ እንደማትወቀስ በማመን፤ ለሱማሌ የታሰበውን ብቻ እየተቃወሙ፣ በትሪፖሊታንያ ጉዳይ አብስቴን ለማድረግ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ወሰኑ::

የኢትዮጵያና የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች በዚህ አኳኋን ተወያይተው በጉባኤው ላይ በሚወሰደው አቋም ከተስማሙ በኋላ፣ በመካከላቸው የነበረው አለመግባባት የተወገደ መስሎ ታየ::

ከአርባ ስምንት ሰዓቶች ጀምሮ ሥራውን የቀጠለው ዋናው ኮሚሲዮን፤ በመጀመሪያ ደረጃ ከመስኮብና ከሕንድ፣ ከኢራቅና ከአውስትራሊያ የቀረቡለትን ልዩ ልዩ ረቂቅ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ካስወገዳቸው በኋላ ንዑስ ኮሚቴ 15 ባዘጋጀው ዶክመንት ላይ ማተኮር ቻለ:: የላቲን አሜሪካ አገሮችና ፈረንሣይ፣ የጣልያንን ጥቅም ለመጠበቅ ትጥቃቸውን ያዘጋጁ ስለሆነ፣ ጣልያን ትሪፖሊታንያን እንዳያገኝ ለማገድ ዓረቦቹና ወገኖቻቸው ያደረጉት ከፍተኛ ጥረት ሳይሳካ ቀረ::

ለሰበቱ የቀድሞ ቅኝ ግዛቶች ከቀረቡት መፍትሔዎች ውስጥ፤ ያለ ችግር በከፍተኛ ድምፅ ማለፍ የቻለው በኤርትራ ጉዳይ ከምዕራብ አውራጃ በስተቀር፣ ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር ይቀላቀል የሚለው አንቀጽ ነበር:: በሀይማኖቱና በባሕሉ ከሱዳን ጋር ስለሚቀራረብ፣ ወደዚያው ይዋሃድ ተብሎ የተፈረደበት የአቆርዳት አውራጃ፤ ዋናው ኮሚሲዮን ላይ ሲቀርብ፤ ብዙ ተቃዋሚዎች ተፈጥረው አከሸፉት:: ይህም ሊደርስ የቻለው፣ የላቲን አሜሪካ አገሮች ከጣልያን የተቀበሉትን መምሪያ ጥሰው ድጋፋቸውን ስለነሱት ነው:: በዚያን ጊዜ ላቲኖቹ ይህንን እርምጃ የወሰዱት፣ በሁለት ምክንያቶች መሆኑ ተደርሶበታል:: ይኸውም፣ 1ኛ/ የኤርትራ የምዕራብ አውራጃዎች ወደ ሱዳን እንዲቀላቀሉ የታቀደው ለእንግሊዞች ጥቅም ስለሆነ፣ 2ኛ/ ላቲኖቹም እንደ አቅማቸው የጣልያን ወገኖች በመሆናቸው፣ በአፍሪካ ላይ የሞግዚትነት ሥልጣን ለኛስ ለምን አይሰጥም ? በማለት የአቆርዳትን አውራጃዎች ለማስተዳደር በመመኘታቸው ነው:: ለዚህም ማስረጃው በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ንግግር በተደረገበት ጊዜ፤ የኢኳቶር (EQUATEUR) መልዕክተኛ ይህ የአቆርዳት አውራጃ በአንድ የላቲን አሜሪካ መንግሥት ሞግዚትነት እንዲተዳደር፤ አቅርቦት የነበረው ረቂቅ ውሳኔ ነው::

በንዑስ ኮሚቴ 15 ከተዘጋጁለት ልዩ ልዩ ረቂቅ ውሳኔዎች ውስጥ፤ ዋናው ኮሚሲዮን ያልተቀበለው የአቆርዳትን አውራጃ ከሱዳን መቀላቀል ብቻ ሲሆን፣ በሌሎቹ ላይ አንዳንድ የቃላትና የአቀራረብ ለውጥ ከማድረግ በስተቀር፣ ሁሉንም በድምፅ ብልጫ ተቀብሎ፤ ግንቦት 15 ቀን 1949 ዓ.ም ለጠቅላላው ጉባኤ ያስተላለፋቸው ረቂቅ ውሳኔዎች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ::

ሀ/ ሊቢያ፤ ሶስቱም አውራጃዎች (ሲረናይከ፣ ፌዘን ትሪፖሊታንያ) ከአሥር ዓመታት በኋላ በአንድነት ተዋህደው የሊቢያ ነፃ መንግሥት ሆነው ይቋቋማሉ:: እስከ አሥር ዓመታት ድረስ፤

- ሲረናይከ በታላቋ ብሪታንያ
- ፌዘን በፈረንሣይ
- ትሪፖሊታንያ በጣልያን ሞግዚትነት ይተዳደራሉ::

ለ/ ሱማሌ፤ በጣልያን ሞግዚትነት ላልተወሰነ ጊዜ ስትተዳደር ከቆየች በኋላ፤ ወደ ፊት ነፃ መንግሥት የመሆን ዕድል ይሰጣታል::

ሐ/ ኤርትራ፤ ከምዕራባዊው ቆላ አውራጃዎች በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር ይዋሀዳሉ:: እስልምና የተስፋፋባቸው የምዕራብ አውራጃዎች ግን የወደፊት ዕድላቸው ተጠንቶ ይወሰናል:: እስከዚያም በእንግሊዝ አስተዳደር ይቆያሉ::

እነዚህ በዋናው ኮሚሲዮን ተመርምረውና ተጠንተው የተዘጋጁት ረቂቅ ውሳኔዎች ለጠቅላላው ጉባኤ ሲቀርቡ፤ ያለችግር እንደሚጸድቁ በተለይ ጉዳዩ በሚመለከታቸው በአብዛኛዎቹ አገሮች የማያጠራጥር እምነት ነበር::

# በጠቅላላው ጉባኤ፣ ከውሳኔው በፊት

በዋናው ኮሚሲዮን ተሰብስበው አንድ ወር በፈጀ ጊዜ ጉዳዩን መርምረው መፍትሔውን በድምፅ ብልጫ ያዘጋጁትና፣ በጠቅላላው ጉባኤ ላይ ተካፍለው የሚያጸድቁት የመላው የተባበሩት መንግሥታት አባሎች ስለሆኑ፣ ለውሳኔ በቀረበው በዚህ ሰነድ ላይ የሀሳብ ልዩነት ይፈጠርና ሊደፈርስ ይችላል ተብሎ አይጠበቅም ነበር:: ሆኖም በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ድጋፋቸውን ከሰጡት 34 አባል አገሮች መካከል፤ በድንገት አንዱ ተወናብዶ ድምፁን ወደ ተቀዋሚነት በመለወጥ የሚጠበቀውን ውጤት እንዳያበላሽ፣ በተለይ የእንግሊዝ መልዕክተኞች በቅርብ መከታተል ነበረባቸው::

ግንቦት 17 ቀን 1949 ዓ.ም ጠቅላላው ጉባኤ ሥራውን ሲጀምር በሶቪየት ሕብረት ግንባር ቀደምትነት ዓረቦቹና እስያውያኖቹ ከዋናው ኮሚሲዮን የቀረበው ረቂቅ ውሳኔ እንዳይጸድቅ ከፍ ያለ ውዝግብ ፈጠሩ::

« .... ይህ በጠቅላላው ጉባኤ እንዲጸድቅ የቀረበው ረቂቅ ውሳኔ፣ ኮሎኒያሊስቶቹና ኢምፔሪያሊስቶቹ በአንድነት ሆነው፣ በተለይም ጣልያንና እንግሊዝ በተባበሩት መንግሥታት ጀርባ ዶልተው፣ ለራሳቸው ጥቅም በማሰብ ብቻ የጐነጐኑት ሀሳብ ስለሆነ፣ አባል አገሮች እንዳይሳሳቱ አስጠንቅቃለሁ:: ...... » በሚል የከረረ ቃል የሶቪየት ሕብረት ዋና መልዕክተኛ አንድሬ ግሮሚኮ (ANDRE GROMYCO) ንግግሩን ጀመረ:: « ...... የላቲን አሜሪካ አገሮችም ሕብረታቸውን አጠንክረው የተሰለፉት በድምፁ ኮሎኒያሊስቶቹን በተለይ ደግሞ ጌታቸው የሆነውን ጣልያንን ለመርዳት ስለሆነ፣ ለተበደሉትና በቅኝ አስተዳደር ሲጨቆኑ ለኖሩት ሕዝቦች አስበው አያውቁም:: ..... የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል አገሮች እንዲያውቁት የሚያስፈልገው፣ በአሁኑ ጊዜ በቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች ላይ የደረሰው የኢኮኖሚ ውድቀት፤ ተወዳዳሪ የሌለውና እጅግ የሚያሣዝን መሆኑን ነው:: በእነዚህ ድሆች አገሮች ላይ የሚያንሰራራው የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት፤ በየአገሩ ላይ የነበረውን ንብረትና የእርሻ ውጤት እየዘረፈ፤ ወደ ሌሎቹ ቅኝ ግዛቶቹ በማሻገሩ፤ የሊቢያን፣ የኤርትራና የሱማሌን ሕዝቦች ከፍተኛ ሥቃይ ላይ ጥሏቸዋል:: ...... በእነዚህ በኮሎኒያሊስት አገሮች ተቀምሞና ተጭበርብሮ በዋናው ኮሚሲዮን ከጸደቀ በኋላ ለጠቅላላው ጉባኤ የቀረበልን ሀሣብ፣ ታላቋ ብሪታንያ ሲረናይካን፣ ጣልያን ትሪፖሊታንያን ሲይዙ የአሜሪካ መንግሥት አማካይ የሆነ የጦር ማከማቻ አግኝቶ፣ ግሪክንና ቱርክን ከዚያም እልፍ በከፊል የአውሮፓን ደቡብ አገሮች፣ በቁጥጥሩ ሥር እንዲያደርግ ነው:: ታላቋ ብሪታንያም ፓሌስቲንን ለማጥፋት ወታደሮቿን ለማንቀሳቀስ የሚመቻት፣ መነሻው ከሲረናይካ ሲሆን ነው:: የፌዘን አውራጃ ለፈረንሣይ እንዲሰጥ የታሰበው፣ በሰሜን አፍሪካ በኮሎኒያሊስት ፈረንሣይ ጭቆና የሚሰቃየው ሕዝብ፣ ለነፃነቱ እንዳይንቀሳቀስ አፍኖ ለመያዝ ነው:: ...... » ይህ ሁሉ የሚያሳየው፤ ኮሎኒያሊስቶች በድሆች አገሮች ላይ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ የሚፈጽሙትን ግፍ፣ ዛሬም ወደፊትም ለመቀጠል የቆረጡ በመሆናቸው፤ ለእነዚህ ለተበደሉት ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ እንዲሆን፣ የሶቪየት ሕብረት ካቀረበው የውሳኔ ሀሣብ የተሻለ አለመኖሩን፣ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች እንዲገነዘቡት አንድሬ ግሮሚኮ በጥብቅ አሳሰበ::

ግሮሚኮ በምዕራባውያኖችና በተለይም በታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ላይ ያዘነበው ወቀሣ ከምን ጊዜውም የበለጠና የጠነከረ ስለሆነ፣ የእንግሊዝ ዋና መልዕክተኛ የመናገሪያው ተራ ሲደርሰው ምን መልስ እንደሚሰጥ ለመስማት፣ አብዛኛዎቹ መልዕተኞች ቸኩለው ነበር:: ሂክቶር ሚክኪል የሰጠው መልስ አጠር ያለና በአቀራረቡም የጨዋ መንፈስ ይዞ፣ በአነጋገሩ የመሰከቡን ዋና መልዕክተኛ ደህና አድርጎ የሚወርፍ ነበር::

« ..... በዋናው ኮሚሲዮን በሰፊው ተመክሮበት፣ በአብዛኛዎቹ የአባል አገሮች ተደግፎ፣ ጠቅላላው ጉባኤ እንዲያጸድቀው የቀረበው ውሳኔ፣ ጣልያንና ታላቋ ብሪታንያ የዶለቱበትና ያዘጋጁት ነው ተብሎ ሲነገር በመገረም ስምቻለሁ:: ሆኖም ይህን የመሰለው ፍሬቢስ አስተያየት ከሶቪየት ሕብረትና ከሳቴሊቶቹ በስተቀር፣ በተባበሩት መንግሥታት አባሎች ዘንድ ተደማጭነት ይኖረዋል ብለን እናስብም::: ሚስተር ግሮሚኮ፣ ለመንቀፍ የጠቀሰውን ጉዳይ በበሰለ አስተያየት ብንመለከተው፣ ሁለት ወይም ሶስት የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች ተወያይተው ለድርጅቱ ሀሳብ ቢያቀርቡ፣ ኃጢያቱ እምን ላይ ነው ? ...... ለምሣሌ የሶቪየት ሕብረትና ሳቴሊቶቹ በእንድነት እየሆኑ፣ ይስማማናል የሚሉትን ሀሳብ በተባበሩት መንግሥታት እንዲጸድቅላቸው ባቀረቡ ቁጥር መቼ ቀን ተችተን እናውቃለን ? መቸስ ቀን ይህ ሀሳብ በመስከብና በተከታዮቹ የተዘጋጀ ነው ብለን ነቅፈን እናውቃለን ? የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ በተቻለ ፍጥነት መፍትሔ እንዲሰጣቸው ስለምትፈልግ፣ ከብዙዎች አገሮችና በተለይም ከጣልያን መንግሥት ጋር መወያየቷን አትሸሽግም:: ...... የሶቪየት ሕብረት ዋና መልዕክተኛ የምንነጋገርበትን ጉዳይ ወደ ጎን ትቶ ወደ ሌላ አቅጣጫ በመራመድ፣ በቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች ላይ የኢኮኖሚ ችግር የደረሰው፣ በየአገሩ ያሉትን ንብረቶች የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ወደ ሌሎች አገር በማዛወሩ ነው የሚል ክስ አቅርቧል:: የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት እውነተኛውን ነገር ለመግለጥ አይጨነቅም:: በምሥራቅና በሰሜን አፍሪካ ከፋሽስት ጋር ተዋግተን ድል ባደረግን ጊዜ፣ ከጠላት ብዙ መሣሪያዎች ማርከን ወደ ሌላው የጦር ግንባር ማስተላለፋችን እርግጥ ነው:: እነዚህንም የጠላት መሣሪያዎች፣ አብዛኛዎቹን በኢራን በኩል እያሻገርን በዚያን ጊዜ የጦር ጓደኞችን ለሆነው፣ ለሶቪየት ሕብረት መንግሥት ልከንለት የተጠቀመበት ለመሆኑ ትክክለኛ ማረጋገጫ አለን:: ..... ይህ የተከበረው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሽንጉ የሀሰትና የፍሬ ቢስ አስተያየቶች የሚሰራጩበት እንዳይሆንና፣ የቁም ነገር ተግባሩን ከመፈጸም እንዳያሰናክለው፣ ለመላው አባል አገሮች አደራ እያልን፣ የቀረበው ረቂቅ ውሳኔ ብዙ የተደከመበት በመሆኑ እንዲጸድቅ ድጋፋችንን እንሰጣለን ..... » በማለት የእንግሊዝ ዋና መልዕክተኛው ንግግሩን ፈጸመ::

እንደተለመደው የሶቪየት ሕብረት ዋና መልዕክተኛ ሀሳብ ሲሰጥ አጨብጭቦ ለመደገፍ፣ በሚያቀርበው ሀሳብ ላይ ነቀፌታ ሲሰነዘርበት ለመቃወምና ለመሳደብ፣ ታጥቀው የሚጠብቁት ፖላንድና ቼኮስሎቫኪያ ቢመቻቸው፣ ወዲያውኑ በእንግሊዝ መልዕክተኛ ላይ ተነስተው ለመጨፈር አይቦዝኑም ነበር:: ነገር ግን የጉባኤው አጀንዳ በመጀመሪያ ደረጃ ከየመልዕክተኞቹ መሪዎች የሚሰጠውን መግለጫ ማዳመጥ ስለሆነ፣ ሁሉም ተራውን እየጠበቀ ከመናገር በስተቀር ለመነታረኪያ የተመደበ ጊዜ አልነበረም:: የሶቪየት ሕብረት በራሱና በተከታዮቹ ስም ሀሳቡን ከገለጸ በኋላ፣ የሳውዲ ዓረቢያ ዋና መልዕክተኛ በዓረብ አገሮች ስም የሚሰጠውን መግለጫ ለመስማት ጉባኤው ይጠብቅ ነበር::

ሚስተር ደጃኒ (DEJANI) ካቀረባቸው ሀሳቦች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

« .... የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ አገሮች የሊቢያ፣ የኤርትራና የሱማሌ ሕዝቦች፤ በምንም ዓይነት መንገድ የጣልያን አስተዳደር እንዳይመለስባቸው ያቀረቡትን አቤቱታ፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በጥልቅ መመልከት አለበት:: ይህ የሕዝብ ጥያቄ ተገቢውን ውሳኔ ሳያገኝ ቀርቶ፤ ጣልያን ወደ አንዳንዶቹ የቀድሞ ኮሎኒዎቹ ይመለስ ቢባል፤ ሕዝቡ ባለው አቅም የሚዋጋ መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት እንዲገነዘበው ያስፈልጋል:: የአሜሪካ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጀምስ በርንስ ስለ ጣልያን ቅኝ አስተዳደር ሲናገር « .....በጭቆና የተመሠረተ አመራር ነበር .... » ካለ በኋላ « ..... ጣልያን በቅኝ ግዛቶቹ የተጠቀመው ለጦር ጉዳይ እንጂ ለሌላ ዋጋ ላለው ተግባር ለመፈጸም አልነበረም ...... » ሲል የገለጸው አስተያየት መታወስ አለበት::

በጣልያን አገር ተወልዶ ለዓለም ሠላም ጠንቅ የነበረው የፋሽስት አስተሳሰብ ከአገሩ ላይ ሥሩ ተነቅሎ ጠፋቷል ለማለት አይቻልም:: በፋሽስት ዘመን የተቋቋሙት አንዳንዶቹ ድርጅቶች ለምሣሌ፣ የጣልያን የአፍሪካ ሚኒስቴር የሚባለው መሥሪያ ቤት አሁንም አለ:: የቀድሞዎቹ የፋሽስት ባለሥልጣኖችም በየወንበሮቻቸው ላይ እንደሚገኙ ታውቋል:: <u>ለምሣሌ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት የጣልያንን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አጅበው በስብሰባችን አዳራሽ የተገኙትን የታወቁ የፋሽስት ባለሥልጣኖች፣ የኢትዮጵያ ዋና መልዕክተኛ ሲጠቁማቸው፣ በሀፍረት ተውጠው ከየወንበራቸው እየዘለሉ ሮጠው ሲወጡ ሁላችንም ተመልክተናል::</u>

ስለዚህ፤ የተባበሩት መንግሥታት፣ አዲሲቷ ጣልያን እየተባለ የሚሰጠው መጠሪያ ትክክል አለመሆኑን ማወቅ አለበት:: በዋናው ኮሚሲዮን ተጠንቶ በጠቅላላው ጉባኤ እንዲጸድቅ ስለቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሳውዲ ዓረቢያ መንግሥት አቋም የሚከተለው ነው::

1. ጣልያን በሊቢያም ሆነ በሱማሌ በማናቸውም መልክ መመለሱን በጥብቅ እንቃወማለን:: እኛ የምንጠይቀው፤ ሊቢያ፤ በሶስት የተከፈሉት አውራጃዎቿ በአንድነት ሆነው፣ በፍጥነት ነፃነቷን እንድታገኝ ነው::

2. ኤርትራ፤ ክርስቲያኖቹ የሚኖሩበት አውራጃዎች ሕዝቡ ኢትዮጵያን ስለሚፈልግ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀሉን እንደግፋለን:: የኤርትራ የምዕራቡ አውራጃ ግን፤ ከሱዳን ጋር ከመሆን በስተቀር ሌላ መፍትሔ ሊገኝለት አይችልም:: ...... »

የዓረቦቹ አቋም ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን የተመሠረተ ሲሆን፣ የቤቨን ስፎርሳን ፎርሙላ ለመቃወም ከወሰኑት የእስያ አገሮች መካከል፣ ሕንድና ፓኪስታን፤ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች በፍጥነት ነፃነት ለመቀበል የተዘጋጁ ናቸው ብለው አያምኑም:: ሁለቱ የማይግባቡ ወንድማማች አገሮች (ሕንድና ፓኪስታን) የሚሰነዝሩት መፍትሔ፤ ሰስቱም የቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶች ለጊዜው በተባበሩት መንግሥታት የሞግዚት አስተዳደር ቢቆዩ ይሻላል የሚል ነው::

በጠቅላላው፣ መስኮቦቹም ሆኑ ዓረቦቹ፣ የእስላም አገሮችም ሆኑ አስያውያኖቹ፣ የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት እንዲወድቅ ተቃዋሚነታቸውን ለማስተባበር ቢሞክሩም፣ ቀደም ሲል በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ድጋፋቸውን ከሰጡት አገሮች መካከል፣ ከዱተኛ ከሌለ በስተቀር የቀረበውን ረቂቅ ውሳኔ ከመጽደቅ የሚያከሽፈው ነገር ሊኖር አይችልም:: እንግሊዞች በጣም የተጨነቁት በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ከደገፉት አገሮች መካከል በመጨረሻው ሰዓት፣ አንዳንዶቹ በዓረቦች ተገዝተው ድምፃቸውን እንዳይለውጡ ነው:: ባደረጉት ክትትል፣ በሊቢያና በሱማሌ ጉዳይ የቀረበው ውሳኔ ሊወድቅ የሚችለው፤ ላይቤሪያና ሀይቲ፣ ሕንድና አውስትራሊያ እንደሚወስዱት አቋም ነው ብለው ጥርጣሬ አደረባቸው::

— አውስትራሊያ የኮመንዌልዝ አባል በመሆኑ፣ በታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ተፅዕኖ ከተቃዋሚነት ወደ ደጋፊነት ድምጹን እንደሚለውጥ ታወቀ::

— ሀይቲ፣ የፈረንሣይና የአሜሪካ መንግሥታት በየፊናቸው ለሬፑብሊኩ ፕሬዚዳንት ማሳሰቢያ ልከው ስለነበረ፣ ዋናው መልዕክተኛ ሚስተር ሰንት ሎት (ST.LOT) የድጋፍ ድምፅ እንደሚሰጥ በተስፋ ይጠበቃል::

— ላይቤሪያ፣ ትክክለኛ አቋሙ ምን እንደሆነ ለማወቅ ችግር ተፈጥሮ ነበር:: በጠቅላላው ጉባኤ ላይ ያደረገው ንግግር ሲታይ በኤርትራ ጉዳይ ድጋፉን ሰጥቶ፤ ትሪፖሊታንያን እና ሱማሌን የሚመለከቱትን ውሳኔዎች ለመቃወም መዘጋጀቱ ታወቀ:: እንግሊዞች ይህንን እንደተረዱ ላይቤሪያ ከተቃዋሚነት ወደ አብስቴንሽን እንዲለወጥ የአሜሪካኖች ተፅዕኖ እንዲያደርጉ ጠየቁ::

የሕንድ መልዕክተኛ በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ድምፅ ከመስጠት ስለተቆጠበ፣ አሁንም በጠቅላላው ጉባኤ ላይ በዚህ አቋሙ ከቀጠለ፣ ጉዳት አያመጣም:: ነገር ግን በልማድ እንደታየው የሕንድ አስተያየት የሚዋልል ስለሆነ፣ ከአብስቴንሽን ወደ ተቃዋሚነት ለመዛወር የሚያግደው ነገር አይኖርም የሚል ግምት ተወሰደ:: ስሞኑን የኔህሩ መንግሥት ባለሥልጣኖች ከአሜሪካ የጦር መሣሪያዎች በእርዳታ ለማግኘት፤ በዋሽንግተን ንግግር በማድረግ ላይ በነበሩበት ጊዜ፤ የስቴት ዲፓርትመንት ኃላፊዎች ለጠቅላላው ጉባኤ ስለጣልያን ኮሎኒዎች ጉዳይ የቀረበውን ሬዞሉሽን ሕንድ እንድትደግፍ መጠነኛ የሆነ ተፅዕኖ ማድረጋቸው ተሰምቷል:: ይህ በአሜሪካኖች በኩል የተሞከረው ውጤት የሚሰጥ ከሆነ፣ ቢያንስ የሕንድ ድምፅ በዋናው ኮሚሲዮን ላይ እንደሆነው በአብስቴንሽን ይቀጥላል እንጂ ተቃዋሚ አይሆንም በማለት እንግሊዞች ተስፋ አደረጉ::

በመጨረሻው ሰዓት አንድ ያልተጠበቀ አዲስ ነገር እንዳይፈጠር፣ የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች ልዩ ክትትል ሲያደርጉ፣ በድንገት በኮሪደሩ ውስጥ የሀይቲ ዋና መልዕክተኛ ሴናተር ሰንት ሎት ከዓረቦች መልዕክተኞች ጋር የተለየ ጭውውት ሲያደርግ አይተው ከፍ ያለ ጥርጣሬ አደረባቸው:: ወዲያውኑ አሜሪካና ፈረንሣይ ፈጣን እርምጃ ስለወሰዱ፣ በጥቂት ሰዓቶች ውስጥ፤ የሀይቲ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳንት በኒውዮርክ የመደበውን ዋና መልዕክተኛውን በስልክ ጠርቶ፣ የጣልያን ኮሎኒዎች የቀረቡትን መፍትሔዎች በሙሉ በመንግሥቱ ስም የድጋፍ ድምፅ እንድትሰጥ ብሎ አዘዘው::

ሴናተር ሰንት ሎት ከአገሩ መሪ በስልክ የተሰጠውን ትዕዛዝ በታላቅ አክብሮት ተቀብያለሁ እያለ ቢያወራም፣ የዓረቦቹ ወገን ለመሆን ልቡ ስለከጀለ፣

አንዳንድ ዘዴ መፍጠር ጀመረ:: ከአሜሪካ መልዕክተኞች ውስጥ፣ ወዳጄ የሚለውን አንድ ሰው ከስብሰባው አዳራሽ ለብቻው ወደ ውጭ ይጠራና፣ በምሥጢር ሀሳቤን ላካፍልህ ይለዋል:: « ...... የሀይቲ ፕሬዚዳንት ራሱ በልክ ደውሎ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ደግፍ ብሎ ትእዛዝ ሰጥቶኛል:: እኔ በራሴ በኩል አንድ ከፍተኛ የሆነ የሞራል ችግር አለብኝ:: የአንድ ጥቁር አገር እንደራሴ ሆኜ፣ እኔም ራሴ ጥቁር ሆኜ፣ ጣልያን የጥቁር አገሮች የሆኑትን ሊቢያንና ሱማሌን እንዲገዛ ድምፅ ስሰጥ፣ በአፍሪካውያንና በእስያውያን ወገኖቼ ዘንድ ከፍ ያለ ዕፍረት ይሰማኛል:: ከአገሬ መሪ የተሰጠኝን ትእዛዝ በትክክል መፈጸም ግዴታዬ መሆኑን አውቃለሁ:: ነገር ግን በራሴ ላይ ከሚደርስብኝ ትዝብትና ውርደት ለመሸሽ፣ ድምፅ መስጠት በሚጀመርበት ጊዜ፣ ምክትሌን በወንበሬ ተክቼ ከጉባኤው አዳራሽ ብወጣ በጣም ጥሩ ይሆናል ብዬ አሰብኩ:: የኔ ምክትል መልኩ ወደ ፈረንጆቹ የሚቀርብ፣ በትውልዱም ክልስ ስለሆነ፣ በደረሰን ትዕዛዝ መሠረት የሀይቲን መንግሥት ድጋፍ በኦፊሴል ሲያቀርብ፣ ምንም ዓይነት ይሉኝታ አይሰማውም:: በዚህ ዘዴ የተፈጸመ እንደሆነ አፍሪካውያኖቹም ሆኑ እስያውያኖቹ፤ እኔን ባለማየታቸው ቁጣቸው ሊበርድ ይችላል:: ...... » በሚል አነጋገር አሜሪካዊ ወዳጁን ደለለ:: ይኸ የጥሁ አሜሪካዊ ለሎሙ የላቲን አሜሪካ አገሮች ጉዳይ አማካሪዎች ከሆኑት ዲፕሎማቶች አንዱ ነው:: ሴናተር ሰንት ሎት የነገረውን ምንም ዓይነት ጥርጣሬ ሳያድርበት አሜን ብሎ ተቀበለ፤ «...... በሀይቲ በኩል የሚያሳስብ ነገር የለም:: ፕሬዚዳንቱ በስልክ ለዋናው መልዕክተኛ ድጋፍ እንዲሰጥ ያስተላለፈው ትዕዛዝ ይፈጸማል ...... » የሚል ዜና ለታላቋ ብሪታንያ እና ለፈረንሣይ መልዕክተኞች ነገረ:: ፈረንሣይና ላቲኖቹ ከአሜሪካዊው ዲፕሎማት በደረሳቸው ዜና በጣም ተደሰቱ:: እንግሊዞች ግን፤ ያቺ በኮሪዶር ውስጥ ያይዋት፣ የዓረቦችና የሀይቲ መልዕክተኛ ሹክሹክታ ከንክኗቸዋል:: ሆኖም ሴናተር ሰንት ሎት የመሪውን ትዕዛዝ ጥሶ የት ሊገባ ? ብለው ማሰባቸው አልቀረም::

በጠቅላላው ጉባኤ ላይ ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ በፊት፣ በእንግሊዞችና በአሜሪካኖች በኩል የተደረገው የደጋፊዎችና የተቃዋሚዎች ቆጠራ ተሰፋ የሚሰጥ ሆኖ ተገኘ:: ይኸውም፣ የሀይቲ ወደ ደጋፊነት መራመድ፣ ኢትዮጵያ በትሪፖሊታንያ ጉዳይ ከተቃዋሚነት ወደ አብስቴንሽን መዛወር፤ የአባል አገሮችን ሁለት ሶስተኛ የድጋፍ ድምፅ ለማሟላት ሂሣቡ ትክክል ይመታል:: በተጨማሪም ላይቤሪያ ኢትዮጵያን ለመደገፍ ሲል ከተቃዋሚነት ወደ አብስቴንሽን ቢለወጥ፤ ሬዞሉሽኑ እንዳይከሽፍ አንድ መጠባበቂያ ይኖራል ተብሎ ተሰፋ ተደረገ::

## የማክሰኞ ግንቦት 17 ቀን ድራማ

እነዚህን ሲንገላቱ የኖሩ የቀድሞ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች የወደፊት ዕድል የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት የተጠበቀው፣ በዚች በግንቦት 17 ቀን 1949 ዓ.ም በማክሰኞ ምሽት ነበር::

ለአርባ ሁለት ቀናቶች የኤርትራ፣ የሊቢያና የሱማሌ ጉዳይ በሰፊው ሲተችበትና ንግግር ሲደረግበት ከከረመ በኋላ፣ በንዑስ ኮሚቴ «15» እና በዋናው ኮሚሲዮን ተበጥረው የተዘጋጁትን መፍትሔዎች፣ መላው የተባበሩት መንግሥታት አባሎች፣ በጠቅላላው ሰብሰባ ላይ ድምፅ በመስጠት እንዲያጸድቁ ወይም እንዲሽሩ ተጠየቁ::

-- ሶቪየት ሕብረትና ሳቴሊቶቹ፣ ዓረቦቹና እስያውያኖቹ፣ ተቃውሞአቸውን በማጠንከር በተለይ የሊቢያንና የሱማሌን ጉዳይ ለማስናከል ቆርጠው ተነስተዋል::

-- የላቲን አሜሪካ አገሮች ከፈረንሣይ ጋር ሆነው፣ በተለይ የትሪፖሊታንያ አውራጃና የሞቃዲሾ ሱማሌ ለጣልያን እንዲሰጡ፣ የድጋፍ ድምፃቸውን አስተባብረው ቀርበዋል::

-- እንግሊዞች የሲረናይከን አውራጃ ይዞ ለመቆየት ያላቸው ፍላጐት ጽኑ ስለሆነ፣ ሊቢያን በሚመለከት ጉዳይ ደጋፊዎች ሆነው ከተቆጠሩት አባል አገሮች መካከል፣ አንዱ በድንገት ሀሳቡን በመለወጥ እንዳይከዳቸው ሥጋት ቢኖራቸውም፣ ዘጠና በመቶ የቀረበው መፍትሔ እንደሚጸድቅ ተስፋ አድርገዋል::

በጠቅላላው ጉባኤ እንዲጸድቅ የቀረበው ዶክመንት፣ ለእያንዳንዱ የቀድሞ ቅኝ ግዛት በየአገሩ እየለየ መፍትሔውን የሚደለድል ስለሆነ፣ የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች ለማጽደቅም ሆነ ለመሻር፣ ድምፃቸውን የሚሰጡት በእያንዳንዱ አገር ጉዳይ ላይ ነበር::

የጠቅላላው ጉባኤ ፕሬዚዳንት አውስትራሊያዊው ሚስተር ኤቫት፣ (MR.H.V.EVATT) በቀረቡት ረቂቅ ውሳኔዎች ላይ፣ በቅደም ተከተል አባል አገሮች ድምፃቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቅ፣ የሀይቲ መንግሥት የመልዕክተኞች መሪ በዚሁ ሰዓት ወንበሬ ላይ አልገኝም ብሎ የተናገረውን ቃል ለውጦ፣ ከውጭ እየሮጠ ወደ አዳራሹ ገብቶ ቦታውን ሲይዝ እንግሊዞች ተመልክተው፣ ወዲያውኑ የአሜሪካንን እና የፈረንሣይን መልዕክተኞች ቀሰቀሱ:: « ...... በመጨረሻው ደቂቃ የሴናተር ሰንት ሎት ወንበሩ ላይ መመለስ ያለ ጥርጥር የፕሬዚዳንቱን ትዕዛዝ እሱ ራሱ መፈጸም ግዴታው መሆኑን ተገንዝቦ ነው፤ ...... » የሚል ማብራሪያ ከአሜሪካ መልዕክተኞች በኩል ለእንግሊዞች ተሰጠ:: ይህም ቢሆን የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች ያደረባቸውን ሥጋት አላቃለለውም::

የሀይቲ ዋና መልዕክተኛ የድምፅ መስጫው ሲቃረብ ወደ ወንበሩ የተመለሰበት ምክንያት፣ አሜሪካኖች እንደተረጐሙት ሳይሆን፣ ከአገሩ መሪ የደረሰውን መምሪያ ለመለወጥ ከእሱ ከራሱ በስተቀር ሌላ ሰው መተካት ስለማይችል ነበር:: ሴናተር ሰንት ሎት የመንግሥቱን ትዕዛዝ ጥሶ የራሱን ፍላጐት ሲፈጽም፣ ከሚመራቸው መልዕክተኞች መካከል ኃላፊነት የሚሰማው ታዛቢ አጠገቡ እንዳይኖር ስለፈለገ፣ ምክትሉን ሚስተር ሾቬልን፣ « ..... እኔ ጉባኤው እስኪፈጸም ቆይቼ አስፈላጊውን አደርጋለሁ:: ..... አንተ ከወዳጆችህ ቀደም ሲል የተቀበልከውን ግብዣ ለማክበር መሄድ ትችላለህ፤ ..... » ብሎ አሰናብቶት ስለነበር፣ የሚስተር ሾቬል አዳራሹ ውስጥ አለመገኘት የእንግሊዞችን ጥርጣሬ አባባሰው:: ቀደም ሲል እንደተገለጸው በቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ፣ አባል መንግሥታት ድምፅ እንዲሰጡበት የሚጠየቁት፣ ለእያንዳንዱ አገር በቀረበው መፍትሔ ላይ ነው:: ለሊቢያና ለሱማሌ የተዘጋጁት መፍትሔዎች ሲቀርቡ፣ የሀይቲ ሬፑብሊክ መንግሥት የመልዕክተኞች መሪ፣ ከአገሩ ፕሬዚዳንት የተሰጠውን ትዕዛዝ ጥሶ ተቃዋሚነቱን ሲገልጽ፣ የታላቋ ብሪታንያን እና አዲሲቷ ሬፑብሊክ የተባለችውን የጣልያንን መንግሥታት እንጀት አሳረረ:: በተዘዋዋሪ ጉዳናም የኢትዮጵያን ዕድል አስናከለ::

በኤርትራ ጉዳይ፣ ከምዕራባዊው ቆላ በስተቀር ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀድ የቀረበው ሀሳብ፣ በሠላሣ ሰባት አገሮች ተደግፎ ሕጉ ከሚጠይቀው ከሁለት ሶስተኛው የበለጠ ድምፅ ማግኘት ቻለ:: ነገር ግን በጣልያን ሞግዚትነት እንዲቆዩ የተባሉት አገሮች ጉዳይ በታየ ጊዜ፣ የአባል መንግሥታትን ሁለት ሶስተኛ ድምፅ ለማግኘት፣ ትሪፖሊታንያ፤ ዕድሜ ለሀይቲ መልዕክተኛ አንድ ድምፅ ብቻ፤ ሱማሌ፤ እድሜ ለሀይቲና ለላይቤሪያ ሁለት ድምፅ ብቻ፤ ስለጐደላቸው፤ እነዚህ መፍትሔዎች የማይጸድቁ ሆኑ::

ለኢትዮጵያ የታሰበው የኤርትራ ጉዳይ ከአስፈላጊው ቁጥር የበለጠ ድጋፍ ሲያገኝ፣ ትሪፖሊታንያ እና ሱማሌ ተፈላጊው ድምፅ ሳይሞላላቸው የቀሩት፣ ጣልያንን ለመጉዳት በማሰብ ነው በማለት፤ የላቲን አሜሪካ አገሮችና ፈረንሣይ እንደ እሣት ነደዱ:: እነዚህ የጣልያን ወዳጆች ወዲያውኑ ተነሣስተው፤ ይህንን የቤቨን ስፎርሳ የተባለውን ፎርሙላ አሸቀንጥረው ለመጣል ድምፃቸውን ማሰትባበር ጀመሩ:: እነሱ እንደፈለጉትም የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ለመወሰን የቀረቡት መፍትሔዎች በሙሉ በአንድነት አጠቃላይ ድምፅ እንዲሰጥባቸው ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ አቀረቡ ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውሳኔ የሚከናወነው በትክክለኛ የፍርድ ሚዛን ላይ ተመሥርቶ ቢሆን ኖሮ፤ ለእያንዳንዱ አገር የቀረቡት የውሳኔ ሀሳቦች የአባሎቹን ሁለት ሶስተኛ የድምፅ ብልጫ ያገኙት እየጸደቀላቸው፣ ሌሎቹ ድምፅ የጐደላቸው ውሳኔዎች ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፉ ማድረግ ይቻል ነበር:: ነገር ግን ላቲኖቹና ፈረንሣዮቹ የሚፈልጉት የጣልያን ዕድል ከተሰናከለ፣ የሌላውም አብሮ እንዲወድም ስለሆነ፣ በቤቨን ስፎርሳ ስምምነት መሠረት የተዘጋጁት መፍትሔዎች እንዲሰረዙ አጠቃላይ ድምፅ ካልተሰጠባቸው ብለው ተሟገቱ:: አሁንም እነሱ እንደፈለጉት፤ በእነዚህ ሶስት ረቂቅ ውሳኔዎች ላይ አባል መንግሥታት ድምፅ እንዲሰጡበት ሲጠየቁ፣ በጥቂት ሰዓቶች ውስጥ ነገር ተለውጦ፣ ሰላሣ ሰባት አገሮች መፍትሔዎቹ እንዳይጸድቁ ሲቃወሙ፤ ደጋፊዎቹ አሥራ አራት አገሮች ብቻ ሆኑ:: ይህንን ጥሩ አጋጣሚ በማየት ከመቅጽበት የፖላንድ መልዕክተኛ ተሽቀዳድሞ « ...... ይህ ጉዳይ ትክክለኛ የሆነ ፍርድ እንዲያገኝ ከአራት ወራት በኋላ በመስከረም 1949 ዓ.ም ለሚከፈተው የአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲተላለፍ እጠይቃለሁ:: ...... » የሚል ሀሳብ አቀረበ::

ከሚያዝያ 6 ቀን 1949 ዓ.ም እስከ ግንቦት 17 ቀን ድረስ፣ የእነዚህ የቀድሞ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች ጉዳይ ብዙ ውዝግብ ያስከተለና፤ የየመንግሥታቱን መልዕክተኞች ያዳከመ በመሆኑ፤ ውሳኔው ለመጭው ስብሰባ እንዲተላለፍ ከፖላንድ የቀረበውን ሀሳብ አባሎቹ ለመቀበል ጊዜ አልወሰደባቸውም:: ፖላንድ ይህን ሀሳብ ያቀረበው የታላቁ መሪው የሶቪየት መንግሥት አስተያየት በዚህ ጉባኤ ላይ ተደማጭነት በማጣቱ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነበር:: ሌሎቹ አገሮች ግን፤ ይህን ሀሳብ የደገፉት ከመሰላቸትና ከመዳከም የተነሳ፤ ለጊዜው ከንትርኩ ወጥተን እስከ መስከረም ድረስ እፎይ እንበል ብለው ነው:: በመጨረሻው ከፖላንድ መልዕክተኛ የቀረበውን ሀሳብ ኢትዮጵያ ብቻዋን ስትቃወም፣ በሃምሣ አንድ አገሮች ድምፅ ተደግፎ፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ዶሴ በሙሉ፤ በመስከረም አጋማሽ 1949 ዓ.ም ለሚከፈተው ለአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲተላለፍ ተወሰነ::



ሱማሌና ትሪፖሊታንያ ለጣልያን እንዳይመለሱ በድምፁ ያስናከለው የሀይቲ መልዕክተኛ ኤሚል ሰንት ሎት ከቀኝ በኩል የቆመው ነው:: በሀይቲ ድምጽ መለወጥ ምክንያት የኤርትራም ግዛት በከፊል ወደ ኢትዮጵያ እንዲቀላቀል የተደረገው ውሳኔ ሳይጸድቅ ቀረ::

(ግንቦት 17ቀን 1949)
(ፎቶ U.N)